ፍኖተ
# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ሚያዝያ 2 ቀን 2004 ዓ.ም. ዋጋ ብር 6.00

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.37

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## የራሳችንን ህንፃ ለመገንባት መልስ እየተጠባበቅን ነው

አቶ ፀጋዬ አላምረው



### የባህል ባሪያ የገበያ ባሪያ የመንግሥት ባሪያ
ዶ/ር ኃይሉ አርአያ 3

### የአዋቂ አጥፊው የብሔራዊ ባንክ ገዥ
በበለጠ ጐሹ ወ/ሚካኤል 12

### ኢትዮጵያውያን ሀገራችን የት ነው?
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ 14






### አዲስ አበባ 23ኛውን ዓለም አቀፍ ጤና ጉባዔ ታዘጋጃለች
11

### በኢትዮጵያ ከፍተኛ ረሃብ ሊከሰት እንደሚችል ተገለፀ
11

### ፍትህ አጣሁ ያለው የመንግስት ሠራተኛ ፍ/ቤት ግቢ ውስጥ ካለው ዛፍ ወጥቶ አልወርድም አለ
13

# አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ክስ መሠረተ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ላይ መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም በፌደራል ከፍተኛ ደረጃ ፍ/ቤት 9ኛ የፍትሀ-ብሔር ችሎት ክስ መሰረተ፡፡

የአንድነት ፓርቲ የክስ ጭብጥ እንደሚያስረዳው የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት "አኬልዳማ" በተሰኘና በሦስት ተከታታይ ክፍል በቀረበ ዘገባ ላይ የፓርቲውን መልካም ስም፣ክብርና ዝና ያጠፋ ሲሆን ይሄንኑ የስም ማጥፋት ተገደው መልስ እንዲያወጡ ለማስወሰን የቀረበ ነው፡፡

ተከሳሾችም አንደኛ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ሲሆን በሁለተኛነት አቶ አብዲ ከማል ናቸው፡፡ መጋቢት 26 ቀን ይሄው ክስ የደረሳቸው ሁለቱ ተከሳሾች ሚያዝያ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ሬጅስትራር መልስ ይዘው እንዲቀርቡ ታዟል፡፡

የክሱ ዝርዝር በአጭሩ እንደሚያስረዳው አንደኛ ተከሳሽ በ2ኛ ተከሳሽ አዘጋጅነት ከህዳር 16-18 ቀን 2004 ዓ.ም «አኬልዳማ» በሚል ርዕስ በሦስት ተከታታይ ክፍል ባቀረቡት የቴሌቪዥን ፕሮግራም የከሳሹን አንድነት ፓርቲ ስም፣ክብርና ዝና የሚያጠፋ በድምፅ፣በምስልና በፅሁፍ የተቀነባበረ ዘገባ በማቅረብ የስም ማጥፋት ፈጽሟል" ይላል፡፡

ይሄንኑ የክስ ዝርዝር በማብራራትም በአኬልዳማ ዘገባ በዲሲፕሊን ግድፈት ከድርጅቱ የተባረሩትን በራሳቸው ፈቃድ ከድርጅቱ የለቀቁትን እንዲሁም በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው በሕግ ቁጥጥር ሥር የሚገኙትን ግለሰቦች የአንድነት አባል ናቸው በማለት በድምጽ፣በምስልና በጽሑፍ የተዘጋጀ የሀሰተኛ ዘገባ አቅርቧል" በማለት ያብራራል፡፡

በተጨማሪም "አንድነትንና ህጋዊ አባላቱን የሁከትና የብጥብጥ ፈጣሪዎች ናቸው በማለት፤አሸባሪ ተብሎ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ 78 ሺህ አባወራዎች ከደቡብ ተፈናቀሉ

በተለያየ ምክንያት፣ በተለያየ ጊዜ፣ ደቡብ ክልላዊ መንግሥት ሰፍረው ንብረትና ቤተሰብ አፍርተው ይኖሩ የነበሩ 78ሺ አማርኛ ተናጋሪ አባወራዎች አስከ 2006 ዓ.ም ተጠቃለው እንዲወጡ መታቀዱን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ዋና ፀሐፊ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ አቶ ተስፋዬ አገኘሁ ያሉትን መረጃ በማጣቀስ እንደገለጹልን ‹‹በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ተፈርሞ በወጣው ደብዳቤ መነሻ ዜጐች ከመኖሪያቸው እየተፈናቀሉ ለስቃይ ተዳርገዋል" ብለዋል፡፡

ከደቡብ ክልል ቤንቺ ማጂ ዞን ጉራ ፋርዳ ወረዳ የተፈናቀሉ አርሶአደሮች በተለያየ ጊዜ አዲስ አበባ መጥተው መኢአድ ጽ/ቤት ተጠልለው የነበሩ ቢሆንም የመንግሥት አካላት መጥተው ‹‹ማሪፊያ ቦታ እንስጣችሁ›› ብለው ከወሰዷቸው በኋላ 6 ኪሎ አካባቢ በሚገኘው አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስድስት ግቢ ማረፋቸው ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን ለእያንዳንዱ አባወራ ብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ እየሰጡ የያዛችሁትን እቃ እየሸጣችሁ ወደ አገራችሁ ግቡ ተብለው ከግቢው እንደተባረሩ ተፈናቃዮች ይናገራሉ፡፡ ‹‹ሁለት መቶ ብር አምስትና ስድስት ቤተሰብ የት ያደርሰናል? ሄደንስ ማን ይቀበለናል? ምን ማረፊያ ቦታስ አለን? ብለን ብንጠይቅ የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ወደትውልድ ሥፍራችሁ ሂዱ፤ እያሉ ከግቢ በፖሊስ አባረሩን›› በማለት ለዝግጅት ክፍላችን ይገልጻሉ፡፡

ሌሎች ከግቢው ተባረርን የሚሉ ደግሞ እኛን ከግቢው ያባረሩን ቀድመው ነው፡፡ ግቢው ውስጥ የነበርነውን ቁጥራችን በርካታ ሰዎች ስብሰባው ደረሰብን የምትሉትን ችግር በዝርዝር ጽፋችሁ አምጡ አሉን፡፡ መጽሐፍና ማንበብ የማይችል በቃላችን እንናገራለን አሉ፡፡ መጽሐፍ የምንችል ችግሩን ዘርዝረን ጻፈን፡፡ ጽሑፋችንን ሰብስበው ወስደው ካነበቡ በኋላ ችግሩን በዝርዝር የጻፍነውን አምስት ሰዎችን መርጠው ሰው ወደ የትውልድ ሀገሩ እንዳይሄድ የምታስተባብሩት እናንተ መሆናችሁን ደርሰንበታል ብለው በቅድሚያ ከሕዝቡ ነጥለው አባረሩን፡፡ ከእንግዲህ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

**የህዳሴ ግደቡን በተመለከተ ኢህአዴግ ሚያራሚደዉ አቋም ከልማቱ ይልቅ ለረዥም የስልጣን ዘመን ማሳመኛ ከማዋሉም በላይ ዝቅተኛ የምረታማነት ደረጃ ያለዉ መሆኑ በጥናቶች ተረጋግጧል፡፡ የግድቡ መሰራት የሚወደድ ቢሆንም ካለዉ ነባራዊ ሁነት አንፃር የሚያመጣቸዉ ተያያች ችግሮ አሉት የሚለዉ ሰለሞን ስዩም የተለያዩ ጥናቶችን ዳሷል፡፡**

# ከልማቱ ይልቅ ለረዥም የስልጣን ዘመን ማሳመኛ የዋለዉ የታላቁ የህዳሴ ግድብ



ሰለሞን ስዩም

**ምርጫ 2002፤ኢህአዴግ ወደ አውራ ፓርቲነት ወይስ ወደ ፈጣን የቁልቁለት ጉዞ?**

ምርጫ 2002 ውጤት በሀገር ውስጥና ውጭ ያሉትን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሊቃን ግርምት ፈጥሮ ነበር፡፡ ኢህአዴግ 99.6 በመቶ "ምርጫ ውጤት" ተከትሎ ወደ አውራ ፓርቲነት መሸጋገሩን በአቶ መለስ በኩል ተገልጾ ነበር፡፡ በወቅቱ ከነበረው አጠቅላይ ሁኔታ በመነሳት የኢህአዴግ የረጅም ዓመት ጠቅላይ ገዥነት የተረጋገጠ መሰለ፡፡

በሌላ በኩል፣ የ99.6 በመቶ ውጤት የኢህአዴግን የቁልቁለት ጉዞ የሚያሳይ ነው የሚሉ ነበሩ፡፡ የአንድነት ፓርቲ ስትራቴጂ ሰነድ ገፅ 90 ላይ እንደተቀመጠው "በኢህአዴግ በኩልም ከገነባው ጤናማ ያልሆነ የግዝፋት መጠን በላይ መሄድ እንደማይችልና የወደፊት አቅጣጫውም ወደታች መውረድ ብቻ መሆን መገመት ይቻላል..." ይላል፡፡

የምርጫ 1997 ትውስታ ሙሉ በሙሉ ባልጠፋበት በዚያ ወቅት፣ የተሻለ ትግል ስትራቴጂ የቱ ነው የሚለው አንገብጋቢ ጥያቄ በስፋት የተነሳበት ነበር፡፡ የምርጫ 2002 ውጤት፣ የሰላማዊ ትግል በኢትዮጵያ የተሻለ አማራጭ አለመሆኑን እንደ አንድ ማስረጃ አድርገው የተከራከሩ ነበሩ፡፡

በዚህ ዓይነት የድል መንፈስ ውስጥ የነበረው ገዥው ፓርቲ፣ የዕድገትና ትራንስፎረሜሽን ዕቅዱን ይፋ አደረገ፡፡ ይህም በሕዝብ ውስጥ ያለውን ተቀባይነት ይበልጥ ለማሳደግ በከፍተኛ ፕሮፓጋንዳ ስራ ላይ ተጠመደ፡፡

ይሁን እንጅ ዜጎች አደብ ሊገዛ ባልቻለው የዋጋ ግሽበት፣ የኃይል መቆራረጥ፣ የሥርዓቱ በሙስና መጨማለቅና መሰል ጉዳዮች፣ ኢህአዴግ ሊፈታው አይችልም ወደሚል መደምደሚያ እየደረሱም ነበር፡፡ ይባስ ብሎ በቱኒዚያ የተቀጣጠለው የለውጥ ንቅናቄ መላ ሰሜን አፍሪካንና መካከለኛውን ምስራቅ ያጥለቀልቅ ጀመር፡፡ የዚህ የለውጥ ንፋስ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የአፍሪካ አገሮች የመዛመት ዕድልን ከፍተኛ ውይይት የቀሰቀሰ ጉዳይ ሆነ፡፡

**የለውጥ ንፋስ ወደ ኢትዮጵያ?**

በ2003 ዓ.ም ሰሜን አፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞ አስተናገደች፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ አሰላሳዮች አብዮቱ ከሚስፋፋባቸው ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነች ተናገሩ፡፡ በተለይ የከተማ ነዋሪ፣ ዓይኑን አልጀዚራና ቢቢሲ ላይ ተክሎ መዋል ጀመረ፡፡ በየካፌውና አደባባዩ ወሬ ሁሉ ቤን አሊ፣ ሙባሪክ፣ ጋዳፊ ሆነ፡፡ በዚያው ወቅት ኢህአዴግ በልሳኖቹና "በሕዝብ" መገናኛ ብዙሃን በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ የዓረቡ ዓይነት አብዮት ሊቀሰትበት የሚችል ነባራዊ ሁኔታ ፈጽሞ እንደሌለ ለማሳመን እንቅስቃሴ ያደርግ ጀመረ፡፡

ይሁን አንጂ ውስጥ ውስጡን እንደሚወራው የኢህአዴግ አስኳል የሆነው ህወሓት፣ የዓረቡ ዓለም ዓይነት አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ የመከሰት ዕድል እንዳለ ግንዛቤ ወስዶ ነበር፡፡ ይህን ፍርሃት ይበልጥ ያጠናከረው በማላዊ፣ በሁጋንዳ፣ በሱዳንና በሌሎች ከሰሃራ በታች የሆኑ የአፍሪካ አገሮች ታይተው የነበሩት አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡

**"ቀድሞ የመግታት" ስትራቴጂ?**

የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንን እነቅስቃሴ ወደ ኢትዮጵያ ይስባሉ ያላቸውን እንቅስቃሴዎች በመግታት፣ ግለሰቦችን በተለያዩ ዘዴዎች ለማስወገድ ተንቀሳቀሰ፡፡ ይህንን የተመለከቱ ፖለቲከኞች ጉዳዩን "ቀድሞ መግታት" ነው ሲሉ ተነተኑ፡፡

ህዝብን ለለውጥ ወደ አደባባይ ይገፋፋሉ ተብሎ ከተለዩ ጉዳዮች ውስጥ ዋንኛው የዋጋ ንረቱ ነበር፡፡ ይህን ለመከላከል ታስቦ ታህሳስ 2003 ዓ.ም. አካባቢ መንግስት የዋጋ ተመን መውጣቱን አስታወቀ፡፡ በወቅቱ መግለጫውን የሰጡት አቶ መለስ፣ የራስ መተማን አይታይባቸው ነበር፡፡ በአጠቃላይ ከአቶ አህመድ ቱሳና ከአቶ ንዋይ ገብረአብ ጋር በመሆን የሰጡት ማብራሪያ ላይ የፊታቸው ሁኔታም የጤነኝነት ሲሜት አይታይባቸዉም ነበር፡፡ የዋጋ ተመን ጉዳይ የተተለመለትን የዋጋ ማረጋጋት ከማምጣ ይልቅ፣ ይበለጥ የገቢያ ምስቅልቅል አስከተለ፡፡

በሌላ በኩል ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ "ሊመጣ ይችላል" ተብሎ ከተፈራው ሕዝባዊ ማዕበል ሊከላከል የሚችል የፕሮፓጋንዳ አቅም አለው ተብሎ ኢህአዴግ ሊያምንበት የቻለ አይመስልም ነበር፡፡

በሌላኛው የሳንቲም ገፅ፣ሕዝቡን በልማት ስም ለመማረክ አዎንታዊ ነገሮችን መምረጥ ያስፈልግ ነበር፡፡ ችግሮችን ይበልጥ አግዝፎና በ1000 አባዝቶ ለሚያየው የኢህአዴግ አስተሳሰብና አሰራር፣ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን "ሊመጣ ይችላል" ተብሎ ከተፈራው ሕዝባዊ ማዕበል ሊከላከል የሚችል የፕሮፓጋንዳ አቅም አለው ብሎ እምነት ሊጥልበት አልቻለም፡፡ በዚህ ሰዓት ነበር አቶ መለስ ቤኒሻጉል ሄደው፣ ስለአባይ ግንባታ መጀመር ያስታወቁት፡፡ የአቶ መለስ "ቁማርተኝነት" በግልፅ ገጦ የወጣውም የዚያን ጊዜ ነበር፡፡

ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ የፖለቲካ ተመራማሪ "ኢህአዴግ የተቃዋሚዎችንና የሕዝቡን የመታገያ አጀንዳ መቀማት ጀምሯል" ይላሉ፡፡ ተመራማሪው በኢትዮጵያ ታሪክ፣በባንዲራ ጉዳይ፣ በሀገራዊ ብሔርተኝነት ዙሪያ የተቃዋሚዎችን ሐሳብ በመንጠቅ የመታገያ አጀንዳ ለማሳጣት እንደሚሞክር ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ትንተ ናቸው ጋር የሚስማማው አባይን ለመገደብ የተደረገው የድንገቴ ውሳኔ ነው፡፡

በአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ ተመራማሪና መምህር የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና "ልማትን የሚቃወም ተቃዋሚ የለም፤ ነገር ግን ለምን አባይ፣ለምን አሁን?" ማለት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የዩኒቨርስቲው የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙት መምህር "ኢህአዴግ ዕድለኛ ነው" ሲሉ ይጀምራሉ፡፡ በራሳቸው ትንተና አባይን መጠቀም የኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ህልም ነበር፡፡ በመሆኑም እንደማንኛውም ባህል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ቁጭት የተፈጠረበት ነገር-ሀሳብ ሆኗል፡፡ በመሆኑም "አባይን ለመገደብ በድንገቴም ቢሆን መነሳት የአረቡ ዓለም አብዮትን መስፋፋት ማስቀረት ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግ የሌላውን የሕዝባዊ ተቀባይነት ለማግኘት የሚረዳው ነው" ይላሉ፡፡ በስም አወጣጡ ዙሪያ ሀሳብ የሰጡ ኤክስፐርቶች ከ "ታላቁ የሚሊኒየም ግድብ" ወደ "ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ" የዞረበት አኳኋን የኢህአዴግን "የለውጥ ጠቅላይነት" የሚወክል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

**ለምን አሁን /2003/?**

በመግቢያ ለማንሳት ከተሞከረው ሀሳብ በተጨማሪ ዶ/ር መረራ ጉዲና ጉዳዩን ወደ ምርጫ 2002 ያገኘው ውጤት ግራመጋባት ፈጥሮበታል፡፡ ያ ውጤት ሊገኝ የሚችለው የተለየ የማጭበርበር ስልት ሲካሄድበት ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የሚከሰተውን የተዓማኒነት ማጣት ኪሳራን ለማስቀየስ ሌላ "አሉታዊ" ነገር መቀየስ ግድ ይላል፡፡ በዶ/ር መረራ አረዳድ ይሄ "የዕድገት እና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ" ነው፡፡

የዕድገትና የትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ የ2002ቱን መደናገርና የ97ቱን የሕዝብ ኩርፊያ በሚነሳው አቧራ ለመሸፈን ነበር፡፡ ሆኖም የታቀደውን ያክል ሳይሆን ከመቅረቱም በላይ ሁሉንም የሚደመስስ ነገር በአረቡ የአፍሪካ አካባቢ ተከሰተ፡፡

ስማቸው እንዳይገለፅ የጠየቁት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ መምህሩ ውሳኔው ድንገቴ መሆኑ ለማየት "በቂ ጥናት ተደርጓል ወይ? የሚል ጥያቄ በመጠየቅ እንመልሳለን" ይላሉ፡፡ ግድቡ የተበሰረው በዘዴ ነው፡፡ ግብፅን ሲወቅሷት በነበረው የትነት ልክ በ45-50C መካከል ያለበት አካባቢ የተጀመረ እንዲሁም መጀመሪያ ያመነጫል ከተባለው በላይ የአንድ ተጨማሪ ግድብ ያክል መስተካከሉ" መልስ ይሰጠናል ይላሉ፡፡ የቤልጅየም ጋንት ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ኢኮኖሚ መምህር አለማየሁ ስሜ "የአባይ ግድብ ሃሣብ በድንገት የመጣነው" ይላሉ፡፡ መምህሩ ዶ/ር አለማየሁ ሰሜ "በኢህአዴግ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ አልተካተተም ነበር፡፡ አስቀድሞ በጀት ሳይያዝለት የመሠረት ድንጋይ የተጣለለት ነው" ይላሉ፡፡ ዓለም አቀፋዊ አውድ መመርመር ተገቢ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ በግብፅ ግዙፍ አብዮታዊ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ነበር፡፡ የአሜሪካ መንግሥት የግብፅ አብዮት አቅጣጫን በትክክል ለማወቅ አልቻለም፡፡ የአሜሪካ መንግሥት ዋነኛ ሥጋት ግብፅ እና እስራኤል የተፈራረሙት የካምፕ ዴቪድ ስምምነት እንዳይፈርስ ነው፡፡ አክራሪ ሙስሊሞች ሥልጣን ከያዙ ይህ ስጋት እውን ሊሆን እንደሚችል ፍራቻ እንደነበር ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም የሰሜን አፍሪካ አብዮት መዛመቱን ለመከላከል ኢህአዴግ የቀየሰው የአባይ ግድብ ከአሜሪካ መንግሥት ፍላጎቶች ጋር ተገጣጠሙ፡፡

**የግደቡ ወጪ ቆጣቢነትና ምርታማነት**

በአሜሪካን ሀገር በቦስተን የሚኖሩ መኀሪ በየነ የተባሉ ተመራማሪ "How efficient is The Grand Ethiopian Renaissance Dam?" በተባለ ጥናታቸው የግድቡን ወጪ ቆጣቢነትና ምርታማነት ከተለያዩ ሀገራት ጋር እያወዳደሩ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

ከሕዝብ በተሰበሰበ ነው በተባሉ ጥያቄዎች ዙሪያ ዝግጅት የተደረገበት የሚመስል ማብራሪያ የሰጡት ጠ/ሚ/ መለስ ዜናዊ ከየትኛውም ግድብ በተሻለ ከትንሽ ውጭ ትልቅ ኃይል የሚመነጭበት ፕሮጀክት መሆኑን አትኩሮት በመስጠት

| ተራ ቁ. | ሀገር | የማመንጨት አቅም (በሜጋ ዋት) | ኃይል በሜጋ ዋት በሰዓት | ምርትማነት በመቶኛ (Energy %) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቼክ ሪፓብሊክ | 10 | 53 | 60 |
| 2 | ብራዚል | 800 | 3,714 | 53 |
| 3 | ብራዚል | 300 | 1,445 | 55 |
| 4 | ብራዚል | 15 | 72 | 55 |
| 5 | ህንድ | 18,134 | 84,193 | 53 |
| 6 | ቻይና | 7,483 | 37,364 | 57 |


ምንጭ፡ ከዓለም አቀፍ የኃይል ማመንጫ 2010

ጉዳዩን የተሻለ ለማብራራት የኢትዮጵያን መንግስት በመገንባት ላይ ያሉና በጥናት ሥር ያሉትን ፕሮጀክቶች ምርታማነትና ወጪ ቆጣቢነታቸውን በማየት ማጠናከር ይቻላል፡፡

| ተራ ቁ. | ፕሮጀክት | የማመንጨት አቅም (በሜጋ ዋት) | ኃይል በሜጋ ዋት በሰዓት | ምርትማነት በመቶኛ (Energy %) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሃለል-ወርበሻ | 422 | 2233 | 60 |
| 2 | ግልገል ግቤ IV | 1472 | 7500 | 58 |
| 3 | ግልገል ግቤ I እና II | 366 | 1788 | 56 |
| 4 | ገናሌ III | 258 | 1200 | 53 |
| 5 | ጨሞጋ የዳ | 278 | 1250 | 51 |
| 6 | ገናሌ VI | 256 | 1000 | 45 |

ምንጭ፡ የአፍሪካ ህብረት - አቶ ምህረት ደበበ በ2011 — "Hydropower for sustainable development" በማለት ካቀረቡት

የሁለቱን መልክ በዚህ መልኩ እንየው፤




አብራርተዋል፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ ከሌሎች ግድቦች ጋር ሲነፃር በግማሽ ድረስ ወጭ የሚቀንስ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የመኀሪ በየነ ጥናት የሚያሳየው ግን የህዳሴው ግድብ ከሌሎች መኀከለኛ ግድቦች ምርታማነት በ22% የሚቀንስ መሆኑን ነው፡፡

የህዳሴው ግድብ ወደ 6000 ሜጋ ዋት የሚጠጋ ኃይል የሚያመነጭ ሲሆን ምርታማነቱ 33% መሆኑን የመንግሥት ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡ በአቶ መኀሪ ትንተና 33% ምርታማነት የያዘው የህዳሴው ግድብ 60% ምርታማነት በመያዝ 2,872 ሜጋ ዋት ኃይል ለማምረት ከተገነባ የኃይል ማመንጫ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም አነስ ያለና ከፍ ያለ ምርታማነት በመያዝ ከ40-45% የግንባታ ወጭ መቀነስ ይቻል እንደነበር የዘርፉ ባለሙያዎች ያትታሉ፡፡ በመሆኑም 33% ምርታማ (15,128 Gwh x100%115.250 Gwx365 ቀናት በ24 ሰዓት) የሆነው የህዳሴ ግድብ በኢትዮጵያም በዓለም አቀፍ ደረጃም በጣም ዝቅተኛ ምርታማነት ያለው ነው፡፡

**በሕዝብ መዋጮ የሚሰራ ግድብ!**

የግድቡን ቴክኒካዊ የመተግበር ዕድል በተመለከተ ባለሙያዎች ግድቡ ሊሰራ እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡ የግንባታ ወጭውን ለመሸፈን የሚያስፈልገውን 80 ቢሊዮን ብር በላይ ከሀገር ውስጥ ለመሰብሰብ ነው የታቀደው፡፡ ይህ ሁለት ዓቢይ ጉዳዮችን የሚመልስ መሆን አለበት፡፡

አንደኛው ከሕዝብ የሚሰበስበው ገንዘብ እጅግ የሙሰኞች መዋቅር ነው በሚባለው "የመለስ ዜናዊ መንግሥት ሌቦች" በኩል ማለፉ ሲሆን ስርዓቱ ይህንን በምን ሊቆጣጠረው እንደሚችል ለመገመት አዳጋች ነው፡፡ ከፍተኛ የቁጥጥር ሥራ እንሰራለን የሚሉት ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ከወር በፊት የመንግሥታቸው ሌቦች እንዳስጨነቋቸው በፓርላማ ተናግረው ነበር፡፡


በሌላ በኩል ህብረተሰቡ በከፍተኛ የኑሮ ውድነት በመሰቃየት ላይ እንደ መገኘቱ የፕሮጀክቱ ገንዘብ የዋጋ ንረቱን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያባብስበት አጋጣሚ እጅግ ሰፊ ነው፡፡ ሀገራዊ ቁጠባ አቅማችን እጅግ ዝቅተኛ ነው፤ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚ ከ5 በመቶ ብቻ ነው፡፡ ከዜጎች የተሰበሰበ ገንዘብ ግድቡን ያጠናቅቃል የሚለው የመንግስት አቋም፣ "ጀብደኝነት" የተሞላበት ነው የሚሉ አልጠፉም፡፡ ለዚህም ማሳያ በአንድ ዓመት ውስጥ ከሕበረተሰቡ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደ 11 ቢሊዮን ብር ውስጥ መሰብሰብ የተቻለው 7 ቢሊዮን ብር ብቻ ነው፤ ከዕቅዱ 63 በመቶ በታች ማለት ነው፡፡ ጥያቄ ታዲያ ዓመታቱ በገፉ ቁጥር ሊሰባበው የሚችል ብር ይቀንሳል ወይስ ይጨምራል ነው፡፡

በቅርቡ የዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ተወካይ ጉዋንግ ዚ ቼን መንግስት ስር የሰደደ የገንዘብ ችግር እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ለዚህ ፕሮጀክት የሚሆን ገንዘብ የማግኘቱ እድሉ እጅግ ዝቅተኛ ነው የሚሉ አሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከዜጎች የሚሰባሰበው ብር ብዙ ተስፋ የማይሰጥ ከሆነ መንግስ ብዙ አመራጭ ላይኖረው ይችላል፡፡ አንድም የገንዘብ ዕትመትን መጨመር ሲሆን፣ ሌላው አማራጭ የደሞዝ ግብርና ከንግዱ ሕብረተሰብ ታክስ መጨመር ነው፡፡ ይህም እጅግ አደገኛ ቁማር ሊሆን ይችላል፡፡ አብዮት ለመከላከል ታስቦ የተወሰዱ ፕሮጀክቶች፣ አብዮትን ወደ ሀገራችን እንዳይጋብዝ ያሰጋል ብሎ የሚከራከሩ አልጠፉም፡፡

**የፕሮፓጋንዳ "ጐርፍ"**

የህዳሴው ግድብ ምርታማነትን በተመለከተ ከሌሎች ፕሮጀክቶች እጅግ የወረደ መሆኑን የመንግሥት መረጃ ራሱ ያሳያል፡፡ ከዚህ አንፃር ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸውን መካከለኛ ግድቦች ሕዝቡን ሳይጫኑ መገንባት ሲቻል በዚህ ደረጃ መጀመሩ ምን ትርጉም አንዳለው ማሰቡ ተገቢ ነው፡፡ የቤልጂየም ጋንት ዩኒቨርሲቲ መምህሩ "ኢህአዴግ ተሸርሽሮ ያለቀውን የፖለቲካ ተቀባይነታቸውን /legitimacy/ እንዲያንሰራራ ለማድረግ ይህ ግዙፍ ግድብ መታሰቡ መልካም አጋጣሚ ሆናቸው" ይላሉ፡፡ መምህሩ የዚህን ምክንያታዊነት ለመረዳት የህወሓት መራሹ ኢህአዴግ መንግሥት የኃጢያተኝነት ስሜትን መረዳት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ህወሓት /ኢህአዴግ በአብዛኛው መንፈሳዊ ሀገራዊ ጉዳዮችን በመሸርሸር የሚከሰስ ነው፡፡ ከዚህ ክስ ለመውጣት ብቸኛው አማራጭ የረዥም ዘመናት ቁጭቶችን መኮርኮር ነበር፡፡ በዚህ በዚህ ከኢትዮጵያ የታሪክ ዘመናት እኩል የሺህ ዓመታት ቁጭት ያዘለውን አባይ በዜሮ ባጀት እንኳ 'መድፈር' ለህወሓት/ኢህአዴግ" ከሰማይ የወረደ መና ነበር፡፡

ወደ 8ዞሯል



# የባህል ባሪያ የገበያ ባሪያ የመንግሥት ባሪያ

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ

ጎበዝ! ለንቱ ነው ባሪያ የምንሆነው? እስከ መቼስ ነው ባሪያ የምንሆነው? ኧረ አንድ በሉ!

እስቲ የባህሉን ባርነት እንመልከት? ከሥነ-ቃላችን እንጀምር፡፡

ጋሼ ማረኝ ማረኝ

ጋሼ ማረኝ ማረኝ

ዶሮ ብር አወጣች እኔ ሥጋ አማረኝ

ይህ ለመጀመሪየ ጊዜ የተባለው መቼ ነው? እኔ ግን የሰማሁት ልጅ ሆኜ ነው፤ በአፄ ኃ/ሥላሴ ጊዜ፤በ1940ዎቹ መጀመሪያ ገደማ፡፡ አስተውሳለሁ፡፡ ጃንሜዳ የጥምቀት ዕለት ነው የሰማሁት፡፡ ሥጋ ያማራት ሙሽራ ነች አሉ ይህን ያለችው ለባሏ፡፡ ይህን ከማለቷ በፊት የዶሮ ዋጋ ከብር በጣም ያነሰ ነበር አሉ፡፡ ሃምሳ ሣንቲም ነበር ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ታዲያ በሙሽሪት ጊዜ ዶሮ ብር አወጣችና አገር ጉድ አለ፡፡

የጉድ ነገር ሲነሳ፣ሳልረሳው አንድ ትዝ ያለኝን ነገር ልንገራችሁ፡፡ በፋሺስት ወረራ ጊዜ መጨረሻ ገደማ ነው አሉ፡፡ የእንግሊዝ ወታደሮች ከአርበኞቻችን ጋር እየተባበሩ ጣሊያንን ከኢትዮጵያ ምድር ያባርሩ በነበረበት ጊዜ ጎንደር አካባቢ ነው አሉ፡፡ ታዲያ አንዱ ሞቅ ያለው እንግሊዛዊ ወታደር የሕዝቡን ስሜት ለመፈተሽ ፈልጎ አጠገቡ ቆሞ ይመለከት የነበረውን ገበሬ ትክ ብሎ አየና "እንግሊዝ ጉድ፣ጣሊያን ጉድ?" ሲል ጠየቀው፡፡ ገበሬው ታዲያ እንግሊዙን ለማስደሰትና ነገር ያሳመረ መስሎት "ኧረግ! ጣሊያን? ከጉድም ጉድ! "አለው ይባላል፡፡ እንግሊዙ ተናዶ እንዴት እንዲህ ትላለህ ብሎ ሊተናኮለው ሲፈልግ በስንት የትርጁማን ገላጋይ ነው ነገሩ ወዲህ ነው ተብሎ ቁጣው የበረደው፡፡

ምናልባት የዛሬ 60 ዓመት ገደማና ከዚያ በፊት ዶሮ ከሃምሳ ሣንቲም አልፋ ብር በማውጣቷ ጉድ ተብሎ ሙሽሪት በግጥም መልክ ቅሬታዋን ገለጠች፡፡ ዛሬ ዶሮ 200 ብርና ከዚያም በላይ አውጥታለች፡፡ መጪው ፋሲካ ነው፡፡ ደርሶ አንበሳ የሆኑት የዶሮ ነጋዴዎች ከ200 ብር አልፈው ስንት እንደሚጠይቁ አይታወቅም፡፡

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ እናንሳ፡፡ በአንድ ዕቃ ላይ፤በተለይ ደግሞ የቅንጦት በሆነ ዕቃ ላይ ያልሆነ ዋጋ ሲጠየቅ ከአግባብነትና አላግባብነት ሁኔታ በመነሳት፣ በጋራም ሆነ በተናጠል "አይ! የቀረው ይቀራል እንጂ በዚህ ዋገማ አልገዛም/አንገዛም ማለት የለብንም? በሌሎች ንቃተህሊናቸው በዳበረ አገሮች በተደጋጋሚ እንደምንሰማው በዳቦ፣ በዘይት፣ በስኳር ወይም በነዳጅ በሣንቲም ደረጃ ዋጋ ተጨመረ ተብሎ፣ሕዝቡ ሠልፍ ይወጣል፡፡ ያለመግዛት አድማ ያካሂዳል (boycott) ያደርጋል፡፡ እኛ ታዲያ ምን አዚም ይዞን ነው ዓመት በዓል በመጣ ቁጥር አምጡ ያሉንን ኪሳችንን አራቁተን ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ዋጋ የምንከፍለው?

ለ200 ብርና ከዚያም በላይ ለሆነ ዋጋ የዳረገን ባህላችን ነው፤በዓመት በዓል የገብስማና የወርቅማ ዶሮ ደም የማፍሰስ ባህል የዶሮ ወጥ ዝግጅት ብዙ ጣጣ አለው፡፡ ጣጣው የባህሉ አካል ሆንዋል፡፡ «ይሸታል ዶሮ፤ ይሸታል ዶሮ ዶሮ የእማምዬ ጓሮ» አስብሎ የለ? የዶሮ ቀለሙ፣ ደሙ፣ ቁሌቱ፣ ሽታው፣ ጣዕሙ፣ ስሙ፣ሽርጉዱ፣ግርግሩ የባህሉ ባርያ አድርጎናል፡፡ ራሳችን ለራሳችን "እጅ ወደ ላይ!" ብለናል፡፡ አምጡ ያሉንን እየከፈልን ነው፡፡ የዶሮ ባህል "እምቢ‌ይ!" የማለት ወኔ አሳጥቶናል፡፡ ደህው በግ መግዛት አቅሜ በይፈቅድልኝም ዶሬዬን አርጄ ዓመትባሌን እንዳቅሜ አሳልፋለሁ» ይባል ነበር፡፡ ዶሮ የመጨረሻ ዝቅተኛ አቅም መግለጫ ነበረች ማለት ነው፡፡ ይህ አባባል ዱሮ ቀረ፡፡ ዛሬ የዶሮ ዋጋ የበግ ዋጋ ሆንዋል፡፡ የበግ ዋጋ የሠንጋ ዋጋ ሆንዋል፡፡ የሠነጋ ዋጋ ምን እንደሆነ ለመናገር አስቸጋሪ ሆንዋል፤ ሰማዩን ዘልቆ ሄዷልና፡፡

የባህል ጫናው ከቤተሰብ ይጀምራል፡፡ ቤታችን ዶሮ ሳይታረድ? የዓመትባል ደም ሳይፈስ!? ዓመትባል፣ዓመትባል ሳይሸት? ጎረቤት ምን ይላል? ይባላል:: የሚኖረው ለጎረቤት ይመስል፡፡

በአሁን ጊዜ በጎጂ ባህል ላይ ዘመቻ ተጀምሯል፡፡ የሴት ግርዛት፣ጠለፋ፣ግግ ማዉጣት ይወገድ፣ቅጥ ያጣ የሠርግ ድግስ አይሆንም እየተባለ ነው፡፡ ይወገድ የሚባሉትም አእምሮአዊ፣አካላዊና፣ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ያስከትላሉ ስለሚባሉ ነው፡፡ ጎጂ ባህሎችን ቀስ በቀስ እያስወገድን ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን አዳዲስ ጎጂ ባህሎችን እየፈጠርን ነው፡፡ ዶሮን በ200 ብርና ከዚያ በላይ መግዛት ጎጂ ባህል እየሆነ በመምጣት ላይ ነው፡፡ የአቅም ጉዳይም አይደለም፡፡ የአግባብነት ጉዳይ ነው፡፡ የመርህ ጉዳይ ነው፡፡ ታዲያ ለዚህ ዓይነት ችግር አንዱ መፍትሔ እምቢይ ማለት ነው፡፡ የባህል ባሪያ አልሆንም ማለት ነዉ፡፡ ሲረግጥ በእኔ አልደረሰም በሚል ዝም ማለት፣ለምን? አለማለት፤በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 30 በሚፈቅደው የመሰብሰብ፣ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቤቱታ የማቅረብ መብት በአምባገነንነት ሲገደብ መንግሥትን በተጠያቂነት አለመያዝ፣ባርነት ነው፡፡ ድንበር እየተሸራረፈ ለጎረቤት አገር ሲሰጥ፣የሃገር ለም መሬት ከዜጎች እየተነጠቀ በቆሎ ዋጋ በሊዝ ሲሰጥ፤ዜጎች አገር አለን፣በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 32 መሠረት በሀገሪቱ በየትኛዉ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት መብት አለን ብለው ከአንዱ የሃገራቸው ክፍል ወደ ሌላው እየሄዱ በሕጋዊ መንገድ መሬት አልምተው፣ንብረት አፍርተው፣ቤተሰብ መሥርተው፣ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ተዋልደው ሲኖሩ፣የአካባቢው ተወላጆች አይደላችሁም ተብለው እንደ ባእድ በመንግሥት ሹማምንት ሲባረሩ ዝም ማለት የመንግሥት ባሪያ መሆን ነው፡፡

ሕግ የዜጎች ከለላ፣የዜጎች አለኝታ በመሆን ፈንታ፣በተጣመመ መንገድ እየተተረጎመ የዜጎች ማጥቂያ መሣሪያ እየሆነ፣በዚህ ሥልት ንጹሃን ዜጎች ሲወነጀሉ፣ሲታሰሩ፣ጥለው ሲሰደዱ፣አገር እውነት ዜጎችን ነፃ የማታወጣበት አገር እየሆነች ስትሄድ እያዩ ዝም ማለት የመንግሥት ባሪያ መሆን ነው፡፡

ለማጠቃለል ከባርነት ለመውጣት የምናደርገው ትግል ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ጥሩ ነው ተብሎ የሚወሰድ ባህል ከጊዜ በኋላ ኢኮኖሚን የሚያቃውስና ጉዳትን የሚያስከትል እየሆነ ከመጣና ሊሻሻል የሚችልበት መንገድ ከጠፋ ባህሉን የመተው ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል፡፡ ዶሮ ወጥን ያክል ጣፋጭና በዙሪያው ያለው ባህል

ወደ 15 ዞሯል



# ድህነት እና ስራ አጥነት አፍላቂው ኢኮኖሚያችን በአመራር እጦት ችግር ውስጥ ነው

በወንድወሰን ፀጋዬ፡

በአሁኑ ጊዜ በየመንገዱ "የታክሲ አለሽ/አለህ" የሚሉ ወጣቶች መብዛቱ ሁላችንንም ግራ የሚያጋባ ነገር ነው፡፡ ሲለን እናዝናለን፤ ያለችንን እንሰጣለን ፤ ወይም ኪሳችን ሲቀዘቅዝ በምናየው እንናደዳለን፤ አንዳንዴ ልክ የዛን ቀን የገባን ይመስል - "ከምር እኮ እዚህ አገር ችግር አለ ፤ ወጣቱ ባይቸግረው አይለምንም" - ብለን ትልቅ ነገር ያረጋገጥን እስኪመስለን ድረስ አጥብቀን ከንፈር እንመጣለን፤ ይህ ችግሮችን በግልፅ አለመለየታችን ምክንያቱ ሁለት ነው፤ አንደኛው የመንግስት "እያደግን ነው፤ አገሪቱ ውስጥ ችግር የለም" የሚል ተራ ፕሮፓጋንዳ ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ በኛ በኩል ችግራችንን በደንብ ኖረነው ከመላመዳችን የተነሳ በቃ ልክ እንዳለንበት እንድንኖር የተፈረደብን ስለሚመስለን ነው፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ችግር ግን ለመረዳት ብዙ ማሰብ ብዙ መመራማር ሳያስፈልግ የኛን አኗኗር፤ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ድህነት፤በየአመቱ በምግብ ተረጂነት ኑሮቸውን የሚገፉ ሰዎችን በየከተሞች ቆሞ የሚታየውን የወጣት ስራ አጥ ብዛት፤ ስራ የፈቱ ቤተሰቦቻችንን ወይም ጎረቤቶቻችንን ማየቱ በቂ ነው፡፡

የኢትዮጳያ ማዕከላዊ ስታቲስቲክሰ ኤጀንሲ በ2003 ዓ.ም ባወጣው መረጃ መሰረት በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ በከተሞች ያለው የስራ አጥነት በመቶኛ 18 እንደሆነ ያሳያል፡፡ ድህነትም ከዛሬ አምስት አመት ከነበረበት 39% ወደ 29.6% ዝቅ እንዳለ የመንግስት መረጃዎች ያሳዩናል፡፡ እነዚህ ቁጥሮች አሁንም አገሪቱ ውስጥ አስከፊ ችግሮች እንዳሉ ቢያሳዩንም፤ ትልቁ ጥያቄ ግን እነዚህ መረጃዎች ምን ያህል ልክ ናቸው የሚለው ነው፤ ይህ በጣም አጠያያቂ ነው፡፡ ባጠቃላይ መረጃ አሰባሰቡ እና አተማመኑ ላይ ካሉት ችግሮች በተጨማሪ በአገሪቱ ውስጥ ያለው የመረጃ ምንጭ ድርጅት ነፃ አለመሆን አገሪቱ ውስጥ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃ ማግኘትን ከባድ አድርጎታል፡፡ (ይህን ችግር ከዚህ በፊትም በሕዝብ ቆጠራው ላይም ያ ሁሉ ህዝብ የት ገባ እስከሚያስብል ድረስ ታይቶል)፡፡ ባጠቃላይ እዚህ አገር ውስጥ በአሁኑ ሰአት መረጃዎች በገዢው ፖለቲካ ቅኝት እየተቃኙ ለፕሮፓጋንዳ እየዋሉ ነው ፡፡ ባጠቃላይ በዚህ አገር ያሉትን ችግሮች ለመረዳት መረጃዎች ከሚነግሩን በላይ በዚህ አስከፊ የዋጋ ንረት መሃል የምንኖርበትን ሁኔታ በማየት፡ አገሪቱ ውስጥ በትክክል የሚታየውን ድህነት እንዲሁም በአገሪቱ ትልልቅ ከተሞች አካባቢ እሁን አሁን በብዛት መንገድ ላይ ቆሞ የሚታየውን የወጣት ብዛት ተገንዝቦ የስራ አጥ ችግሩ እንዲሁም ድህነቱ በፖለቲካ እየተቃኙ ከሚቀርቡት መረጃዎች የባሰ አስከፊ መሆኑን ለማየት በቂ ነው፡፡

የድህነትና ሌሎችም ችግሮች በጥሩ መረጃ ካለመደገፋቸውም በላይ የነዚህን ችግሮች መንስዔዎች መንግስት ብዙ ጊዜ ከራሱ ጫንቃ ሲያወርድ ይታያል፡፡ ለምሳሌ የስራ አጥነት ችግር መንስዔው የወጣቱ ስራ ፈጥሮ ለመስራት ያለመፈለግ፤ እንዲሁም ሌሎች የስራ ባህሎችን እያጋነነ ስሎ የችግሩን መንስዔ ወደኛ ሲያላክክ ይታያል፡፡ እነዚህ ችግሮች የራሳቸው አስተዋፅኦ አያደርጉም ባይባልም፤ ዋነኛ ችግሮችን በትክክል መርምሮ ከማስቀመጥ ይልቅ አላስፈላጊ ነገሮች ላይ በማተኮር መንግስት እራሱን ከተጠያቂነት ሲያርቅ በተደጋጋሚ ይታያል፡፡ መሆን የነበረበት ግን አገሪቱ ውስጥ ድህነትና ስራ አጥነት በስፋት መኖሩን ማመን ነው፤ "ቀነሰ" በሚል ትክክለኛነቱ አጠራጣሪ በሆነ መረጃ ራስን ማታለል መንስኤውን ለይቶ ማከምን ከባድ ይደርጉታል፡፡ ባጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ድክመት ያለበት መሆኑ፤ አስከፊ ድህነትን መቅረፍና፤ አዲስ የስራ ዕድል መፍጠር የተሳነው አድርጎታል፡፡ የኢህአዴግ መንግስት የአገራችን ኢኮኖሚ በ 11 % እያደገ ነው ይበለን እንጂ ኢኮኖሚው ግን ኪስ የሚገባ ነገር ያልተፈጠረበት ነው፡፡ እድገቱ የት እንዳለ ግራ ያጋባል፡፡ በዚህች አገር እኛ የምናውቀው ኑሮ ባለንበት መርገጥ መሆኑን ነው፤ ለዚያውም በአስከፊ ድህንት ውስጥ ፤ ለብዙ ጊዜ አብሮን የቆየው ፀሎታችንም "የባሰ አታምጣ" ነው፡፡ (... የችግሩን መንስዔ መርምሮ ሁኔታዎችን ከመለወጥ ይልቅ ችግርን፤ረሀብን፤ቤት እጦትን፤ ስራ አጥነትን ተላምደን ለመኖር ስንጣጣር እንገኛለን)፡፡

## ብቃት እና ተጠያቂነት ያለው አመራር እጦት

የዚህ ሁሉ ችግራችን ዋናኛው ተጠያቂ - ምንም መሸፋፈን ሳያስፈልግ - አገሪቱ ብቁና ተጠያቂነት ያለው ትክክለኛ አመራር አለማግኘቷ ነው፡፡ ብቃት ያለው ትክክለኛ አመራር አለመኖር ኢኮኖሚው ማደግ ያለበትን ያህል እንዳያድግ አድርጎታል፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከግብርናው ጥገኝነት ተላቆ ወደ ኢንዱስትሪው ዘርፍ አተኩሮ መዋቅራዊ ለውጥ እንዳያመጣ አግቶታል፡፡ ከሁሉም በላይ አሁን የሚያነጋግረንን ድህነትና ስራ አጥነትን መቅረፍ የሚችል ፤ ስራ የመፍጠር አቅም ያለው ኢኮኖሚያዊ ልማትን ማሳካት አልተቻለም፡፡ ይህ በተለይ በሁለት ዋና ድክመቶች ላይ ያተኩራል፡፡ አንደኛው እና ዋናው የፖሊሲ ቀረፃ ላይ ያለ ችግር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአተገባበር ችግር ነው፡፡ አሁን ያለው የኢሕአዴግ መንግስት ለባለፉት 20 አመታት በሁለቱም በኩል ታላቅ የሚባል ውድቀቶችን አስምዝግቧል፡፡

የመንግስት የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ፖሊሲ - የኢሕአዴግ መንግስት ሲከተለው የከረመው አሁንም በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ውስጥ እንደዋና ፖሊሲ የሚከተለው የግብርና መር ፖሊሲ ነው ፡፡ ይህ ፖሊሲ ሲቀረፅ ታልሞለት የነበረውን የግብርናውን ዘርፍ አሳድጎ ከግብርናው የሚገኘው እድገት ወይም ገቢ የኢንዱስተሪውን ዘርፍ እድገት እንዲያነቃቃ የነበረ ሲሆን፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግብርናውም ማደግ የነበረበትን ያህል ሊያድግ ሳይችል የኢንዱስትሪውም እድገት ሳይነቃቃ፤ የታሰበውም መዋቅራዊ ለውጥ ሳይመጣ ይህው ከነችግራችንና ከነድህነታችን 20 ዓመታት አስቆጠርን፡፡ የሚገርመው መንግስት ግብርናው በማደግ ላይ ነው፤ ሀብታም ገበሬዎች እያፈራን ነው፤ ይበል እንጂ የሰብሎች ምርታማነት አሁንም በጣም ዝቅተኛ ነው፤ በመስኖ የሚለማ መሬት

ወደ 14 ዞሯል

ፍኖተ -ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ። ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሥር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር የፓርቲው ጋዜጣ ነው።

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል። የማንኛዉም ሰዉ ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን። ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማቅረብ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤ.ቁ 028

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ብስራት ወ/ሚካኤል

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መሥፍን

አምደኞች፡- ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ወንድሙ ኢብሳ
አንዱዓለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ቀለሙ ሁነኛው
በለጠ ጎሹ

ኮምፒውተር ጽሑፍ፡-
የሺ ሃብቴ
ብርቱካን መንገሻ

ህትመት ክትትል፡-
አያክሉህም ጀንበሩ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ

አሣታሚው፡-
አንድነት ለዴሞክሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ.ቁ አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07 የቤ.ቁ 984

የዝግጅት ክፍሉ
ስልክ +251 118-44 08 40
+251 922 11 17 62
+251 926 81 46 81
+251 913 05 69 42
+251 923 11 93 74

ፖ.ሳ.ቁ፡ 4222

ኢሜይል፡- fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር፡- +251-111226288

# ርዕሰ አንቀፅ

## ነፃ አስተየት




# የሰላማዊ ትግሉን አንድ ርከን ከፍ ማድረግ የወቅቱ ጥያቄ ነው!

የደርግ አገዛዝ ተወግዶ፣ ህገ-መንግስታዊ አሰራርና መደብለ ፓርቲን የምር የተቀበለ ሥርዓት ይመሰረታል የሚል የብዙ ኢትዮጵያውያን ምኞትና ተስፋ ነበር፡፡ ኢትዮጵውያን ለአንዴና ለመጨረሺያ ጊዜ ከጥላቻ ፖለቲካና ከመገዳደል ወጥተን፣ በሃሳብ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ሥልጡን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ የነበረው ተስፋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደበዘዘ መምጣቱ ግልፅ ነው፡፡ በትግሉ ሂደት፣ ቀላል የማይባሉ ወገኖች የሰለማዊን መስመር በመልቀቅ ወደ ሁሉን አቀፍ አማራጭ መሄዳቸው አንዱ ማሳያ ነው፡፡

አገዛዙ በሂደት ልቦና ይገዛል ብሎ መጠበቅ የዋህነት እንደሆነ በግልጽ ይታያል፡፡ ከሁሉ በላይ ለሀገራዊ መግባባትና ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ ያለው እብሪትና ንቀት የሚያስተዛዝብ ነው፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ አንድነት/መድረክና ሌሎች ሀቀኛ ተቃዋሚዎች ከኢህአዲግ ከጦርነት ያለተናነሰ ዘመቻ እየተደረገባቸው ይገኛል፡፡ የደንህነት ተቋሙ፣ የሀገርን ጥቅም በሚየስጠብቅ ስራ ላይ ከመጠመድ ይልቅ በየፓርቲዎች ቢሮዎች አከባቢ ተበትነው እንደ ስራ ፈት ተገትረው የሚውሉበት ሁኔታ የቀን ተቀን ትይንት ነው፡፡ ስራቸው የአመራሮችን ስልክ በመጥልፍ ማን ምን አወራ በሚል የተጠመዱ ናቸው፡፡

በህግ እውቅና አግኝተው፣ በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ከህዝብ ጋር ተቀራርበው እንዳይወያዩ ያለ መሰናከል አጅግ አሳሳቢ ነው፡፡ አንድነት/መድረክ የህዝባዊ ስብሰባና የወቅታዊ ውይይቶች አዘጋጅ ንዑስ ኮሚቴ፣ ባለፉት ሶስት ወራት ተከታታይ ህዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ ቢንቀሳቀስም፣ አዳራሽ ለማግኘት አልተቻለም፡፡

በቅርቡ የሙገር ሲሚንቶ ሠራተኞች ማህበር የድርጅቱን አደራሽ ለመድረክ ካከራየ በኋላ፣ መልሶ ሃሰብን መቀየሩን የህግ የበላይነትና ተጠያቂነት የሚባል ነገር ፈጽሞ የሌለ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህ ሆን ተብሎ ተቃዋሚዎችን ከህዝብ ጋር ተገናኝቶ እንዳይወያይ የሚደረግ እኩይ ተግባር፣ ሰላማዊ ትግሉን እያሽመደመደው ይገኛል፡፡

አገዛዙ እየተከተለው ያለው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከጽህፈት ቤታቸው ውጭ ምንም ዓይነት የፖለቲካ እንቅስቀሴ እንዳያደርጉ የሚከለክል አሰራር፣ ህገ-መንግቱን የሚጥስ ተግባር ነው፡፡ ግን እስከመቼ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ተጣሱ እየተባለ ሲጮሆ ይኖራል? እስከ መቼ አንቀጽ እያጠቀሱ በጋዜጣዊ መግለጫ ተገድቦ መኖር ይቻላል? መሠረታዊ የመደራጀትና የመሰብሰብ መብት በግልጽ ከተናደ፣ በህጋዊ ፓርቲ ተመዝግበን እየሠራን ነው በሚሉትና በህቡ እየሰሩ ነው ከሚባሉ ፓርቲዎች መካከል ያለው ልዩነቱ ምኑ ላይ ነው?

በዚህ ሁሉ አጣብቅኝ ውስጥ ያለው ሰላማዊ ትግል ስኬታማ ለማድረግ በአንድነት በኩል እየተደረገው ያለው ጥረት መልካም ነው፡፡ ግን "ሳይሰለቹ ደጋግሞ መሞከር" የሚባለው መርህ እስከመቼ የሚቀጥል ነው?

ይህ በእንዲህ እንዳለ በህወሓት/ኢህአዴግ በኩል ታማኝ ለሆኑ "ተቃዋሚዎች" እየተደረገ ያለው የገንዘብ ድጋፍ ዓላማው ግልጽ ነው፡፡ በእጅ አዙር መድረክና መሰል ድርጅቶችን ለማዳከም መውተርተር ነው፡፡ እንዚህ ፓርቲዎች ግን ማን እንደሆኑ ህዝቡ በደንብ አድርጎ ያውቃቸዋል፡፡ ኢህአዴግ በዓለም ላይ ገዥው ፓርቲ ለተቃዎሚዎች ብር የሚሰጥበት ሃገር ልምድ ካለ ቢነግረን መልካም ነው፡፡

ሰላማዊ ትግልን ከገባበት የውድቀት አዙሪት አውጥቶ ለድል ለማብቃት ከፍተኛ ስራ መሰራት እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ ብዙ ያልተሞከሩ ስራዎች አንዳሉ እሙን ነው፡፡ አንደኛው አማራጭ ምንም እንኳን ፍርድ ቤቶች የነጻነት ችግር ቢኖርባቸውም ህገ መንግስቱን በግልጽ የሚጥሱ አካላት ላይ በአቋም መግለጫ ብቻ ሳይሆን በህግ መጠየቅ አስፈላጊ ሆኖ ይታያል፡፡ በሂደቱም ፍርድ ቤቶችን ይበልጥ ለመፈተሽ ተጨማሪ አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡

በተጨማሪም የቤት ለቤት ቅስቀሳና በየሜዳው ሕዝብን የማወያየት ስራ በፋጣኝ መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ከተለመደው ህዝብ የማግኛ ዘዴዎች ውጭ ማቀድና መንቀሳቀስ የግድ ይላል፡፡

ይህ ማለት ተቃዋሚዎች ችግር የለባቸውም ማለት አይደለም፡፡ በአንድነት ፓርቲ በኩል ለዚህ የሚመጥን ስትራቴጂና ታክቲክ መንደፉ እንደ አንድ እምርታ የሚታይ ነው፡፡ ይህን ስታራቴጂ ለማስፈጸም የምችል የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም መፍጠር ግን ወሳኝ የትግሉ ምዕራፍ ነው፡፡

ተቃዋሚ ጎራ የሚታየው መሠረታዊ ችግሮች መቀበል ይጠበቅበታል፡፡ አንድነት እንደ ፓርቲ፣ ትግሉ ያለበትን መሠረታዊ ችግር በግልጽ ለይቶ እየተንቀሳቀሰ መገኘቱ የሚያበረታታ ነው፡፡ አንድነት ያለፉ ሶስት ዓመት ተኩል የሄደበትን አቅጣጫ በጥልቀት መገምገሙ እንደመልካም ጅምር የሚታይ ነው፡፡

አንድነት ከዚህም ይበልጥ ፖለቲካውን ለማዛመን የሚደረገው ጥረት አጠናክሮ ሊቀጥልበት ይገባል፡፡ በተለይ በሶስት ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ይበልጥ ጠንክሮ ሊሰራ ይገባዋል፤ የፓርቲውን አቅም የማጠናከር ስራዎች፣ ከሌሎች ሀቀኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ወይም በመዋሃድ መስራት፣ ግልፅ የሆነ አማራጭ ፖሊሲዎችን ማስቀመጥ አንገብጋቢ የወቅቱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

የፓርቲውን አቅም ጥራት ባለው የሰው ኃይል የመገንባቱ ሂደት ተጠናክሮ ሊኬድበት ይገባል፡፡ በፓርቲው ብቃት ያለው የሰው ኃይል ወደ ትግሉ እንዲገቡ የማድረግ ስራ አንደወሳኝ ስራ ተቆጥሮ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ፓርቲውን በቁሳቁስና በፋይናንስ የማጠናከር ስራም ለነገ የሚተው ስራ አይደለም፡፡

አሁን በሀገራችን ያለውን የፖለቲካ ችግር በተናጥል ሳይሆን በጋራ ወደ ፊት መግፋት አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ አንድነት ተቀብሎታል፡፡ የመድረክን ወደ ግንባርነት የማሸጋገር ጉዳይ በተሻለ ቅልጥፍና ለማጠናቀቅ መስራት አንዱ ጉዳይ ሆኖ፣ አንድነት የጀመረውን ከሌሎች ሀቀኛ ተቋዋሚዎች ጋር የሚደረጉ ድርድሮችን በቅንነትና በሆደ ሰፊነት የተሳካ እንዲሆኑ ቀን ከሌሊት መስራት ወሳኝ ነው፡፡ ያለፉ የቅንጅትና የውደት ልምዶችን በመቀመርና የነበሩ የእርስ በእርስ አለመተማመኖችን አስወግዶ፣ የተሻለ የትብብር መድረክ ለመፍጠር መታገል የግድ ይላል፡፡

አሁኑ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የትግል ምዕራፍ ከአይዶሎጂ አቋም በላይ ነው፡፡ የትግሉ ቁልፍ ጥያቄ የነጻነትና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዥታ የለም፡፡

ይሁን እንጅ እንደ አንድነት ያለ በሰላማዊ ትግል የሚያምን ፓርቲ፣ ግልጽ የሆነ ዝርዝር አማራጭ ፖሊሲ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ትግሉ በስሜትና በጥላጫ ላይ የተመሠረተ እንዳይሆን መስራት ያስፈልጋል፡፡ ትግሉን በሃሳብ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአንድነት ፓርቲ በኩል የፖሊሲ ቀረጻ አንጻር የተጀመሩ ስራዎች ቢኖሩም፣ በተሻለ ፍጥነት መጨረስ ያስፈልጋል፡፡

በሀገራችን በአሁኑ ወቅት ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት በተጨባጭ አለ ማለት የማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል ማለት ይቻላል፡፡ አገዛዙ ስራው ሁሉ ተቃዋሚዎችንና ነጻ ሚዲያዎችን ማዋረድና ማንኳሰስ ሆኗል፡፡ ተቋዋሚዎች ልክ እንደማርያም ጠላት በሄዱበት ሁሉ፣ መብታቸውንና ክብራቸውን ለመግፈፍ መስራት የአገዛዙ መለያ ሆናል፡፡

ይህ ማለት ግን እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ አለብን ማለት አይደለም፡፡ የህዝቡ ልብ ውስጥ ለመስፈር ማንኛውንም ዓይነት መሰዋትነት ለመክፈል መንቀሰቀስ ያስፈልጋል፡፡ ለዚሁ ተፈጻሚነት የአመራሩ ሚና ቁልፍ ነው፡፡ ትግሉ ከተከላካይነት አውጥቶ ወደ አጥቂነት ማሸጋገር ግድ ይላል፡፡


ኢህአዴግ ከቅርጽ አንጻር ካለሆነ በቀር፣ በይዘት ከደረግ ጋር አንድ መሆናቸውን በተለያዩ ጊዜያት አስመስክሯል፡፡ ከአቶ መለስ አገዛዝ እውነተኛ መድበለ ሥርዓት መጠበቅ በፍጹም አይቻልም፡፡ የኢህአዴግ አቋም ግልጽ ነው፡፡ "ተቃዋሚዎች እግር እስኪያወጡ ድረስ እንጠብቃቸዋለን፣ እግር ሲያወጡ እንቆርጣቸዋለን" ነው፡፡ የሰላማዊ ታጋዮችን መታሰር ምክንያቱ ይሄው ነው፡፡

የአገዛዙ የቁልቁለት ጉዞ ማቆሚያ የሚገኝለትም አይመስልም፡፡ አገዛዙ በህዝብ ያለው ቅቡልነት በየጊዜው እየወረደ እየወረደ መጥቶ፣ በአባይ ግድብ ዙሪያ የተገደበ ሆኗል፡፡ አገዛዙ የያዘውን ስልጣን ከማስጠበቅ አንጻር ብቻ የሚያይ ሆኗል፡፡

ትግሉን ለድል ለማብቃት በቆራጥነትና በፅናት እንታገል፡፡ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መፈጠር መስዋዓትነት ለመክፈል የሚታገሉና እየከፈሉ የሚገኙ ክብር ይገባቸዋል፡፡

ጋዜጣችን "ፍኖተ-ነፃነት" ብለናታል፡፡ "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር "የነፃነት መንገድ" ማለት ነው!!

# ይድረስ ለተከበራችሁ ጠቅላዮች



ከተድላ ተሰማ (ዶ/ር)

ይህችን አጭር መልዕክት ለጠቅላዮች ማለትም ለክቡር የኤፌዴሪ ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ እና ለክቡር የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚ/ር እና የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ለማስተላለፍ ስታዘብ የወሰደብኝ ጊዜ አጭር የማይባል ቢሆንም በዚሁ ጋዜጣ ማክሰኞ መጋቢት 18 ቀን 2004 ዓ.ም. ዕትም ላይ በገጽ 13 እና 15 ላይ መ/ር ቀለሙ ሁነኛው የተባሉ ግለሰብ ያሰፈሩት ጽሑፍ ርዕሰ ጉዳዩ "ይድረስ ለአቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚ/ር እና የውጭ ጉዳይ ሚ/ር" የሚል ሲሆን አምዱ በውስጡ ብዙ ሀሳቦችን ያዘለ ቢሆንም ለአንባቢው ጎላ ብለው ከሚታዩ ነጥቦች አንዱና አብረን እንድንመለከት የፈለኩት "ታዳጊ ሕጻናት ከወላይታ ወደ መዲናችን አዲስ አበባ በመሰደድ በለጋነታቸው የሕይወትን መራራ ጽዋ እየተጎነጩ መሆናቸውን ከመግለጻቸውም ባሻገር የእነዚህ ሕጻናት ሕይወት መቅበዝበዝ ነገ የብሔረሰቡን ህልውና ፣ስምና ዝናን በማበላሸት የታሪክ ማፈሪያ እንዳይሆኑ" ሲሉ ስጋታቸውን እንዲህ ይገልጹታል፡፡ "ለተወደዳችሁ የወላይታ ብሔረሰብ ተወላጆች! አኩሪ ታሪክ ያላችሁ ህዝብ ናችሁ፡፡ ቅቤና ማር የምታፈልቅ ለም መሬት ላይ የሰፈራችሁ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች! ከሁሉም በላይ እንግዳ ተቀባይነታችሁና በፍቅር አብሮ የመኖር ባህላችሁ እጅጉን የሚያስደንቅ ነው፡፡ ሙዚቃችሁና ዳንኪራችሁ በአገራችን ቁጥር አንድ ተወዳጅ ነው፡፡ ተወዳጁ ንጉስ ጦናም የኢትዮጵያ ታሪክ አንድ አካል ነው፡፡

ዛሬ የአብራካችሁ ክፋዮች በተለይም የወላጆቻቸውን ፍቅር ያላጣጣሙ ህጻናት በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ላይ ሎተሪ እያዞሩ ሲጎሳቆሉ ስናያቸው አይኖቻችን እንባ ያጤዛሉ፡፡ አንጀታችን በሀዘን ይላወሳል፡፡ ስለዚህ ኩሩ ታሪክ ያለው የወላይታ ህዝብ የታሪክ ማፈሪያ እንዳይሆን ይህን ፍልሰት ለማቆም ርብርብ እንዲያደርግ እማጸናለሁ፡፡" ይህን ጊዜ ነበር እስክሪብቶዬን አንስቼ ከወረቀት በማገናኘት ብቻዬን ሳስብና ሳውጠነጥን የቆየሁትን የእነዚህን ሕጻናት ድምጽ አልባ ጩኸት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አመራሮች ለመግለጽ የወደድኩት፡፡

በእኔ እይታ ለእነዚህ ታዳጊ ህጻናት መሰደድ እና መቅበዝበዝ ዋነኞቹ ምክንያቶች ናቸው ብዬ ከምላቸው፡-

የወላይታ ሕዝብ በሰፊ የመሬት ይዞታ ላይ ያለመስፈሩ፣ በአሁኑ ወቅት ከዞኑ ሕዝብ አምሳ ከመቶ እጅ (50%) በላይ ቁጥር ያላቸው ለስራ ያልደረሱ ነገር ግን ለምግብ ያላነሱ በሚባል የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚመደቡ ሕጻናት መሆናቸው፣ አምራች የሰው ሀይል ቁጥር ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረጉ፤ በፈጣን ዕድገት እየጨመረ የመጣው የዞኑ የሕዝብ ቁጥር በዞኑ ከተሞች ሆነ ገጠሩ ሰፋሪዎች ላይ ከፍተኛ የመሬት ጥግግት ማስከተሉ ለእርሻ መሬት ጥበት መዘዝ አይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው በዞኑ ዋና ከተማ ሶዶ ላይ የሚገኘው ግዙፉ ዳሞታ ተራራ በአሁኑ ወቅት እየታረሰ ለእርሻ፣ለቤት ግንባታና ለመሰል ተግባራት እየዋለ ይገኛል፡፡ ይህ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ያስከተለው ከፍተኛ የመሬት ጥግግት ለአርሶ አደሩ የእርሻ መሬት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ማድረጉ እና መሰል ጉዳዮች ሲገኙበት ይህን ችግር አስመልክቶ የወላይታ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ወሕዴግ) በመግለጫው እንደገለጸው የዞኑ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና ተፈጥሯዊ የአየር ጸባይ ለእርሻም ሆነ ለኢንዱስትሪ ምርታማነት ምቹ ቢሆንም የእርሻ መሬት ስፋት በፈጣን እድገት ላይ ካለው የህዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር በቂ አለመሆኑን አስመልክቶ የወላይታ ኢኮኖሚያዊ መዋቅር በአፋጣኝ ከግብርና ተላቆ ወደ ኢንዱስትሪ ማዕከልነት መቀየር እንዳለበት መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም. በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ አሰነብበውናል፡፡

ስለዚህ መንግስትና ባለ ድርሻ አካላት የዚህን ሕዝብ ችግር ተረድቶ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ካልቻሉ ዋነኛ እንጀራቸው እየሆነ የመጣውን ትምህርታቸውን ጥለው የሚሰደዱ ሕጻናት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመጨመሩ ባሻገር በመዲናችን ጎዳናዎች ላይ እንደምንመለከታቸው ከሰው ተራ ወጥተው ሊኖሩ ይገደዳሉ፡፡ ነገሩን ደግሞ በጣም የከፋ የሚያደርገው ከቀዬአቸው ተሰደው ከመጡበት ከተማ በልተው ማደር አለመቻላቸው ነው፡፡ ይህን ጊዜ ነው ራባቸውን ለማስታገስ ሲሉ ከማይገባበት የሚገቡት፣ የማይነካ የሚነኩት፤ብሎም ሕዝብን ወደ መድላት የሚመጡት፡፡

ስለዚህ በእውነት ጠቅላዮቻችን የእነዚህን ሕጻናት ስደት አስከፊ ገጽታ አይተውት ይሆን? በእርግጥ እንደሚመስለኝ ስደቱ እንዳለ ካወቅን የነገሩን ክብደት ማሰቡ ከባድ አይመስለኝም፡፡ የከበደን ለችግሩ መፍትሔ መስጠቱ ነው የሚመስለኝ፡፡ ለዚህ ነው የእነዚህን ሕጻናት ድምጽ አልባ ጩኸት ለጠቅላዮቻችን እንዲደርሳቸው የወደድኩት፡፡ ክቡር ምክትል ጠቅላዩ ከዚያው ቀበሌ እንደመሆናቸው መጠን የነገሩ አሳሳቢነትና አስከፊነት ከማንም በላይ ቶሎ ይገባቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ ክቡር ዋና ጠቅላዩም እንደ በላይ የሀገር መሪነታቸው የነገሩን ክብደትና በብሔረሰቡ ሆነ በመዲናችን ብሎም በአገራችን ሊያስከትል የሚችለውን አስከፊ ገጽታ ተገንዝበው የነገ ሀገር ተረካቢ ሕጽናቱን ድምጽ በማድመጥ የብሔረሰቡን ህልውና እንዲጠብቁልን አጥብቄ በአክብሮት እማጸናለሁ፡፡

መ/ሩ እንደገለጹት የእነዚህን ስደተኞች ጩኸት በትክክል ያደመጡ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም በወላይታ ምድር ተወልዶ የወላይታን ቅቤ፣ ማርና ጮማ ሳይመገቡ ብሎም የሚወዱትን ትምህርታቸውን ጥለው ተሰደው ሀይ የሚላቸው በሌለበት ከተማ ጎዳና ላይ ውሎ ማደር ምንኛ መበደል ነው?

እንደሚታወቀው የወላይታ ህዝብ ትምህርትን ቀዳሚና ቀዳሚ አላማው አድርጎ ከያዘ ረጅም ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን በዞኑ ካለው ከተማሪ የሰው ሀይል ብዛት በተጨማሪ በአገራችን አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ሲቋቋሙ ለወላይታም ዕድል መሰጠቱ ይታወቃል፡፡ ይህ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ሊገነባ ሲታቀድ ከአንዳንድ ግለሰቦች ለተነሳው ተቃውሞ የተሰጠው ምላሽ «ንብ ባለበት ቀፎ ይሰቀላል» የተባለለት የወላይታ ሕዝብ የትምህርትን ጥቅም በትክክል የተረዳ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁን አሁን የምንሰማውና የምናየው ለወላይታ እንዲሁም ለአገራችን ኢትዮጵያ ፈታኝ እና የዕድገት ማነቆ እንዳይሆን ስጋቱ አለኝ፡፡ የስጋቴ መነሻ የሆነው ባለፈው የካቲት 3 ቀን 2004 ዓ.ም የወላይታ ልማት ማህበር (ወልማ) አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ምክር ቤት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ከአቀረባቸው አጀንዳዎች አስደንጋጭና አሳዛኝ ሆኖ ያገኘሁት በዞኑ እ.ኢ.ኤ 2001 የትምህርት ዘመን ተመዝግበው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ከነበሩት ተማሪዎች ወደ 21,000 (ሀያ አንድ ሺህ) ገደማ የሚጠጉ ተማሪዎች ከት/ት ገበታቸው እንደተፈናቀሉ አሰምተውናል፡፡ ምን ያህል የሚዘገንን ዜና ነው? እነዚህ ከት/ት ገበታቸው የተፈናቀሉ ተማሪዎችስ የት ነው የገቡት? በየአመቱ የዚህን ያህል ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ከት/ት ገበታቸው የሚፈናቀሉ ከሆነ ከሁለትና ሶስት አስርት አመታት በኋላ የብሔረሰቡ እጣ ፋንታቸው ምን ይሆናል? በእርግጥ ጠቅላዮቻችን ይህን ታውቃላችሁ? ለመሆኑ በመዲናችን ጎደናዎች ላይ ተጎሳቁለው የሚበላ አጥተው የሚንከራተቱ ሕጻናት የወላይታ ብሔረሰብ ተወላጆች ብቻ ናቸው? ወይስ የሌሎች ብሔር ተወላጆች ጭምር? እስቲ ወደ ራሳችን እንመልከት፡፡ እያንዳንዳችን በግልም ሆነ በጋራ በብሔር ደረጃ የነዚህን ጨቅላ፣የነገ ሀገር ተረካቢ ሕጻናት ስደትን ለመግታት ምን አስተዋጽኦ አበረከትን? ስለዚህ ይህን ፍልሰት ለመግታት በተለይም የብሔሩ አስተዳደሮች እና የክልሉ መንግስት አፋጣኝ ርምጃ ካልወሰዱ ነገ የተማረችና የተዋበች ሀገር መጠበቁ የዋህነት ይሆናል፡፡ ይህን በመረዳት የሚመለከተው አካል ሁሉ ስለሚሰጣቸው አፋጣኝ ምላሽ ከወዲሁ እያመሰገንኩ የብሔር ብሔረሰቦችን ነጻነት፣ እኩልነት እና ጥቅምን ለማክበር ሆነ ለማስከበር፤ መቻቻልንና መደጋገፍን ባሕላችን ለማድረግ፤ ድህነትን እና ኋላ ቀርነትን ፈጽሞ ለማስወገድ ከወትሮ ተግተን እንስራ እላለሁ፡፡ ቸር ይግጠመን ፡፡

# በአማራ ሕዝብ ላይ የተከፈተው ዘመቻና የብአዴን ዝምታ



ዳንኤል ተፈራ

አንድ ስልክ ተደወለልኝ፡፡ ቁጥሩ ላይ አፍጥጬ ለማንሳት ዘገየሁ፡፡ ቢሆንም አነሳሁት፡፡ ከወዲያኛው ጫፍ በጭንቀት የታፈነ የሚመስል ድምፅ "ሄሎ! . . ." አለኝ፡፡ ማን ልበል? ከየት ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን አስከተልኩ፡፡ "ከጋምቤላ ነው፡፡ የአማራ ብሔር ተወላጅ ነኝ" ካለኝ በኋላ የእኔን ምንም አይነት ምላሽ ሳይጠብቅ ጥያቄዎችን ማዥጐድጐድ ጀመረ፡፡ "እንዴት አይነት በደል ነው የሚፈፀመው? ምን አይነት ግፍ ነው እየተሰራብን ያለው? ለማን ነው አቤት የሚባለው? ሀገራችንስ የት ነው? ኢትዮጵያ እስከየት ድረስ ናት? እንዴት አንድ ህዝብ ያውም ባገሩ ሀብትና ንብረቱን ተቀምቶ፤ ካለማው ማሳ እና ከከብቶች ነጥለው እንደ ምናምንቴ ወጣ ይሉታል? እኛስ ነገ ያለን ዋስትና ምንድን ነው? ዥጉርጉሩና ሰብጥሩ የኢትዮጵያ ህዝብስ ዋስትና ምንድን ነው? የአንድነታችንን ገመድ ክር ነው እየበጠሱት ያለው፡፡ ለምን እንደደወልኩልህ ታውቃለህ? ይሄንን እርር ድብን ያደረገኝን ክፉ ድርጊት ብትፅፍልኝ ብየ ነው፡፡ ከጭንቀቱ የተገላገልኩ መስሎኝ ነው፡፡ በሀገራቸው ላይ ስደተኛ እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ዜጐች መጠጊያ ፍለጋ ወደ ጋምቤላ ሲጐርፉ አይቼ ነው፡፡ መንግሥት ባለበት ሀገር እንዴት! . . . እንዴት የመኖር ዋስትናህን ታጣለህ፤ መንግስት በሚባል አካል ትዕዛዝ እንዴት "ወደ ሀገርህ ውጣ!" ትባላለህ? ይሄ ደባ ነው፡፡ የአማራ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ደባ፡፡ ዘመቻ ነው የተከፈተው ሰምተሃል? . . ." የደወለልኝ ድምፅ እየተቆራረጠ ሄደ፡፡ ወደ ለቅሶ ሲቀየር ሰማሁት፡፡ የማፅናኛ ዕድል እንኳ ሳላገኝ ስልኩ ተቋረጠ፡፡ መልሽ ለማግኘት ያደረግሁት መከራም የተሳካ አልነበረም፡፡

የጋምቤላው ደዋይ ለጭንቀት ሰጥቶኝ ጠፋ፡፡ እውነት ግን መንግሥት የሚባለው አካል ዋስትና ካልሰጠን፤ በሀገራችን ላይ ሃብት የማፍራትና የመኖር መብታችን ጥያቄ ምልክት ውስጥ ከገባ አቤት የሚባለው ለማን ነው? እያልኩ ሌሎች ጥያቄዎችንም አከልኩ፡፡

የጋምቤላው ደዋይ ያነሳቸው ጥያቄዎች መመለስ የሚገባቸው ብሔርተኝነትን የሚያበረታታውንና ቋንቋን መሠረት ያደረገውን ፌደራሊዝም ያረቀቁትና ያፀደቁት አቶ መለስና ፓርቲያቸው ናቸው፡፡ አቶ መለስ እነዚህ በግፍ ሃብትና ንብረታቸውን ተቀምተው በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ የተባረሩ ለፍቶ አደሮች ጽ/ቤታቸው ድረስ በመሄድ እንዲታደጓቸው ቢማፀኑም መልስ አልሰጧቸውም፡፡ ይልቁንም በመኪና ተጠርዘው በአስቸኳይ ከአካባቢያቸው ገለል እንዲሉላቸው ተደረገ፡፡ ይሄንን ለማስፈፀም ደግሞ በአማራ ሕዝብ ስም የተደራጀው ብአዴን ከፍተኛውን ሚና ተጫወተ፡፡ ይሄ ድርጅት እንደ ድርጅት ኃላፊነቱን ያልተወጣና የዜጐችን ተዘዋውሮ መኖር፣ ሀብት ማፍራት መብት የሚያከብር እንዴውም የዜጐች ተዘዋውሮ መኖርና ሀብት ማፍራት መብት የማያከብር፣ እንዴውም የዜጐች መብት ሲገፈፍ ከበሮ የሚደልቅ ድርጅት ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ብአዴን ሀላፊነቱን በአግባቡ አልተወጣም ማለት ይቻላል፡፡ እነ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ሕገ-መንግስቱንና የኢትዮጵያውያንን የመዘዋወር መብት የሚገድብ ሕግ አውጥተው ይሄንኑ ሰብዓዊ መብት የሚደፈጥጥ ህጋቸውን በዘመቻ መልክ በተለይ በአማራ ህዝብ ላይ ሲከፍቱ ብአዴን በማውገዝ ፈንታ በአስፈፃሚነት መሠለፉ ታሪካዊ ተጠያቂነት እንዲወድቅበት ያደርጋል፡፡ መጠየቅም ይኖርበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ገዥው ፓርቲ ብሔርን መሠረት ያደረገ ፖለቲካ ያራምዳል የሚል ትችት ሲመጣበት የሚመልሰው መልስ አጭር ነው፡፡ "የኢትዮጵያ የብሔር ብሄረሰቦችን መብት የማያከብሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች እንዲህ ይላሉ" የሚል፡፡ ይሄ ግን ሆድ የሚሞላ መልስ አይደለም፡፡ የፖለቲካ ጨዋታ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙም አንድም ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጨካክኖ አያውቅም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ተከባባሪ ነው፡፡ ይሄንን የመከባበር ባህሉን ግን ገዥዎች የፈጠሩለት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ተዋልዶና ተዛምዶ የኖረ ስብጥር ህዝብ ነው፡፡ ይሄን ህዝብ ነው እንደወንፊት አንጠርጥሮ ለመለያየት የተፈለገው፡፡

የጉራፈርዳ ወረዳ ኗሪዎች ሃገሬ ብለው ወደ ደቡብ ያመሩ ኢትዮጵያውያንን እቅፍ ድግፍ አድርገው ተቀበሏቸው እንጅ እንደ እነ አቶ ሽፈራው ዘር ቆጥረው ወዳገራችሁ አላሉም፡፡ "ወደገራችሁ!" የኢትዮጵያ ህዝብ የአንድነት ገመድ ላይ የተቃጣ አደገኛ ምላጭ ነው፡፡ በቤንች ማጂ በጉራፈርዳ የሚኖሩት የሚኒጥ ብሔረሰቦች ወንድሞቻቸው የሆኑ የአማራ ተወላጆችን አብረው ያለሙ ዘንድ ጋበዘዋቸው ነበርና ለእነዚህ ወንድሞቻቸው በህጋዊ መንገድ መሬት ሰጥተው የአብሮ መኖርና የአብሮ ማደግ ጥሪ አስተላለፉላቸው፡፡ ድምፃቸው ሳይሰማም በፍቅር ኖሩ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ መገለጫም ይሄው ነው፡፡ አብሮነት፡፡ መሬት አምላክ በጊያዜዊነት እንቆይባት ዘንድ የተሰጠችን የጋራ ሀብት ናት፡፡

እነ አቶ ሽፈራውና የሚመሩት መንግስት፤ እንዲሁም ቋንቋን መሠረት ያደረገውን ፌደራሊዝም እንዳገኙ የጨለጡ ካድሬዎቻቸው የህዝቦች በአንድ ላይ መኖር፣ መተሳሰብና ፍቅር እረፍት የነሳቸው ይመስላል፡፡ በሚኒጥ ብሔረሰቦችና በአማራ ተወላጆች መካከል ያለው መግባባት እንቅልፍ የነሳቸው ሆኗል፡፡ እናም በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ደብዳቤ መሪነትና በካድሬው አስፈፃሚነት "ወደገራችሁ!" የሚል የተበላሸ መፈክር ይዘው ጉራፈርዳ ወረዱ፡፡ የአብሮነቱን ገመድም በጠሱት፡፡ ይሄ እጅግ በጣም አስፈሪው አደጋ ነው፡፡ ወደ አገራችሁ? ማለት ምን ማለት ነው? የብአዴን ዝምታስ? የፌደራሊዝሙ መጨረሻስ?

የብአዴን ዝምታ ስል አንድ ብርቱ ኢትዮጵያዊ ትዝ አሉኝ፡፡ ነብሳቸውን ይማርና እኒህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ብአዴን እንዲፈጠር እንደ ምክንያት የሆኑ ሰው ናቸው፡፡ ባለ አፍሮ ፀጉርና ደርባባ፤ ረዘም ያለ ካፖርት መሳይ ኮት የሚያዘወትሩ፤ ኢትዮጵያን አብዝተው የሚወዱና ኢትዮጵያውያንን በቀዶ ህክምና ሞያቸው ሲያገለግሉ የኖሩ፤ ለገበሬ ታላቅ ክብር የነበራቸው፤ የኤርትራን መገንጠል አብዝተው በአደባባይ የተቃወሙ ሙሁር ናቸው፡፡ ፕ/ሮ አስራት ወልደየስ፡፡

የፕ/ሮ አስራት ወልደየስ የቅርብ ወዳጅ የነበሩ ሰው እንዳጫወቱኝ የኢህአዴግን የፌደራሊዝም አወቃቀር

ወደ 10 ዞሯል

# የራሳችንን ህንፃ ለመገንባት መልስ እየተጠባበቅን ነው



የዛሬው እንግዳችን አቶ ፀጋዬ አላምረው ይባላሉ፡፡ ተወልደው ያደጉት ጐጃም ውስጥ በምትገኘው በይልማና ዴንሳ ወረዳ ነው፡፡ አቶ ፀጋዬ የሒሳብ ባለሙያና የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር ሲሆኑ ከባልደረባችን ብስራት ወ/ሚካኤል ጋር አጭር ቆይታ አድርገዋል፤እንድታነቡም በአክብሮት ጋብዘናል፡፡

- አቶ ፀጋዬ ወደ ፖለቲካው ሕይወት እንዴት ገቡ?

በራሴ ተነሳሽነት የድርሻዬን ለመወጣት ተማሪ እያለሁ ነው የገባሁት፡፡

ወደ ፖለቲካው የገባሁት በወቅቱ ልጅም ስለነበርኩ በሀገሪቱ ላይ ያኔ የተፈጠረው ችግር ሲሆን በተለይም የኤርትራ መገንጠል፣ዜጐችን በቋንቋና በጐሳ የመከፋፈል፣የአሰብ ወደብ በህገወጥ መንገድ ለኤርትራ ሲሰጥ እንደማንኛውም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሲያንገበግበኝ በተናጠል ችግሩን መፍታት ስለማይቻል ወደ ተደራጀ ፖለቲካ ገባሁ፡፡ በወቅቱ በነ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ መአህድ የተባለ ድርጅት ተመስርቶ ስለነበር እኔም እዛው ተቀላቀልኩ፡፡ ከዚያም መአህድ ወደ መኢአድ ሲሸጋገርም እዛው ነበርኩ፡፡ በ1997 ዓ.ም መኢአድ ከቀስተደመና፣ኢዴፓ፣እና ኢዴሊ ጋር ቅንጅትን መስርተው በተፈጠረው ችግር አመራሮቻችንና አባሎቻችን ታሰሩ፡፡ በመጨረሻም አመራሮቹ ከእስር ከተፈቱ በኋላ ቅንጅትን በነበረበት ማስቀጠል ስላልተቻለና ወደ አንድ ውህድ ፓርቲ ለማምጣት ተሞክሮ ሳይሳካ ቀረ፡፡ በመጨረሻም ጥረቱ እንዳልተሳካ ሲታወቅ የወቅቱ የቅንጅት ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ ሀገርና ወገን ወዳድ ዜጐች በጋራ በመሆን አንድነት ፓርቲን መስርተን እየተንቀሳቀስን ነው፡፡ እኔም የሀገሪቱ ችግር በተለይ በዜጐች ላይ የሚፈፀመው በደልና ግፍ እየጨመረ በመምጣቱ እንደዜጋ የሚጠበቅብን ለመወጣት አሁንም በአንድነት ውስጥ እየጣርኩ እገኛለሁ፡፡ ወደፊትም ቢሆን ያለው የሀገራችን ችግር እስካልተቀረፈ ድረስ በህጋዊና ሠላማዊ መንገድ በሚታገለው አንድነት ውስጥ ሆኜ እታገላለሁ፡፡

- በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ያልዎት የስራ ድርሻ ምንድነው?

የፓርቲው የፋይናንስ ጉዳይ ምክትል ኃላፊ እና የብሔራዊ ም/ቤት አባል በመሆን እያገለገልኩ እገኛለሁ፡፡

- የፋይናንስ ጉዳይ በፓርቲው ውስጥ በዋነኝነት የሚያከናውነው ተግባር ምንድነው?

ከአባላት ገንዘብ ማሰባሰብ፣ለፓርቲው መጠናከር የሚያገለግሉ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ሥርዓት መዘርጋት፣ ጋዜጣው (ፍኖተ ነፃነት) የሚጠናከርበትን የገንዘብ አቅም ማጐልበትና በፓርቲው ምክር ቤት የፀደቁትን በጀቶች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውንና እየዋሉ መሆናቸውን መከታተልና መቆጣጠር ዋነኛው የፋይናንስ ክፍል ተግባር ነው፡፡

- በእናንተ ክፍል በፓርቲው ውስጥ የተሰራ ውጤታማ የሆነ ሥራ ካለ ቢጠቅሱልኝ?

የፋይናንስ ክፍል ፓርቲው 2ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን ካከናወነ በኋላ በአዲስ መልክ ተዋቅሮ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ይህ ኮሚቴ በስሩ ሦስት ኮሚቴዎችን አቋቁሟል፡፡

የመጀመሪያው ቅስቀሳና ግብይት በውጭ ሀገሮች ገንዘብ አሰባሳቢ ክትትል ኮሚቴ፣ሁለተኛው በሀገር ውስጥ ድጋፍ ሰጭዎች በዓይነትና በገንዘብ የሚደረገውን ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴና ሦስተኛው የቀጠናዎች አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሯል፡፡ እነዚህ ሦስት ኮሚቴዎች በሥራቸው ንዑሳን ኮሚቴ በማቋቋም የየራሳቸው ዕቅድና በጀት አውጥተው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡

በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ የወጣው የእራት ግብዣ መርሃ ግብር የገንዘብ ማሰባሰብ ሂደት ለማከናወንም ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ ሌላው የኢንፎርሜሽን ማናጅመንት ሲስተም (የመረጃ አስተዳደር ዘዴ) በመዘርጋት አባላትን የት እንደሚገኙና ስንት እንደሚከፍሉ በማጠናቀር ኮምፒዩተራይዝድ የማድረግ ሥራ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡ በቅርቡ ይሄም ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የሥራ ክፍሉ ከተቋቋመ አራተኛ ወሩ ሲሆን ለጊዜው ያከናወናቸው ከላይ የጠቀስኳቸው ውጤታማ ስራዎቻችን ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

- በገንዘብ ማሰባሰቡ ሥራስ ምን ያህል ሄዳችኋል?

የሥራ ክፍሉ ምን ያህል ገንዘብ ለመሰብሰብ እንዳሰበ አቅደን በፓርቲ ብሔራዊ ም/ቤት ፀድቆ ወደ ተግባር ገብተናል፡፡

- በዋነኝነት የወደፊት የገንዘብ ምንጫችሁ ሊሆን የሚችለው ምንድነው?

እኛ ማለትም ፓርቲው በዋነኝነት የገንዘብ ምንጭ ብለን የምናስበው ከአባሎቻችን የምናገኘው ድጋፍ ነው፡፡ ይህ ማለት አባላት የሚከፍሉት ወርሃዊ መዋጮ ብቻ ፓርቲውን ወደፊት ያራምደዋል ብለን አናስብም፡፡ ለምሳሌ አባላት ከወርሃዊ መዋጮ ክፍያ በተጨማሪ በሚችሉት አቅም ያላቸውን ጊዜ፣ጉልበት፣ቁሳቁስና እውቀታቸውንም በመለገስ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በገንዘብ ሲተመን ቀላል አይደለም፡፡

ከአባላት በተጨማሪ በሀገር ውስጥና በውጭ ያሉ ከፓርቲው ደጋፊዎች የምናገኘው ድጋፍ ሌላው ትልቅ የገንዘብ ምንጫችን ነው ብለን አቅደናል፡፡

- ሌላ የገንዘብ ምንጭ መፍጠር አይቻልም?

ይቻላል፡፡ እኛም በዕቅዶቻችን ላይ አስፍረናል፡፡ አንዱ የገንዘብ ምንጭ ይሆናል ያልነው በኢንተርኔት ከደጋፊዎችና አባላት ገንዘብ በመሰብሰብ ስልት፣የካርድ ሽያጭ፣የእራት ግብዣ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለፓርቲዎች ከመንግሥት ድጎማ ይደረጋል ብለን እንጠብቃለን፡፡ ነገር ግን ድጎማውን ለማግኘት ለኢህአዴግ ታማኝ ተቃዋሚ መሆን ይጠበቃል፡፡ በዚህ ምክንያት ድጎማውን ማግኘት አይቻልም፡፡ ሌላው ፓርቲው (አንድነት) የራሱን የቢሮ ሕንፃ ለመገንባት አስቧል፡፡ ይህንንም ፓርቲው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሊዝ አስተዳደር ቢሮ ቦታ እንዲሰጠው በደብዳቤ ጠይቆ መልስ ቢሰጠን የህንፃው ዲዛይን ወጥቶ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በቀጥታ ወደ ሥራ በመግባት ህንፃውን በፍጥነት ለማጠናቀቅ በሀገር ውስጥ እና በውጭ የሚኖሩ አባላትንና ደጋፊዎችን እናስተባብርና ለቤት ኪራይ የምናወጣውን ወጪ በመቀነስ ለሌላ የፓርቲው እንቅስቃሴ መጠናከር እንዲውል ታስቧል፡፡ ምናልባት በምናደርገው የእራት ግብዣ ላይ የከተማ መስተዳደሩ በጐ ምላሽ ከሰጠን ለሕዝብ ይበሰራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ከላይ ከጠቀስኳቸው ውጭ ህጋዊ የሆኑ ሌሎች የገንዘብ መፍጠሪያ ምንጭ ለማካሄድ አስበናል፡፡

- ሀገር ውስጥና ባህርማዶ (ውጭ ሀገር) ካሉ አባሎቻችሁና ደጋፊዎቻችሁ የምታገኙትን ገንዘብ የምትቆጣጠሩበት ስልት አለ?

አዎ፡፡ አንድነት ፓርቲን ከሌሎች ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ በም/ቤት በፀደቀ በጀትና በዓመቱ መጨረሻ በገለልተኛ ኦዲተር ሂሳቡን ማስመርመሩ ነው፡፡ ማንኛውንም ለፓርቲው የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ መጀመሪያ ባንክ ቤት ከገባ በኋላ ነው ሥራ ላይ የሚውለው፡፡ በገንዘብ ቁጥጥር ስርዓቱ ጥብቅ ነው፡፡ ገቢና ወጭ ሽያጮች እንኳ ሲካሄዱ በህጋዊ ደረሰኝ ነው፡፡ ሌው ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ወጪ እንኳ ሊደረግ አይችልም፡፡ የምንከተለው ዘመናዊውን የሒሳብ አያያዝ ስልት ነው፡፡

- አንድ ግለሰብ በተለይ ባለሀብት ስሜ ሳይጠቀስ በቁሳቁስም ሆነ በገንዘብ ፓርቲውን መርዳት እፈልጋለሁ ቢል ምን ታደርጋላችሁ?

በመጀመሪያ ፓርቲያችን ያለደረሰኝ ምንም ዓይነት ገንዘብም ሆነ ቁሳቁስ አይቀበልም፡፡ ምንአልባት ድጋፍ ማድረግ ቢፈልጉ እንኳ በልጃቸው፣በባለቤታቸው አሊያም በጓደኞቻቸው ስም ገቢ አድርገው ደረሰኝ መቀበል አለባቸው፡፡ ነገር ግን ለአንድነት ፓርቲ ድጋፍ ማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ፈርቶ ሳይሆን ደፍሮ ቢሆን እንሻለን፡፡ በተለይ በውጭ የሚገኙ ደጋፊዎቻችን በአካባቢያቸው በሚገኙ የአንድነት ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር (ቻርተር) ጋ በመሄድ አሊያም በመላክ አስተዋፅዖ ማድረግ ይችላሉ፤ በአቅራቢያቸው የአንድነት ቻርተር ከሌለም በፓርቲው የሒሳብ ቁጥር ገቢ ከተደረገና የላኩበትን ደረሰኝ ሲልኩልን እኛም ገንዘባቸው ወደ ፓርቲው ካዝና ስለመግባቱ ማረጋገጫ ደረሰኝ እና የምስጋና የምስክር ወረቀት ባሉበት ሀገር እንልካለን፡፡ በቅርቡም በዌብሳይት ክፍያ እንጀምራለን፡፡ ከዚያ በኋላም ድጋፋቸውን በዚህ መልኩ ገቢ ማድረግ እንደሚችሉ ከወዲሁ እናሳውቃለን፡፡ በሀገር ውስጥ ያሉ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ከፓርቲው ዋና ጽ/ቤትም ሆነ በክልሎች ከሚገኙ ቢሮዎቻችን ለሰጡት የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ድጋፍ ደረሰኝ መቀበል አለባቸው፡፡

- ወደፊት አንድነት በፋይናንስ በኩል ምን ለመስራት አስቧል?

ጠንካራና አስተማማኝ ፋይናንስ ያለው ተቋም በመገንባት ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ አስበናል፡፡ ይህ ሲባል ከፖለቲካው እንቅስቃሴ ሳንርቅ የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል የበኩላችንን ለመወጣት ቅድሚያ ጠንካራ ተቋም በመመስረት በጥቂቱም ቢሆን ከጥገኝነት ለመላቀቅ አቅደናል፡፡ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ያሉ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ገንዘባቸውን፣እውቀታቸውንና ውድ ሕይወታቸውን እየሰጡ ያሉት የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይፈጠራል ብለው በማሰብ ስለሆነ ለሚያደርጉልን ድጋፍ ሁሉ አንድነት ምስጋናውን እያቀረበ ከዚህ በኋላም ድጋፋቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ፓርቲያችን ይተማመናል፡፡

- የሀገሪቱን ወቅታዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዴት ታዘቡት?

ለመግለፅ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምሁራን፣ወጣቶች፣ገበሬዎች ከሀገራቸው እንዲሰደዱ ተደርጓል በተለይ ወጣት ምሁራን የፖለቲካው ሥርዓት በፈጠረው ችግር ሲሰደዱ መንገድ ላይ የሚቀሩት ብዙዎች ናቸው፡፡ ሴት እህቶቻችንም በአረብ ሀገራት እየሄዱ የቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመቀየር ሲሉ መከራና ግፍ እየተቀበሉ ነው፣ ህይወታቸውም እያለፈ ነው፡፡ ገበሬዎች ሳይቀሩ ከኖሩበት ቀዬ በግዳጅ እንዲፈናቀሉ እየተደረገና እንደሌላ ሀገር ዜጋ እየታዩ ነው፡፡ ለምሳሌ ከቤንች ማጂ በደቡብ ክልል መንግሥት ልዩ ትዕዛዝ እንዲፈናቀሉ ተደርጓል፡፡ እነኚህ ዜጐቻችን የአካባቢው ማኅበረሰብ ሳይቀር እያለቀሰ ሸኘቷቸዋል፣ አሁንም ኢትዮጵያዊነታቸው ተንቆ አማራ ናችሁ ወደ ሀገራችሁ ሂዱ ተብለው ገበሬዎች እንኳ እየተሰቃዩ ነው፤የሚገርመው ሀገራቸው ኢትዮጵያ ሆኖ ሳለ ወደ ሀገራችሁ መባሉ የበለጠ ያበግናል፡፡

በሌላ በኩል ለሀገራችን የሚቆረቆሩ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና ጋዜጠኞችም በግፍ ታስረው እየተሰቃዩ ነው፡፡ እዚህ ላይ አቶ አንዱዓለም አራጌ፣አቶ በቀለ ገርባ፣አቶ ናትናኤል መኮንን፣አቶ አልባና ሌሊሳ፣ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና ሌሎች ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞችም ለእስር ተዳርገዋል፡፡ እንደነ አንዱዓለም ያሉ ወጣቶች ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው በመቆርቆራቸው ከማሰር ይልቅ መንከባከብና መሸለም ይገባ ነበር፡፡ ምክንያቱም ሀገሪቱን በቀጣይ እንዲመራ የተዘጋጀ ወጣት በሌለበት በራሳቸው ተነሳሽነት በህጋዊ መንገድ ወደ ፖለቲካው ገብተው መሳተፋቸው ሊያስመሰግናቸው ይገባ ነበር፤ነገር ግን ለእስር መዳረጋቸው የሀገሪቱ የፖለቲካ ነፀብራቅ ነው፡፡

የኑሮ ውድነት፣የዋጋ ግሽበት፣የመሰረታዊ ፍጆታ ዕቃዎች የዋጋ ንረት፣የታፈነ ጩኸት፣ስደት፣ረሃብና ስቃይ የእርስበርስ ግጭትና ፍርሃት የወቅቱ የፖለቲካ ውጤት ነውና ሁላችንም በአንድነት ተረባርበን ልናስተካክለው ይገባል፡፡ ድህነቱም በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ነው ያለው፡፡

- በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ድህነት ቀንሷል የሚል ሪፖርት መንግሥት ይፋ ማድረጉን አልሰሙም?

ሰምቻለሁ ይሄ ሕዝብን የመናቅ ካልሆነ በየትኛው የኢኮኖሚክስና የመረጃ ቀመር ነው ድህነት ቀንሷል የሚባለው? እኔ ቀልድ መስሎ ነው የሚታየኝ፡፡

በአሁን ሰዓት ዜጐቻችን በቀን አንዴ እንኳ መብላት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ ከተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ረሃብና ችግር ፀንቶባቸው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በየመንገዱ ህፃናት፣አዛውንትና ወጣቶች ሲለምኑና ጐዳና ሲያድሩ እያየህ፤የነኚህም ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በምን ሂሳብ ነው ድህነት ቀንሷል የሚባለው? እኔ በበኩሌ ይሄ ሕዝብን አላውቅህም፣አልራበህም፣ጠግበህ ደልቶሃል ብሎ የመሳለቅ ያህል ነው የሚመስለኝ፡፡ ያለውን የድህነት መባባስ ለማረጋገጥ ሌላ ሳይንሳዊ ቀመር ማወቅ ሳያስፈልግህ በየመንገዱ እና በየቤታችን አይተን የምናውቀውና የምናረጋግጠው እውነታ ነው፡፡ ህፃናት ተማሪዎች ርቧቸው በትምህርት ገበታቸው ላይ እያሉ እየወደቁ እኮ ነው፡፡

- እስኪ ስለተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እናንተን ጨምሮ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አያይዘው የሚነግሩኝ ነገር ካለዎት?

ተቃዋሚች ላይ የማይካድ ትልቅ ችግር አለ፡፡ ሀገራችንን በአንድ ላይ ተጋግዘን ከማቅናት ይልቅ መናናቅ መለያየትና መከፋፈል ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት በአንድ ብሔር ስም እንኳ ከ10 ያላነሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ፡፡ ሁሉም ግን ብሔሩን ከስቃይ ሊታደጉት አልቻሉም፣ ይልቅ የማኅበረሰቡን ችግር አባባሱት እንጂ፡፡ ስለዚህ ለሀገራችንና ሕዝባችን ሕልውና በአንድ ላይ ተሰባስበን በጠነከረና በተባበረ ክንድ መታገል ይገባናል፡፡ ሕዝቡ ላይ የሚደርሰውንና የሚፈፀመውንም በደል ወደማኅበረሰቡ ወርደን ልንጋራ ይገባል፣ለሥልጣን ከመሮጥ ለሀገርና ለሕዝብ ህልውና ልንጥር ይገባናል፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጡረታ ከወጡ በኋላ የሚገባበት ሣይሆን ከወጣትነት ጀምሮ መታገልን ይጠይቃል፡፡

# "የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም"

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) የብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብትና ጥቅም መከበርን ይደግፋል:: የከፋፍለህ ግዛው የጎሳ ፖለቲካን ግን አጥብቆ ይቃወማል:: የኢህአዴግ መርዘኛና የከፋፍለህ ግዛው የጎሳ ፖለቲካ በሃገሪቱ ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት በተደጋጋሚ ታይቷል:: በበደኖ፣በአርባጉጉ፣በወለጋና በጋምቤላ የተፈጠረው ችግርና የደረሰው እልቂት አንድ ማስረጃ ነው:: በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የዚህ መርዘኛ ፖሊሲ ውጤት በደቡቡ የሃገራችን ክፍል በተለይ ደግሞ በቤንች ማጂ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ እየታየ ነው:: ከክልሉ ፕሬዚደንት ጀምሮ በክልሉ ሹማምንት በተሰጠ የጽሑፍ ትዕዛዝ ዓይን ያወጣ በደል እየተፈጸመ ሕዝብ ለሰቆቃ እየተዳረገ ነው::

የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በተለይ ከሃገራችን የአማራው ክልል የመጡና እስከ 30 ዓመት ድረስ በቦታው ሰፍረው መሬት በህጋዊ መንገድ አግኝተው፣ቤተሰብ መሥርተው፣ንብረት አፍርተው፣ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ተጋብተውና ተዋልደው ከኖሩበት አካባቢ እየተነቀሉ እንዲባረሩ ተደርጎ ለስቃይ እየተዳረጉ ነው::

የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 32 "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ . . . በመረጠው የሃገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት . . .ነፃነት አለው" ይላል:: ስለዚህ አንድ ዜጋ የአካባቢውን ሕግና ሥርዓት እስከአከበረ ድረስ በሃገሩ የትኛውም ክፍል የመኖር መብት እንዳለው ይህ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ግልጽ አድርጓል:: ቢያጠፋም በክልላዊውም ሆነ በሃገራዊው ሥርዓት ታይቶ ሕጉ በሚወስነው መሠረት በአለበት ይቀጣል እንጂ በገዛ ሃገሩ እንደ ባዕድ ከአካባቢው አይባረርም:: ዜጎችን ከሚኖሩበት አፈናቅሎ ማባረር፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወታቸው እንዲቃወስ፣ሕፃናት ትምህርታቸው እንዲቋረጥ ማድረግ ኢ-ሕጋዊና ኢ-ሰብአዊ ነው::

ኢህአዴግ እንደሚነግረን የፌደራል ሥርዓቱ ዓላማ የብሔሮችን፣የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን መብትና ጥቅም ለማስከብር ነው:: ይህ ማለት ግን ዜጎች መብታቸው የሚከበረውና ጥቅማቸው የሚጠበቀው በክልላቸው ውስጥ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው ማለት አይደለም:: ዜጎች በሃገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ቦታ በሕግ የተሰጧቸው መብቶችና ጥቅሞች መከበር አለባቸው:: ብአዴን ስሙ እንደሚያመለክተው ለአማራው ሕዝብ መብትና ጥቅም የቆምኩ ነኝ ካለ በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል የሚገኙ ተወላጆች በሕግ የተሰጧቸው መብቶችና ጥቅምች መከበራቸውን ከሚመለከታቸው ክልሎች ኃላፊዎች ጋር በመመካከር ማስከበር መቻል አለበት:: ብአዴን ግን እስከ አሁን ድረስ ይህንን ሲያደርግ አልታየም:: የኢህአዴግ አንዱ ክፍል የሆነው ደኢሕዴን ከአማራ ክልል የመጡ ዜጎችን በግፍ ከክልሉ ሲያባርር "የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም" እንደሚባለው ብአዴን ለክልሉ ሕዝብ መብትና ጥቅም ለመቆም አቅም አንሶታል:: ይባስ ብሎ ደግሞ እኩያ አጋሩ ነው ከሚባለው ደኢሕዴን ጋር በመነጋገር የማፈናቀሉ ድርጊት እንዲቆም፤ የተፈናቀሉትም ወደየቦታቸው እንዲመለሱ ለማድረግ በመጣር ፈንታ ደኢሕዴን የወሰደውን ግፋዊ ርምጃ አሜን ብሎ የተቀበለ በሚመስል ሁኔታ ተፈናቅለው ወደ አዲስ አበባ የመጡትንና በችግር ላይ የወደቁ የክልሉ ዜጎች እየደረሰባቸው ያለውን ስቃይ የኢትዮጵያ ሕዝብና የዓለም ህብረተሰብ እንዳያይ በየቀበሌው በማጎርና ወደተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ያለፈቃዳቸው በመበታተን የመሸፋፈን ሥራ በመሥራት ላይ ነው:: እዚህ ላይ በብአዴንና በደኢሕዴን መካከል የአቻላቻና በእኩልነት ተመካክሮ ለችግሩ መፍትሔ የመሻት ሁኔታ አይታይም::

አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ወላሳ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ለቤንች ማጂ ዞን ጽ/ቤት በጻፉት የማባረሪያ መመሪያ ላይ በአራቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል የተደረሰ የጋራ ስምምነት መኖሩን ጠቁመዋል:: ይህ ስምምነትም እንዲህ ይላል፡- "በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ሰፈራን በሚመለከት ያለው አሰራር ከክልል ክልል የሚፈፀም ሳይሆን በክልሎች በውስጣቸው ብቻ እንዲፈፀም የጋራ ሃገራዊ ስምምነት ተደርጓል":: በዚህ ስምምነት መሠረት የሕዝብ ሰፈራ ማካሄድ ካስፈለገ መካሄድ ያለበት በየክልሉ ውስጥ ብቻ ነው የሚል ግልፅ ትርጉም አለው:: ይህ የተሳሳተ ስምምነት ነው:: ዜጎች ሥርዓት በአለው ሁኔታ በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል የመኖር ሕገ-መንግሥታዊ መብት አላቸው:: ይህ መብት መከበር አለበት:: የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ይህን መብት የመገደብ ሥልጣንም ሆነ መብት የላቸውም::

የተፈናቀሉ ዜጎች እንደሚሉት ከሆነ የመፈናቀላቸው ስውር ምክንያት በአለፉት ምርጫዎች መሬት የሰጣቸውን የኢህአዴግ መንግሥት ስለ አልመረጡ ነው:: ተፈናቃዮቹ "መሬት የሰጣችሁን መንግሥት ስለአልመረጣችሁ ከእንግዲህ ወዲህ አትፈልጉም" ተብለናል ነው የሚሉት:: ከዚህ አኳያ የኢህአዴግ አካል የሆነው ብአዴን የተፈናቃዮቹን መብትና ጥቅም ከማስከበር ወደ ኋላ ማለቱ ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ትርጉም ያለው ይመስላል::

በአጭሩ ዜጎችን የማፈናቀል ኢ-ሕጋዊና ኢ-ሰብአዊ ድርጊት መቆም አለበት:: የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ነበሩበት ተመልሰው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወታቸውን መቀጠል አለባቸው:: ሕፃናት ወደ ትምህርት ቤታቸው ተመልሰው ትምህርታቸውን መቀጠል አለባቸው:: የተነጣጠሉ ቤተሰቦች መሰባሰብ አለባቸው:: የዜጎች የህይወት ዋስትና መረጋገጥ አለበት:: የተነጣጠሉ ቤተሰቦች መሰባሰብ አለባቸው:: የዜጎች የህይወት ዋስትና መረጋገጥ አለበት:: ወላጆች "አገራችን የት ነው?" የሚለውን የልጆቻቸውን ጥያቄ ለመመለስ ሊቸገሩ አይገባም::

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ

# ታግቶ ከነበረው አጽም ላይ አበባ አኑረናል

## አቶ ተረፈ ኃይሌ

በብሩክ ከበደ

ቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑ አጽም ከየወደቀበት ተሰባስቦ ያረፈበት የሰማዕታት ሙዚየም እንዳንገባ ታግደን ነበር ያሉ ተጐጂዎችና የሰለባዎቹ ቤተሰቦች ባለፈው እሁድ መጋቢት 9 ቀን 2004 ዓ.ም ረፋድ ላይ አበባ የማኖርና የሻማ ማብራት ስነስራት አካሄዱ::

በለቱም የተጎጂ ቤተሰቡን በመወከል አቶ ተረፈ ኃይሌ "እስከዛሬ ድረስ በጥቂት ግለሰቦች አንባገነናዊ ህሳቤና ከሙዚየሙ መገንባት ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን ከፍተኛ ምዝበራ፣ ብክለትና አስተዳደራዊ ብልሹነት ተከታትለን በማጋለጣችንና ተጎጂዎችን ከሥራችን በማሰባሰባችን ታግደን የነበርን ቢሆንም አሁን ግን የተለያዩ እልህ አስጨራሽ ትግሎችን አካሂደን ዛሬ ድላችን ለማብሰራችን እንደ አንዱ ምልክት ተደርጎ ይቆጠራል::" ካሉ በኋላ "ሌሎቹም የእኛን አርአያ በመከተል ለፍትህና ዴሞክራሲ የተሰው ወገኖቹን አላማ እንዲቀጥሉበት አሳስበው የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ከመጀመሪያው ጀምሮ ጉዳዩን እየተከታተለ ለሕዝብ ይፋ ስላደረገልን ከልብ እናመሠግናለን::" ሲሉ ተናግረዋል::

በዚህ የአበባ ማስቀመጥ ስነ-ሥርዓት ላይ ከአንድ መቶ ሃያ በላይ ተጎጂና የሰማዕታት ቤተሰቦች ለፈጣሪ ምስጋና ይድረሰው በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ በአጽሞቹ ላይ አበባ የማስቀመጥና ሻማ የማብራት ስነ-ሥርዓት አካሄደዋል:: የሰማዕታቱ መታሰቢያ አዲሱ የቦርድ አመራርም በዝግጅቱ ላይ የተገኙ ሲሆን የቦርዱ ሊቀመንበር አቶ አብዱላዚዝ አህመድ" ከእንግዲህ በራሳችን ጉዳይ የሚከለክለን ማንም አይኖርም" ብለዋል::

በመጨረሻም የቀድሞው በሙስናና በአስተዳደር ብልሹነት ተወግዞ ከአመራርነት የተወገደው ወ/ሮ አይንዬ ጽጌ (የአቶ ተፈራ ዋልዋ ባለቤት) የሚመሩት ማህበር ራሳቸውን ጨምሮ ኢህአፓን የመታው የመኢሶን አባላት ነበሩ በሚልም በስብሰባው ላይ መብጠልጠላቸው የሚታወቅ ነው::

# ኢህአዴግ ወዳጆቹን ጨርሶል

## አንዳንድ የከተማዋ ነዋሪዎች

ብሩክ ከበደ

ነዋሪነታቸው በአዲስ አበባ ከተማ የሆኑ ግለሰቦች "ኢህአዴግ ቀደም ሲል ደርግን ጨፍጫፊና ፋሽስት ነው" እያለ ሲያውግዘውና እሱ ከመሰረተው ኢሰፓ ፓርቲ ጋር አብሬ አልሰራም እያለ ቢቆይም አሁን ግን ውስጡ እየሰገሰገ ነው:: ሲሉ ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል አቤት አሉ::

አቤቱታቸውን አቶ ካቢቲመር ተሰማ በተባለው ግለሰብ በኩል እንዳቀረቡት ከሆነም ኢህአዴግ በደርግ ጊዜ በየቀበሌው በአብዮት ጥበቃነት፣ አይወማ፣ በአይሴማ፣ በካድሬነትና በደህንነት ተቋማት ውስጥ ይሰሩ የነበሩትን በስሩ በማሰባሰብ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ቁርሾና ቂም እንዲያገረሽ ወይም እንዲባባስ ተግቶ እየሰራ በመሆኑ ኢትዮጵያውያኖች ከዚህ አደገኛ አካሄድ ጠንቀቅ ይበሉ ሲሉ አስገንዝበዋል::

# ኢትዮጵያውያን ሀገራችን . . .

ከገፅ 14 የዞረ

ልጆችንና ነፍሰጡር ሴቶችን ይዞ መሰደድ ከስደቶች ሁሉ የከፋ ስደት ነዉ:: ኢትዮጵያዉያን ሁሉ እንደዚህ ያለዉን አሰራር ልንቃወመው ግድ ነው:: ይህ ዓይነቱ ተረጋግተው እየኖሩ ያሉትን ሰዎች ሳያስቡ ማፈናቀሉ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ነግ በኔ የሚያሰኝ ነዉ:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተወልዶ ባደገበት አካባቢ አይደለም ያለዉ:: ትግራይ የተወለደዉ ካፋ፣ ወለጋ የተወለደው ሀረር፣ ወሎ የተወለደው ጎንደር፣ ሀረር የተወለደዉ ጂማ ..... እና በመሳሰሉት ክልሎች ሁሉም ሀገሩ ስለሆነ በመረጠውና በወደደው ክልል ሄዶ ሠርቶ ንብረት አፍርቶ መኖር ይችላል:: በዚህ አሁን ባለዉ ሁኔታ ግን ማንም የትም ምንም አለኝ ለማለት ይቸገራል:: መተማመንም አይችልም:: ስለዚህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለተፈናቀሉት ምስኪን ገበሬዎች ሳይሆን እንዲህ አይነቱ ህገወጥ አሰራር ነገ በራሱ ላይ እንዳይደርስ ዛሬ ላይ ሆኖ ይህንን አሰራር ይቃወም ዘንድ ግድ ነዉ:: መቃወምም ይጠበቅበታል::

ውድ አንባቢያን! እኔ በሁኑ ሰዓት በሀገራችን በኢትዮጵያ በተለይ በደቡብ ክልል እየተደረገ ያለዉን ሁኔታ ስሰማ ያለሁበት ሀገር በእርግጥ አባቶቻችን የነገሩን ኢትዮጵያ ይህቺ ናትን? እስከማለት ደርሻለሁ:: ሀገራችን ኢትዮጵያ እንኳን ለራሷ ህዝብ ይቅርና መጠጊያ ላጡና በራሳቸዉ ህዝብ መከራና ስደት ሲደርስባቸዉ ለነበሩ ለዉጭ ሀገር ሰዎች መጠጊያ እንደነበረች ታሪክ ያትታል:: ነቢዩ መሐመድ ያን ጊዜ የእስልማና ኃይማኖትን እንዳይሰብኩ መከራ በደረሰባቸዉ ጊዜ ለተከታዮቻቸዉ ያሉት እንዲህ ነበር" ወደ ሐበሻ ተሰደዱ፤ በእርሷ አንድ ንጉስ ከእርሱ ፊት ማንም ተበዳይ አይኖርም::...ስለዚህ ተሰደዱ ካላችሁበት ሁኔታ አውጥቶ ድል እስከንጎናጸፍ ድረስ..." አህመዲን ጀበል ከጻፉት ገጽ 34 የተወሰደ::በዚሁ መጽሐፍ በገጽ 37 ላይ ስደተኞቹ ኢትዮጵያ የነበረውን ሁኔታ እንዲህ ሲሉ ነበር የገለጹት:: "ሐበሻ ገባን፤ መልካም ጎረቤቶችንም አገኘን::በሃይማኖታችን ምክንያት የሚደረግብን ተፅእኖ አልነበረም:: ለአላህንም በሰላም መገዛት ጀመርን::አንድም ችግርና መከራ አላጋጠመንም:: የምንጠላውን ነገር አልሰማንም::" እንግዲህ እኔ ከታሪክ ያነበብኩትና አባትና እናቴ የነገሩኝ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ኢትዮጵያዉያን እንኳን ለወገናቸዉ ለኢትዮጵያዉያን ይቅርና ወገኖቻቸዉ ላሳደዱአቸዉ ሳይቀር መጠጊያ መልካም ጎረቤት እንደነበሩ ይታወቃል:: አሁን ባለንበት ደረጃ ግን የሚደረገዉን ስሰማ ቤተሰቦቼ ኢትዮጵያ ከምትባለዉ ሀገር በስደት ወደሌላ ሀገር ይዘውኝ ሄደዉ ከሌላ ሀገር ያሳደጉኝ እስኪመስለኝ ድረስ ግራ ተጋብቻለሁ::

ሌላ ብዙ ጊዜ በቤተክርስቲያን አካባቢ የሚነገር አንድ ታሪክ አለ፡፤ ሀገሩን ጀርመን ይሁን እንግሊዝ ወይንም ፈረንሳይ እንደሆነ በቅጡ አላስታውሰውም:: ሆኖም ለዛሬዉ ጽሁፌ ግን ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ ልጠቀምበት ተገደድኩ፤ ታሪኩ እንዲህ ነዉ:: በአንድ ወቅት ከላይ ከጠቀስኳቸዉ የውጭ ሀገር ዜጋ ልጁን ይዞ ኢትዮጵያን ሊጎበኝ ይመጣል:: ታዲያ በትግራይ በኩል ሲገባ ወቅቱ እንደዛሬው ሆቴል በየቦታዉ አልነበረምና ምግብ ፈልጎ ወደሰፈር ጎራ ሲል ቀኑ 21 ኖሮ የማርያም ዝክር ተደግሶ ነበር እንጀራዉን አብልተዉ መጠጡን አጠትተው የሸኙት:: መቼም እንዳሁኑ ችግር አልነበረምና ለነገሩ በዚህ ዓመትም በአጋጣሚ ወደ ትግራይ ሄጄ የአቡነ አረጋዊ ዕለት የትግራይ ህዝብ አላፊ አግዳሚዉን ከመንገድ እየጎተተ ሲያበላ አየሁ:: ኢትዮጵያዊ ኖረዉም አልኖረዉም ያለውን ነው ተካፍሎ የሚበላዉ:: ታዲያ ይህ ፈረንጅ ከበላ ከጠጣ በኋላ ሂሳብ ሊክፍል ሲል እንደማይከፈል ይነግሩታል:: ይህ ሰው ለልጁ "እንዴት ነዉ ነገሩ? በነጻ የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ እኒህ ኢትዮጵያዉያን እንደ እግዚአብሔር ናቸው?" ይለዋል:: ከትግራይ ወጥተዉ ወሎም ሲገቡ እንዲሁ በዓታ ዝክር ተደግሶ ኖሮ በልተዉ ጠጥተዉ ሊከፍሉ ሲሉ እንደማይከፍሉ ይነግሩአቸዋል፤ በዚህም ይህ ፈረንጅ ለልጁ "እንዴት ነዉ ነገሩ? በነጻ የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ:: እኒህ ኢትዮጵያዉያን እንደእግዚአብሔር ናቸዉ::" ይለዋል:: ሸዋም ሲገቡ እንዲሁ ያጋጥመዉል፤ ያንኑ ቃል ለልጁ ይነግረዋል:: ጎጃምና ጎንደር ደቡብና ጉራጌ ሁሉን ጎብኝቶ ሲመለስ በኢትዮጵያውያን ደግነት የገጠመዉን ከእግዚአብሔር ጋር አመሳስሎ ለልጁ እየነገረዉ ወደሃገሩ እንደተመለሰ ይተረካል::

ይህ ፈረንጅ አርጅቶ ይሞታል:: ልጁ የአባቱን ሀብት ወርሶ እያለ አንድ ወቅት አንድ አስደንጋጭ ጋዜጣ ያነባል:: ያም የሚያነበዉ ጋዜጣ ያ እንደእግዚአብሔር ያለምንም ክፍያ እንግዳ የሚያበላዉ ህዝብ መራቡን የሚገልጽ ነበር::ይህ ልጅ ወዲያዉኑ እግዚአብሔር ተርቧል ብሎ ከአባቱ የወረሰዉን ንብረት ሸጦ ለኢትዮጵዉያን እንዲሰጥ እንዳደረገ ይነገራል::

ስለዚህ የኢትዮጵያዉያን ባህል ይህ ሆኖ እያለ ዛሬ ወገንን "ወደ ሀገራችን ሂዱ" ማለት ምን ዓይነት ጭካኔ ነው? ለመሆኑ እነዚህ ዜጎች ሀገራቸው የት ነው? ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ኬንያ . . . ? አቶ ሽፈራው ሽጉጤ የሀገርን ትርጉም ቢመልሱልን ሕሊናችን ያርፋል:: በተረፈ ቦታህ አይደለም የሚል ኢትዮጳያውያን ይህንን አሸማቃቂ መርዘማ ፖለቲካ ልንቃወመው፣ ልንታገለው፣ ልናስቆመው ልንቀይረው ይገባል:: አመሰግናለሁ::

## ያንግ ሰቦም ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ክለብ ተማሪዎችን አስመረቀ

ያንግ ሳቦም ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ክለብ ለ8ኛ ጊዜ ያሠለጠናቸውን ተኳንዶ ሠልጣኞች ሰሞኑን አስመረቀ፡፡ ቴኳንዶ ክለቡ ባለፈው እሁድ ጥሪ የተደረገላቸው የክብር እንግዶች የቴኳንዶ ባለሞያዎችና የተመራቂ ቤተሰቦች በተገኙበት በአራት ኪሎ ሥልጠናና ትምህርት ማዕከል አስመርቋል፡፡

ምረቃው በደማቅ ሥነ ሥርዓትና ትርኢቶች የተከናወነ ሲሆን፡፡ ተማራቂዎች ቡድን እና በግል በመሆን ታዳሚውን ያዝናኑ የቴኳንዶ ትርኢቶችን አቅርበዋል፡፡ ያንግ ሳቦም ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ ክለብ በከተማችን ከሚገኙት ስመጥር የሥልጠና ክለብ አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ ሰባት ኮርሶችን አሰልጥኖ ማስመረቁ ይታወቃል፡፡

## ለገጣሚያን

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የፓርቲውን ህዝባዊ ዓላማና ራዕይ እንዲሁም በሰላማዊ ትግል ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ መዝሙር ለማዘጋጀት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ይህን አስመልክቶ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ግጥም ለህዝብ ግንኙነት ክፍል ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት

## መቅዲ የቴሌቭዥን ሾው ተጀመረ

በመቅዲ ፕሮዳክሽን ኀ/የተወሰነ የግል ማህበር አየተዘጋጀ የሚቀርበው "መቅዲ ሾው" የቴሌቭዥን ፕሮግራም በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ጀመረ፡፡ ፕሮግራሙ የታዋቂ ግለሰቦችን የህየወት ልምድ የሚያቀርብ ሲሆን ከዚህ ቀደም የአዳም ገመና ፣ ዘራፍ እና ዲፕሎማት የተሰኙ ፊልሞችን ለተመልካች አቅርቧል፡፡ መቅዲ የቴሌቭዥን ሾው የመቅዲ ፕሮዳክሽን ባለቤትና ስራ አስኪያጅ መቅደስ ፀጋዬ ነው፡፡

## 3ኛ የሻማ ምሽት

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የፖለቲካ የህሊና እስረኞችን የሚያስታውስበትን ሦስተኛውን የሻማ ምሽት ያካሂደል፡፡

ሰዓት፡- ከቀኑ 10፡30 ጀምሮ

ቦታ፡- በድርጅቱ ጽ/ቤት ግቢ

ውስጥ በሃገራችን የፖለቲካና የህሊና አስረኞች እንዳይኖሩ የምትመኙ ሁሉ የፕሮግራሙ ተከፋይ እንድትሆኑ ተጋብዛችኋል፡፡

# ከልማቱ ይልቅ . . .

ከገፅ 2 የዞረ

"ሙቭ አት ኢት" የተባለ ዓለም አቀፉ ተቋም በሠራው የዳሰሳ ጥናት መሠረት አብዛኞቹ ገለልተኛ ምሁራን ኢህአዴግ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የመውደቂያ ነጥብ እንዳላሰራ ይስማማሉ፡፡ ምሁራኖቹ ኢህአዴግ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እንዳልተሳካለት እንደሚያስብ በተመሳሳይ ሁኔታ ይስማማሉ፡፡ ስርዓቶች በሕዝብ ዘንድ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲገጥማቸው ቁሳዊና የሚታይ ነገር በማሳየት ሕዝብ ለማማሰል ይሞክራሉ፡፡ ዶ/ር መረራ ይህንን ሁኔታ "ኢህአዴግ በብዙ አቅጣጫ ስለጨነቀው እያተራመሰ ጊዜ ለመግዛት የፈለገ ይመስላል" ይላሉ፡፡

የህዳሴው ግድብ ከታወጀበት ጊዜ አንስቶ፣ ኢቲቪና "ልማታዊ አርቲስቶች" አሰልቺ በሆነ ፕሮፓጋንዳ ላይ ተጠምደው ይገኛሉ፡፡ ኢህአዴግ የስልጣን ቅብሉነቱ የመነጨው ከግድቡ ይምስል ያህል፣ "አባይን የገደበ ታላቁ መሪያችን" ፕሮፓጋንዳ ለአንዳንዳዶቹ አታካች ሆኗል፡፡ ከዚህም አልፎ ይህን ያህል ብር የሚወጣበት ፕሮጀክቱ ለምን የመስኖ ልማት አላካተተም? ግድብን ለመገንባት ግልጽ ጨረታ ለምን አልተደረገም? ከአከባቢ ተቆርቋሪዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሁሉ በሀገር ከዳተኝነት ያስፈርጃል፡፡

የኢህአዴግ ህልውና በህዳሴው ግድብ ላይ የተንጠለጠለ ይመስላል የሚሉም አልጠፉም፡፡ አባይን ግድብ ላይ ጥያቄ ማንሳት ማለት፣ ኢህዴግን የቆመበት መሰሶ እንደመነቅነቅ እየተቆጠረ ያለ ይመስላል፡፡

የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ ከሚያመጣው ልማት በላቀ መልኩ ለጠ/ሚኒስትሩ "አባይን የደፈረ መሪ" እየተባለ ይደሰኮርላቸው ጀመር፡፡ "በጠ/ሚኒስትሩ ዙሪያ ጣኦታዊ የፖለቲካ ተክለሰውነት (personality cult) ለመቅረፅ የመንግሥት ሚዲያ ፕሮፖጋንዳውን አጧጧፎታል፡፡

አንዳንዴ ፕሮፓጋንዳዎቹ "ዓባይ ከተገደበ፣ ሁሉም ችግሮች ይወገዳሉ" የሚሉ ይመስላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አካሄድ ፈረንጆች የፖለቲካ እሽኮለሌ (political abstraction) ይሉታል፡፡ በተጨባጭ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ፤ የኃይል መቆራረጥ የቀን ተቀን የዜጎች ምሬቱ ሆኖ እያለ፤ የመንግስት ቢሮክራሲ እጅግ የሚያበግን ሆኖ እያለ፤ ከስድስት ዓመት በኋላ ኑሮ ይለወጣል የሚል ፕሮፓጋንዳ እስኬት እንደሚያደርስ ማወቅ ይከብዳል፡፡

ወሳኙ ጉዳይ ታዲያ "የህዳሴ ግድብ ላይ እየተደረገ ያለው ከፍተኛ ፕሮፓጋንዳ፣ ዜጎች አሁን ያለባቸውን የኑሮ ሸክም አስረስቶ በተስፋ የመሙላት አቅሙ ምን ያህል ድረስ ይወስዳል?" ነው ይላሉ፡፡ አቶ መለስ ደጋግመው "የሕዝብ መነቃቃት እንዳይቀዘቅዝ መስራት ያስፈልጋል" የሚሉት ለዚሁ ይመስል፡፡

### ዴፕሎማሲያዊ እንደምታው

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በውሃ ፖለቲካ ለረዥም አመታት ተመራማሪ የሆኑት መምህር "ከባዱ ጥያቄ የግድቡ ግንባታ የግብፅን ይሁንታ ያገኛል ወይ? የሚል ነው» ይላሉ፡፡ እንደ ዶ/ሩ ትንተና ግብፅ አሁን ከምታገኘው ውሃ ላይ ትንሽም እንኳን ቢሆን ከተቀነሰ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደሚያስከትል ይታመናል፡፡ ግብፆች የውሃ ፍላጎታቸውን የሚተምኑት በአሁኑ ፍጆታቸው ላይ ብቻ ተመርኩዘው ሳይሆን የወደፊት የሕዝብ እና የኢኮኖሚ ዕድገታቸውን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ የሚያገኙት ውሃ በከፍተኛ መጠንየሚቀንስ ከሆነ እስከ ጦርነት ድረስ የዘለቀ መዘዝ ሊያመጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ አስቀድሞ ግብፅን ጨምሮ የአባይ ተፋሰስ ድንበርተኛ ሀገሮችን ስምምነት ማግኘቱ ሊታለፍ የማይችል ግዴታ ነው፡፡ ግድቡ የግብፅንና የሚመለከታቸውን ሌሎች ሀገሮች ይሁንታ ካገኘ መጪው ከሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጭ ዕርዳታና ብድር ሊሸፈን መቻሉንም መርሳት የለብንም፡፡

ችግሩ ግን ግብጾች አሁን የሚያሳዩት መለሳለስ ጊዜ ለመግዛት ብቻ ነው የሚሉም አልጠፉም፡፡ ግብጽ ውስጥ የፈነዳው ህዝባዊ ማዕበል ወደ ኢትዮጵያ ይመጣል ተብሎ በተፈራበት ወቅት፣ አቶ መሰል አባይን ለመገደብ ወሰኑ፡፡ በማያቋርጥ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ስትናጥ የነበረችው ግብጽ፣ "የተቆጠበ" ዲፕሎማሲን መርጣለች፡፡

አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ግብጽ እየተረጋጋች መምጣቷን ማስተዋል ይቻላል፡፡ በተለይም የሀገሪቱ ዋናኛ ፓርቲ ሙስሊም ብራዘርሁድ፣ ከወታደሩ ጋር ተናቦ የመስራት ሁኔታ መልካም ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይገልጻሉ፡፡ ሙስሊም ብራዘርሁድ Mr. XXን በቅርቡ ለሚደረገው ፕሬዝደንትነት የሚወዳደርለት እጩ አቅርቧል፡፡ ካይራት ኢል-ሻተር የግብጽ መሪ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ጥያቄ ታዲያ ግብጽ ይበልጥ እየተረጋጋች በመጣች ቁጥር፣ ካይራት ኢል-ሻተር የሚከተሉት ፖሊሲ ኢትዮጵያ እንደምትመኘው ዓይነት ላይሆን የመቻል ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የግብፅ አቋም በኢትዮጵያ ውስጥ ጉዳይ ሊኖር የሚችለው ተጽኖ ከህወሓት መሪዎች በደንብ አድርገው የሚረዱት ነው፡፡ በመሆኑ ለሚመጣው ከፍተኛ ተጽኖ ራስን ማዘጋጀት ወሳኝ ነው፡፡

### "ቁማርተኛው" መለስ

አቶ መለስን በቅርበት ያውቋዋቸው የነበሩ ሲናገሩ፣ መለስ ደንበኛ "manipulator" እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ የህዳሴውን ግድብ ውሳኔያቸውን ያየ ደግሞ፣ መለስ ከባድ "ቁማርተኛ" እንደሆኑ ይከራከራሉ፡፡ ይህ ባህሪያቸው በተለያዩ ጊዚያት በግልጽ ታይቷል፤ በበህወሓት በ1997 ዓ.ም. ገደማ በነበረው የውስጥ ትግሉ፣ በ1993 ዓ.ም. በተደረገው የውስጥ ትግልን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ግን የህዳሴው ግድብ በዘላቂነት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የለውጥ ፍላጐት በማደፈን፣ አሸናፊ ያደርጋቸው ይሆን?

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች መምህሩ "ኢህአዴግ ጊዜ ለመግዛት ያመጣው ሀሳብ መጥፊያው እንዳይሆን ነው ስጋት አለኝ" ካሉ በኋላ "ህብረተሰቡም በኑሮ ውድነቱና አባይን የመጠቀም የዘመኑ ጉጉት መኃል በአጣብቂኝ ተይዘዋል" ይላሉ፡፡

የመለስ የፖለቲካ "ቁማርተኛነት" ማብቂያ የቱ ጋ እንደሆነ

ወደ 14 የዞሯል

መገመት ያስቸግራል፡፡ ግን ቻይናውያን ከቁመራ አንጻር አንድ አባባል አላቸው፤ "If you must play, decide upon three things at the start: the rules of the game, the stakes, and the quitting time."

# ድህነት እና . . .

ከገፅ 14 የዞረ

ኑሮ እለውጣለሁ በማለት ውጭ ሄደው ምን እንደሚሰሩና ምን ዓይነት አስከፊ ችግሮች እንደሚገጥማቸው ሁላችንም የምናውቀው ነው፡፡ ይህ ሁኔታ - 1. በአሁኑ ሰአት መንግስት አደገ የሚለው ኢኮኖሚ የአብዛኛውን ቤትን እያንኳኳ ውድ እህቶቻችንን ለስደት እየዳረገ መሆኑን 2. በአሁኑ ጊዜ አገሪቱ ልጆቿን አስተምራ ለልማት መጠቀም ሲገባት ለችግር መዳጓን፤ 3. የአገሪቱ ኢኮኖሚ የሴቶችን የመኖር እና የመስራት መብትን በማክበር ሴቶችን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ ማሻሻል ሲገባው የሴቶችን በአገራቸው የመኖር መብት በአስከፊ ድህነት ምክንያት ነጥቋቸዋል፡፡ ይህም በባዕዳን አገር ተሰደው አስከፊ ኑሮን እንዲኖሩ ተገደዋል፡፡

በጣም የሚገርመው በነዚህና በሌሎችም ውትብትብ ችግሮች በተዘፈቀች አገር ውስጥ የኢሕአዴግ መንግስት በአሁኑ ጊዜ ተጠምዶ ያለው አገሪቱ አደገች አዲስ አበባ ውስጥ ፎቆች ተሰሩ የሚል የሞኝ ጨዋታ ላይ ነው፡፡ አንዳንዴ በጣም የሚያሳፍረው መንግስት ስለ አገሪቱ ማደግ መስካሪ ከውጭ ሲያመጣ ነው፡፡ የሚደንቀው ደግሞ እነሱም የአዲስ አበባን ፎቆች ቆጥረው ሲሄዱ ነው፡፡ ምስክር ካስፈለገ እዚህ እኛ አለን አይደል እንዴ፤ ኑሮውን ከነግሳንግሱ እየኖርነው ያለነው፡፡ አንድ አስተዋይ እናት በአደንቆሪው ቴሌቪዥን ባንድ ወቅት ስለአገሪቱ እድገት ተጠይቀው የተናገሩት ትልቅ መልስ የሚሆን ይመስለኛል - "እንዴ!... ፎቅ ማለት እድገት ማለት ነው እንዴ!..." ብለው መልሰው ጋዜጠኛውን ጠይቀውታል፡፡ ስለዚህ ስለ አገሪቱ እድገት ምስክር ካስፈለገ ከኛ በላይ ማንም አይኖርም ፤ እኛ አለን አይደል እንዴ እንድ ሺህ ብር በማትሞላ የወር ገቢ ከስድስት ቤተሰብ በላይ የምንቀልብ፤ ልጆቻችንን ቁርስና ምሳ በተራ (አንዱ ቁርስ ላይ አንዱ ምሳ ላይ) የምንመግብ፤ ቤት መከራየት ከብዶን ቤተሰብ ላይ ተጣብቀን በአንድ ትንሽ ክፍል ቤት ውስጥ ከአምስት ሳናንስ ተደራርበን የምንተኛ፤ እኛ አለን አይደል እንዴ ስራአጡ ውንድማችን በኬንያ፤ በሱዳን ልጥፋ እያለ ናላችንን የሚያዞረን፡ እህታችን አረብ አገር ሆና «ቀጣሪዎቼ አላኖሩኝም» ባለች ቁጥር ሞተች እያልን የምንሳቀቅ፡፡ ገጠር ያሉት ዘመዶቻችን ማዳበሪያ እና ምርጥ ዘር መግዣ ላኩ እያሉ የሚወተውቱን ሌላው የኑሯችን ውጋት ነው፡፡ ስለዚህ ስለኢኮኖሚው ምስክር ካስፈለገ እኛ እንበቃለን፡፡

ላጠቃልና ዋናው ቁም ነገሩ ድህንት ፤ ርሀብ፤ ስራ አጥነት፤ የቤት እጦት ችግሮች የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዋና መገለጫ ሆነዋል፡፡ የነዚህ ችግሮች መንሰዔው ደግሞ አገሪቱን በማስተዳደር ላይ ያለው መንግስት የአመራር ብቃትና ተጠያቂነት ማጣት ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት "የአደግን" ዝማሬውን ቢተወውና፤ ልማት የሌለው ልማታዊ ንግግሩን ትቶ ፤ ከምር እዚች አገር ላይ እንዴት ሁሉንም በእኩል ያካተተ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እንደሚቻል ቢሰራ መልካም ነው፡፡ይህንን ለማድረግ ፖለቲካው ላይ ልጥፍ ብሎ እድሜ ልክ እገሪቱን እንዴት እንደሚገዛ ብቻ ማለሙን አቁሞ አገሪቱ ውስጥ ጤናማ የፖለቲካ ስርዓት እንዲዘረጋ ቢያበረታታ፤ ድህነትን እና ረሀብን ታሪክ የሚያደርግ ነፃ ድርጅቶችንና ማህበረሰብ መፍጠር ይቻላል፡፡

## ምህዳሩ ጠቦል ፤ ሰፍቷል ! !

ከምርጫ 97 በኋላ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል ፤ ሰፍቷል ፤ ባለበት ነው ፤ ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማስከበር አስፈላጊ የህግ ማዕቀፎች ወጥተዋል ፡፡ የሚሉ ሐሳቦች ከግራና ቀኝ ሲንሸራሸሩ መስማት የተለመደ ነው ፡፡ "ተቃዋሚዎችንና ነፃውን ሚዲያ በአስተዳደራዊ ሁኔታ እንታገላቸዋለን" በማለት አቶ በረከት ከተናገሩ በኋላ አገሪቱ ሁሉ አዋጅ በአዋጅ ሆነ ፡፡

የተሻሻለው የፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ፣ የብዙኃን መገናኛ አዋጅ ፤ የበጐ አድራጐት አዋጅ ፣ የፀረ ሽብር አዋጅ ፣ የተባሉ የአፈና አዋጆች ተሸጎደጎዱ ፡፡ በሌላ በኩል ይህንን የሚያስፈጽም ፍ/ቤት ዐቃቢ ህግ ፣ ፖሊስ ፣ ደህንነት ተጠናክሮ ተደራጀ ፡፡ ሥራቸውን እያከናወኑ ናቸው ፡፡

እነ ጀነራል ተፈራ ማሞ በሽብርተኝነት ተከሰሱ እና ፍ/ቤት ቀረቡ ፡፡ የፍርድ ሂደቱን ለመከታተል የሚመጣው ታዳሚ በርካታ ስለሆነ ጉዳዩን ይመለከተው የነበረው ችሎት ፍትህ አዳራሽ ይሰየም ነበር ፡፡ ፍትህ አዳራሽ በግምት 300 ሰው ይይዛል ፡፡ ቀድሞ የመጣ ቦታ ይሰጠዋል ፡፡ ሲሞላ ፖሊሶች በትህትና ሞልቷል ይላሉ ፡፡ አዳራሽ የመግባት ዕድል ያልገጠመዉ ጉዳዩን ውጪ ሆኖ ይከታተላል ፡፡ እነ ኤልያስ ክፍሌ ሲከሰሱ ጉዳዩን የሚከታተለው ችሎት በአብዛኛው ሙስና በሚባለው አዳራሽ ይሰየም ነበር ፡፡ ይህ አዳራሽ በግምት 100 ሰው ይይዛል ፡፡ አሁንም እንደዚሁ የገባ ገባ ያልገባ ዉጭ ሆኖ ይከታተል ፡፡ እነ አንዱዓለም አራጌ ሲከሰሱ ጉዳዩን የያዘው ችሎት ዐቃቢ ህግ ማሰረጃዎቹን አቅርቦ እስካጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ችሎቱ በሙሉ ሙሰና አዳራሽ እየተሰየመ ይመለከተው ነበር ፡፡

ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ችሎቱ በግምት 25 ሰው በሚይዝ ክፍል ውስጥ እየተሰየመ እየተመለከተው ነው ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ችሎቱ ከመሰየሙ በፊት ደህንነቶችና ሲቪል ለባሽ የሚባሉ ፖሊሶች ቀድመው ቦታውን ስለሚይዙት ጉዳዩን ለመከታተል የሚመጡ ቤተሰብና ጋዜጠኞች በፖሊስ የሚደረገውን ተደርገው ይባረራሉ ፡፡ እውነቱ ይህ ነው ፡፡ እኔ ስለ ፖለቲካው አላወራሁም ፡፡ ምህዳሩ ጠቧል ሰፍቷል ለሚለው ክርክር መልሱ ምን ሊሆን ይችላል?

## ባንዲራና መዘዙ

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አምስት ሺ ዘመን እንዳለው በአንድ ወቅት አንድ ጽሑፍ ማንበቤን አስታውሳለሁ ፡፡ ምን ያህል እውነት ነው የሚለውን ለታሪክ ባለሞያዎች ልተወው ፡፡ በቅርቡ በቀድሞ ሰንደቅዓላማ ላይ የወቅቱ የኢህአዴግ መንግስት ዓርማ የባንዲራው አካል እንዲሆን በአዋጅ በመጽደቁ ወደድንም ጠላንም ብናምንበትም ባናምንበትም ኮከብ ያለውን ሰንደቅዓላማ እንድንቀበለው ተገደናል ፡፡ ከኢህአዴግ መንግሥት በኋላስ ምን ሊሆን ይችል ይሆን? የምናየው ይሆናል ፡፡

ይህንን ሁሉም ስለሚውቀው አዲስ ነገር አይደለም ፡፡ ለእኔ የገረመኝ የክልል መንግስታት ሰንደቅዓላማና የክልሉ ገዢው ፓርቲ ዓርማ አንድ መሆን ነው ፡፡ ኦሮሚያን ስንመለከት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅዓላማ አለው ፡፡ ገዢው ፓርቲ ኦህዴድ ዓርማ አለው ፡፡ ትግራይ ብንሄድ የህወሓት ዓርማና የክልሉ መንግስት ሰንደቅዓላማ ሆኖ ተሰይሟል ፡፡ አማራ ብንሄድ የብአዴን ዓርማ የክልሉ ሰንደቅዓላማ ነው ፡፡ ከኦሮሚያ በስተቀር ሁሉም አንድ ነው ፡፡

የእውነት ምርጫ ተደረጐ የክልሉ ገዢ ፓርቲ ባይመረጥ የተመረጠው አዲሱ ፓርቲ ያለፈውን ፓርቲ ዓርማ እንደ ክልሉ ሰንደቅዓላማ ተቀብሎ ሊጠቀምበት ነው? ወይስ አዲስ ሰንደቅዓላማ ሊያወጣ ነው? በባንዲራ ስም ምን እየተሠራ ነው? ወይ የባንዲራ መዘዝ ! !

# አደብና ወደብ ያሳጣን መንግሥት ሲኩራራ ይገርመኛል

ሰለሞን ስዩም

በተለያዩ ዘርፎች የተለያዩ አመለካከቶች ይኖሩናል:: ለፃድቃን ያለንን አመለካከት ለማንም ተራ ሰው መያዝ አንችልም:: አሊያም ለቤተ ክርስቲያን ያለንን ክብር ለመንግሥት ላይኖረን ይችላል:: እንዴትስ ሊኖረን ይችላል? መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተለያየ አለማትን ለማዉረስ የሚሰሩ ናቸዉ:: መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተለያየ አለማትን ለማየት የሚፈልጉ ተቋማት ናቸው:: ቤተ ክርስቲያን ያላትን ይዛ የምትቆይ ዋጋዋም፣ ድርሻዋም የማይለዋወጥ ናት:: ለመንግሥት ይህ ይሆናል ብዬ አላስብም:: ለምሳሌ የአሁኑ መንግሥት ከቀድሞው የመሻል ተፈጥሯዊ ግዴታ አለበት:: ኢ-መደበኛ በሆነ አኳኋን ምንም ቢሆን የምንሄደው ወደ ፊት ነው ይባላል:: በመሆኑም ኢህአዴግ ተነስቶ "በትራንስፖርቱ ዘርፍ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ከነበረው በ1000% አሻሽዬዋለሁ" ቢል ቁጥሩ ጉዳይ ሆኖ መነሳት የለበትም:: መነሳት ያለበት "በዘመኑ ትራንስፖርት መች ነበር?" የሚል ጥያቄ ነው:: ይህን ጥያቄ ያልጠየቀ ሰው በቀጥታ የኢህአዴግ ወጥመድ ውስጥ መውደቁ አይቀሬ ነው:: ምክንያቱም የኢህአዴግ ትልቁ ችሎታ "የቁጥር መረጃ መጋገር" ነውና:: በነገራችን ላይ የማርክ ተወይንን ስራዎች ከ "Adventure of Huckleberry finn" ጀምሮ ለማንበብ ሞክሬያለሁ:: ነገር ግን ዛሬም ድረስ ቀልቤን የገዛው ምሳሌ የሌለኝ ይመስል ሁሌ የማነሳት "Damned, lies and statistics" የምትለውን ዓ.ነገሩን ነው:: በርግጥ "የኢህአዴግን ቁጥር ያመነ ጉም የዘገነ" አንድ ናቸው ማለት እችል ነበር:: ነገር ግን ይህኛው ፍሬ ነገሩን ‹‹አለመጨበጥ›› ብቻ አድርጎ ያስቀረዋል:: የማርክ ትዌይን አባባል ግን "በቁጥር ጫወታ አሸናፊ የለም" ከሚለውም በላይ ነው:: በትዌይን አባባል ያሉት ውሸቶች ሦስት ሲሆኑ ከነዚህ አንዱ ቁጥር /statistics/ ነው:: እናላችሁ 11.2 በመቶ እያደጉ መኖር ከዚህ የተለየ ትርጉም የለውም:: ደግሞ አደግን እንበል፣ ኑሮ ተወዶም፣ ህይወት ተወድዳም:: ግን እኮ የምናድገው አንዲት የአሜሪካ የዞን ከተማ ከምታድገው ኢኮኖሚ በ11% እና ከዚያ በታች በሚያንስ ድምር ነው:: መቼም የህይወታችንን መሻሻል አለመሻሻል ለመገንዘብ የግድ ኢኮኖምክስ መማር አለባቸው የሚል እምነት የያዘዉ የአቶ መለስ መንግሥት "ኑሮ የተወደደው፤ የዋጋ ንረቱ የጦዘው በምናስመዘግበው ተምዘግዛጊ የኢኮኖሚ እድገት ነው" ይሉናል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተለይ የነኩት ሁሉ ወርቅ እንደሚሆን ሁሉ አሉታዊ የተባሉ ነገሮች በገጠሙ ቁጥር ዕድል አድርገው ያቀርቡታል:: ባለፉት 21 ዓመታት ሁለት ተመሳሳይ ነገሮችን አስተውዬባቸዋለሁ:: አንድኛ ሁሉንም ነገር ወርቅ አድርጎ ማቅረቡ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሁሌም የሚገኙበት የጠቅላይነት መንበራቸው ነው::

የኑሮ ውድነት ከተነሳ ዘንዳ አንድ ነገር ልመርቅ:: አንዲት ባለ ግሮሰሪ በአስር ብር ለገዛችው ሳር እንኳን ለቤቷ፣ ለጀበናዋ ት ረከቦትም የማትሆን ነበረች:: ታዲያ ይህን ያየ እንድ ተጠቃሚ "ወገን ይሄ ደግሞ ምን ቢሆን ነው ዋጋዉ እንዲህ የተሰቀለው? የተመረተው በኛው ሀገር ነው ግን?" ሲል ጠይቋል::

አቶ መለስ መንግሥት በትልቁ የሚከሰስበት አንዱ ጉዳይ ብሔራዊ/ሀገራዊ አንድነትንና የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ማመጣጠን ያለመቻሉ ነው:: የአቶ መለስ ቡድን በአመፂ አብዮተኝነት ስልጣን የጨበጠ በመሆኑ ነገሮችን ከባዶ መጀመር መፈለጉ ያስማማል:: ነገር ግን እጅግ በበዛ መልኩ የቀድሞውን የብሔራዊ አንድነት መንፈስ በብሔር ብሔረሰቦች መብት ለመገዳደር ስል ሌላኛውን ጫፍ ያዘ:: ይህን ባነሳሁ መጠን በ1960ዎቹ እጅግ ተወዳጅ የነበረውን ጨቋኝ ተጨቋኝ /Dependency theory/ ማውራት ይቀናኛል:: አብዮተኞቹ የዚህን ፅንሰ ሀሳብ አንድ አቅጣጫ በመውሰድ ኤርትራ እንድትገነጠል፣ ሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎችም የመገንጠያ የህግ ድጋፍ የሚሆን ህገ መንግሥት በመስራት ደመደሙ:: የሰሞኑ የደቡብ ክልል አሉታዊ ብሔርተኝነትም ከዚህ መች ይዘላል:: የአንድ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የሆኑትን አቶ ሽፈራዉ ሽጉጤን ‹‹አማሮች ወደ ሀገራችሁ›› ያሰኛቸዉ ምን ሆኖ ነዉ::

ዛሬም ድረስ የአሰብ ጉዳይ እንደ አዲስ ያሳስበኛል:: በርግጥ የመለስ ዜናዊ መንግሥት ‹‹የአሰብ ናፋቂ›› ሊለኛ ይችላል:: ሆኖም ዛሬም አሰብ ሄጄ መዝናናት ያምረኛል:: ሞምባሳ፣ አሊያም ሲሸልስ አሊያም ሲንጋፖር ለምን እንደማይናፍቁኝ አላውቅም:: አዎን የመለስ መንግሥት በብሉይ ትንተና ቢፈረጀኝና ቢከሰኝም አሰብን ከነ የአሰብ ራስ ገዝ መሬቷ እናፍቃታለሁ:: ይህ ለጅቡቲ በቀን ከ300 ሚሊዮን ዶላር በላይ በመክፈላችንም አይደለም:: አሰብ ከነ ግዛቷ የኢትዮጵያ መሆኗን ከልቡናዬ በተጨማሪ ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያምን አንብቤ አሰብን ያሳጣን ህወሓት እንጂ ህግ ያለመሆኑን፣ ተፈጥሮ ያለመሆኗን በማረጋገጤ ነው:: በነገራችን ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሚያውቋቸው ሸቀጦች በቀን 300 ሚለዮን የሚያስወጣው ወደብ ብቻ ነው:: ወደብ ከመግቢያ መውጪያነቱ በተጨማሪ የያዘውን የደህንነት ጥቅም መዘርዘር አያስፈልገኝም::

አቶ ስብሃት ነጋ የኤርትራ /አሰብ ጉዳይ ከተነሳ ደግሞ ደደቢት እንደሚገኙ አቋም መያዛቸው ይነገራል:: በአጠቃላይ ህወሓት ውስጥ የመለስ ቡድን የሚባለው "ኤርትራዊነትን" በማበረታታትና በማቀንቀን ይታወቃል:: በአጠቃላይ ‹‹በመቀነስ›› የሚኩራራ መንግሥት አለን:: አቶ መለስ ደመሩ ከተባለ ‹‹ዜሮ ሰም ጌም›› ከማለት አይዘሉም:: መቀነስ ቢያቆሙ ከዜሮ የሚበልጥ ነገር አይደምሩም:: በተቃራኒዉ አጤ ምኒልክ በማስፋታቸዉ/

በመደመራቸዉ ሠይጣን ተደርገው ይሳላሉ::

አመራር እንደሚወስን መረዳት ይቻላል:: ‹‹አመራር እዉቀቱ ብቻ ሳይሆን መንፈሱም ይፈለጋል›› ይላሉ የዘረፉ ባለሙያዎች:: መሪዎቻችን ለማህበራዊና ስነ ልቡናዊ ብልፅግና ለምን እንደማይጨነቁ ለማሰብ እሞክራለሁ:: ዋናው ነገር በዚህ ዘርፍ ብዙም ያልተሳካላቸው በመሆናቸው ለኛም ጭንቅ የለባቸውም:: ዴሞክራሲ፣ መልካም ስነ ምግባር፣ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት አልተሳኩም:: ህወሓት/ኢህአዴግ በዚህ በኩል ወድቋል:: በመሆኑም ተቃራኒው ተሳክቷል:: "ስለ መፃህፍት" የተባለ ፕሮግራም ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ ቀርቦ ነበር:: አንዱ ታዳሚ ‹‹ለተማሪዎቻችን ምን የንባብ ባህል ሰጠንና መልካም አንባቢ እንጠብቃለን" ሲል ለጠየቀው ጥያቄ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ የራሳቸውን አስተያየት ሲሰጡ "9ኛ ክፍል ስማር ከተሰጡኝ 13 መፃህፍት አንዱ ዌብስተርስ ዲክሽነሪ ነበር፤ የክፍል ውስጡን በአንድ በኩል የመፃህፍቱን በሌላ ትይዩ እያፃፍኩ ነው የማመሳክረው፤ በመሆኑም አጠሬራ ይገኜ ለፈተና ክፍል አልገባም ነበር" ብለዋል:: ዶ/ር ፈቃደ በተቃራኒው ቸልታችን ትክክለኛውን ፍሬ ማፍራቱን ተናግረው ነበር::

በዲሽ ባመጣነው ነገር "ማንቼ አርሴን" አፈራን:: ሀይላቾንን ስራፊት በማድረግ በጫትና በተለያዩ ሱሶች የናወዘ ትውልድ በበቂ ሁኔታ ማፍራታችን ይታወቃል:: ጫት የተስፋ ማጣት፣ በተፈጥሯዊው በራስ ያለመተማመን፣ እንዲሁም የውሸት ሽግግ መሆኑ ይታወቃል:: እንጠጣለን፣ አንዳንድ ሰዎች ወጣቱ የጫት ትዉልድ ሆኗል ይላሉ:: በኤድስ እንሞታለን እንዘርፋለን:: ቅብዝብዝ ሆነን ምን አደብ አለን፤ አደብ የሚገዛዉ የተረጋጋ ትዉልድ ነዉ::

በአጠቃላይ አደብም አሰብም ያሳጣን መንግሥት ግን ይኩራራል::

## የአዋቂ አጥፊው ......

ከገፅ 15 የዞረ

ባንክን ወደ ገንዘብ ማተሚያና አሮጌ ብር ማከማቻ ድረጅት ቀየራችሁት እንዴ? ለዚህማ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ይበቃ ነበር" ይላሉ! የሚገርመው ነገር፣አቶ ምናሴ ለማ ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው ቀደም ብሎ አቶ ተክለ ወልድ ቢሮ ብቅ እያሉ ይጫወቱ ነበር፤ ምን እንደመከሯቸው አቶ ተክለወልድ ቢነግሩን ጥሩ ነበር!

በአሁኑ ጊዜ አቶ ተክለወልድ በታማኝነት ያገለገሏቸው ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የከዷቸው ይመስላል:: አቶ መለስ ለዋጋ ንረት አንደኛው መንስዔ ብሔራዊ ባንክ ለመንግሥታት የሚያበድረው ገንዘብ መሆኑን በአደባባይ (በፓርላማቸው) አምነዋል! እሳቸው ትዕዛዝ የተበተነውን ገንዘብ በአቶ ተክለወልድ ላይ አላከኩ! አቶ ተክለወልድ "የጨዳ ፍየል" (Scapegoat) ሆነዋል ማለት ነው:: አቶ ተክለወልድ ግን ሙያቸው ከሚጠይቀው ሥነ ምግባር ውጪ እያወቁ ለጥቅም ሲሉ ያደረጉት ስለሆነ፣የጭዳ ፍየል መሆኑ አይበዛባቸውም:: ለነገሩ፣እሳቸውም የሚመጣውን መዘዝ አውቀው፣ድምፃቸውን አጥፍተው ሊሾልኩ አስበው ነበር:: ለኮሜሳ ባንክ /የአፍሪካ ባንክ/ ገዥነት ተወዳድረው ሳይሣካላቸው እንደቀረ ወሬ ሰምቻለሁ:: መረጃዬ ትክክል ካልሆነ ለመታረም ዝግጁ ነኝ:: ለቦታው ሙያዊ ዕውቀቱ አያንሳቸውም ነበር፤ ግን በኢትዮጵያ ያደረሱትን የገንዘብ ፖሊሲ መመሰቃቀል ለተገነዘበ፣በውድድሩ መውደቃቸው አያስገርምም:: የሚገርመዉ፣ከሳቸው በልምድ ያነሰ ግን የላቀ ዓለም አቀፋዊ የፋይናንስ ዕውቀት ያለው ወጣት ኢትዮጵያዊ ነው ያሸነፋቸው! እሳቸው በግል ቢሸነፉም ኢትዮጵያ ግን አሸንፋለች! ድሉን የተቀዳጀው የአምባሳደር ይልማ ታደሰ ልጅ መሆኑን ተረድቼአለሁ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣አቶ ተክለወልድ ሰሞኑን በአቶ መለስ ፓርላማ ቀርበው መግለጫ ሰጥተዋል:: ቀጣፊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ መጋቢት 14 ቀን 2004 ባወጣው እትሙ እንዲህ ሲል ዘግቧል፤

"የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባለፉት ሰባት ወራት የተረጋጋ የዋጋና የውጭ ምንዛሪ ተመን እንዲኖር የሚያደርጉ ተግባራት ማከናወኑን አስታወቀ::"

እንግዲህ፣እግዚአብሔር ያሳያችሁ! የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን ለአንድ የአሜሪካ ዶላር ወደ 18 ብር እያሻቀበ ባለበት እና በራሳቸው ስታትስቲክስ መሠረት የዋጋ ንረት ከ32 በመቶ ወደ 36 በመቶ በወጣበት ሁኔታ፣ የዚህ ዓይነት ቅጥፈት ምን ይባላል?! ግን ከአዲስ ዘመን ድሮስ ምን ይጠበቃል? የባለ ብሩህ አእምሮ ባለፀጋና የዴሞክራሲ ታጋይ የሆነው አንዱዓለም አራጌ ያለ አንዳች አሳማኝ ምክንያት በግፍ ዘብጥያ እንዲወርድ ከተደረገ በኋላ፣አዲስ ዘመን በዚሁ እትሙ ላይ እንዲህ ብሎ ዘግቧል፤

"አሁንም አቶ አንዱዓለም የፍርድ ቤቱን ቀና አካሄድና የችሎቱን ነፃነትየሚጋፋ የአደባባይ ንግግር እያደረጉና በፊርማቸው የተረጋገጠ ነው የተባለለትን ጽሑፍ በጋዜጣ እያወጡ ፍርድ ቤቱ ዝምታን መምረጥ ያለበት አይመስለኝም::"

አዲስ ዘመኖች፣አንዱዓለም አራጌ ላይ ከዚህ የበለጠ ግፍ ምን ይፈፀምበት ነው የምትሉት? በግፍ ታሰረ፣በግፍ ተደበደበ! ይገደል ነው የምትሉት? እሱ ቢሞት ሺ አንዱዓለም አራጌዎች አሉ! ወደፊትም ይፈጠራሉ! በበኩሌ፣በዓለም እንደ አዲስ ዘመን ገጽ ሦስት ቀጣፊ የፈጠራ ድርሰት ያለ አይመስለኝም! ወንድሜ ወደተነሳሁበት ጉዳይ ልመለስ:: እኔም አላርፍ፤ ጓደኛዬ በተለይ የአዲስ ዘመን ገጽ ሦስትን ካነበብህ የደም ግፊት ባይኖርብህ እንኳን፣በስትሮክ (stroke) ልትሞት ትችላለህ ብሎኝ ነበር! አዲስ ዘመኖች የሰው ሕይወት ለማጥፋት የሚጠቀሙበት የግድያ ስልት መሆኑ ነው መሰለኝ!

እናም፣በአሁኑ ጊዜ አቶ ተክለወልድ ያሉበት ሁኔታ የሚያስቀና አይመስለኝም:: ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከድተዋቸው በአደባባይ ስለ አጋለጧቸው ከፍተኛ ቅሬታ እንዳደረባቸው ይገመታል:: የሚገርመው ነገር ከእንግዲህ ለአቶ መለስ ብድር መስጠት አቁሜአለሁ በአሉበት አንደበታቸው፣ ወደ 43 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የመንግሥት ግምጃ ቤት ሰነዶች ለባንኮች ሰጭአለሁ ማለታቸው ነው:: በዋጋ ንረት ላይ ባላቸው ተፅዕኖ፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመንግሥት የሚያበድሯቸው ብድሮች ብዙም ልዩነት የላቸውም:: ብሔራዊ ባንክ የሚያበድረው ብድር ተፅዕኖ መቶ በመቶ ቢሆን፣የንግድ ባንክ ተፅዕኖ ከሰማኒያ አምስት በመቶ አያንስም!

አቶ ተክለወልድ እያወቁ በዋጋ ንረት የኢትዮጵያን ሕዝብ አስርበዋል:: አብዛኛዎቹ የመንግሥት ሠራተኞች የሚያገኙት ደመወዝ ከምግብ እና ከቤት ኪራይ ሊያልፍ ያልቻለው እሳቸው ባመጡት የዋጋ ንረት ነው! መምህራን "አሁንስ በቃ! ቀኑን ሙሉ የምንፈጋው ለዚች ደመወዝ ነው እንዴ?" ብለው አድማ እየመቱ ነው! ስልሳ እና ሰባ ብር ጭማሪ ብሎ መስጠት እውነትም ስድብ ነው!በዚህ በዓቢይ ፆም አንድ ዓሣ ለመብላት 78 ብር ያስፈልጋል፤ ጫማ ለማስጠረግ ደግሞ ሦስት ብር ይጠይቃል! የሀገር ውስጥ ጫማ ለመግዛት እስከ 600 ብር ያስፈልጋል! ስለ ዋጋ ንረት ስንቱ ተወርቶ፣ስንቱ ይቀራል? በበኩሌ በጣም የሚያሳዝነኝ፣ አቶ ተክለወልድ፣ "እንዳውመንት" ተብዬዎች ያለአግባብ የወሰዱትን 2.5 ቢሊዮን ብር የባንክ ብድር ያለአግባብ ሲዘረዝላቸው ትንፍሽ አለማለታቸው ነው! ዕዳው ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ተዛውሯል! በሌላ አገላለፅ፣ኤፈርት የበላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እየከፈለ ነው! የቀድሞ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሠራተኛ የነበረና አሁን በጡረታ ላይ ያለ ጓደኛዬ ስለ አቶ ተክለወልድ የተናገረው ግን ከዚህም በባሰ አስደንግጦኛል! "አቶ ተክለወልድ ከድርቅ ቀጥሎ ሕዝብን ያስራቡ ባለሥልጣን ናቸው!" ነበር ያለኝ! ቀጣፊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ለዚህም መልስ እንደሚኖረው እርግጠኛ ነኝ:: "ድርቅ አለ፤ረሀብ ግን የለም" እንደሚለው ሁሉ፣ "የዋጋ ንረት አለ፤ግን ረሀብ የለም" ብሎ የሐሰት ፕሮፖጋንዳ መፈክር እንደሚለቅ አልጠራጠርም! ግን አቶ መለስ ራሳቸውን ከተጠያቂነት ለማዳን ሲሉ ይጨክነባቸው ይሆን? የጭዳ ፍየል ከመሆን ያውጣን! አሜን ያውጣን!

# የሰሞኑ የመምህራን የሥራ ማቆም አድማና የኢህአዴግ የፍርሃት ሩጫ



ከመ/ር ቀለሙ ሁነኛው
kelemhun@yahoo.om

መምህራን መንግሥት በደመወዝ እርከን ላይ ያደረገውን አሳፋሪ ማሻሻያ በመቃወም የአቋም መግለጫ ከማስተላለፍ ባሻገር በብዙ ት/ቤቶች የሥራ ማቆም አድማ ማድረጋቸው ይታወቃል፡፡ ትግሉን በተቀናጀ መልኩ የሚመራ ኃይል ባለመኖሩ እንቅስቃሴው ባጭሩ ቢቀጭም ለህወሓት /ኢህአዴግ መሪዎች ግን ብርቱ የማስጠንቀቂያ ደወልን አስተጋብቷል፡፡ የኢህአዴግ አባል የሆኑ መምህራን ጭምር የትግሉ ግንባር ቀደም ተዋናይ መሆናቸው የኢህአዴግን ርቃን መቅረት የሚመሰክር ነው፡፡

በድሬደዋው ጉባኤ ላይ እንደጀግና ፎክሮና አቅራርቶ ፅኑ የአቋም መግለጫ ያስተላለፈውንና በየት/ቤቱ መምህራንን ለትግል ያነሳሳው ኢህአዴግ ሠራሹ መምህራን ማህበር በኢህአዴግ ሹማምንት ተራ ጩኸት ተፍረክርኮ በቀላሉ እጁን ሰጠ፤ ጥቂት መምህራንን ለችግር አጋፍጦ ዘወር አለ፡፡ በእርግጥ ማህበሩ በኢህአዴግ ተጠፍጥፎ የተሰራ የእጅ ሥራ በመሆኑ ገና ከጅምሩ ትግሉን እንደማያስቀጥል ይታወቅ ነበር፡፡ ይሄ ከመምህራን የተሰወረ አይደለም፡፡ ከዝንብ ማር አይጠበቅምና በቀጣይ የማህበሩ ሕልውናም ሆነ ለአባላቱ አንዳችም ፋይዳ የለውም፡፡ በጎንደርና በአዲስ አበባ የተደረጉትን የሥራ ማቆም አድማዎችን መርታችኋል በሚል ጥቂት መምህራን ከሥራቸው እንዲሰናበቱ ተድርጓል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ማህበሩ ምን እያደረገ እንዳለ በውል ባይታወቅም የኢህአዴግ ሹማምንት ለአፍታ ቆም ብለው ቢያስተውሉ ይበጃቸዋል፡፡ ከመምህራን ጋር እልህ መጋባት አደጋው የከፋ ነው፡፡ ኢህአዴግ ቢያምንም ባያምንም መምህር የለውጥ ሐዋሪያ ነው፡፡ እልፍ አእላፍ ደቀመዛሙርትም እንዳሉት ማጤን ይገባል፡፡

በተለይም በአዲስ አበባ በሚገኙ አያሌ ት/ቤቶች መምህራን የወሰዷቸው ርምጃዎች ከቢሮአቸው ተሽከርካሪ ወንበሮች የማይነሱ የኢህአዴግ ሹመኞችን ሲያሯሩጣቸው ከርሟል፡፡ ለትምህርት ጥራትና ስርጭት ይህን ያህል ቢሮጡ ኖሮ ምንኛ ተስፋን የሰነቀን ትውልድ ባፈራን? በሥልጣን ዘመናቸው አንድም ቀን የት/ቤቶችን ደጃፍ ረግጠው የማያውቁ ሹማምንት የመምህራንን የሥራ ማቆም አድማ ለማክሸፍ ሲቅበዘበዙ ላስተዋለ ኢህአዴግ የኮሽታ ድምፅ እንኳን የምታስበረግገው ደረጃ ላይ መድረሱን ይገነዘባል፡፡ ይሄ ደግሞ በሕዝብ ዘንድ ለመጠላቱ አንዱ ማረጋገጫ ነው፤ ማስተዋል የሚችል ከሆነ፡፡

የአዲስ አበባ የኢህአዴግ ሹመኞች በየት/ቤቱ እየተሯሯጡ መምህራንን ለማነጋገር በሞከሩበት መድረክ ሁሉ ተግባራቸው ማስፈራራት ነበር፡፡ «ከሥራ እናባርራችኋለን! የተለየ የፖለቲካ አጀንዳ እንደ አላችሁ ደርሰንበታል! ይሄ ድርጊት አመፅን ለማነሳሳት የታቀደ ነው፡፡ እንቅስቃሴያችሁ ከአሸባሪዎች ተግባር ተነጥሎ አይታይም» የሚሉ ዛቻዎችን አዝንበዋል፡፡ በጣም የሚያስገርመው ኢህአዴግ የዜጎችን ተራብን ተጠማን፣ ታረዝን ስለዚህ የደመወዝ ጭማሪ ይደረግልንን ድምፅ (እንቅስቃሴ) ሕገ መንግስቱን በመጣስ በአሸባሪነት ለመፈረጅ የሚቃጣው አፋኝ መንግስት ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 42/ለ ላይ የተጠቀሰውን ሥራ የማቆም አድማ የማድረግን ዴሞክራሲያዊ መብት በራሱ ጊዜ ሲሽረው ታይቷል፡፡ ዜጎች መብታቸውን ለማስከበር ሥራ የማቆም አድማ በማድረግ መንግስትን ማስጨነቅ የ21ኛው ክ/ዘመን ሥልጣኔ (Globalization) የወለደው ክስተት ነው፡፡ ባደጉ አገራት የሚገኙ ዜጎች "በውሃ ቀጠነ" ሰበብ ሥራ በማቆም ተቃውሞአቸውን በሰላማዊ መንገድ ሲገልፁ እያየን በኛ አገር ብቻ ወንጀል የሚሆንበት ምክንያት (ያውም በሕገ መንግስቱ ላይ የሠፈረ መብት ሆኖ) በእጅጉ ያሳዝናል፡፡ ዛሬ በኢትዮጵያ በሚያስደንቅ ሁኔታ ራበኝም ሽብር ሆኗል፡፡

በሰሞኑ የመምህራን ሥራ ማቆም አድማ ምክንያት በየት/ቤቱ የተገኙ ባለስልጣናት ቋንቋ "መምህራን የሥራ ማቆም አድማ እንደያደርጉ የሚደነግግ ህግ አለ" ሲሉ የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ከፍተኛ የህይወት ዋጋ የተከፈለበት እንደሆነ ነጋ ጠባ እንደ ፈጣሪ ቃል የሚሰብኩንን ሕገ መንግስት በአደባባይ ጥሰውታል፡፡ ለምንድነው መምህራን የሥራ ማቆም አድማ የማያደርጉት? የትኛው አንቀፅ ላይ ነው ለመምህራን የተለየ ድንጋጌ የተደረገው? እነዚህ ሹመኞች ሲናገሩ ለድሃው የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች (ተማሪዎች) ከማሰብ የመነጨ አድርገው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ አስበው ሞተዋል! በጣም የሚያስገርመው የኢህአዴግ ሹመኞች ለትምህርት ክ/ጊዜ ብክነት ተቆርቋሪ ለመምሰል መሞከራቸው ነው፡፡ እነ እሱ በፈለጋቸው ጊዜ የዓመቱ ትምህርት ሳይጠናቀቅ ት/ቤቶች እንዲዘጉ መመሪያ እየሠጡ ስለመሆኑ ማንም የሚያውቀው ነው፡፡ በ2003 ዓ.ም መምህራን ወደ ስልጠና ይገባሉ በሚል ሰበብ በዓመቱ ውስጥ መሰጠት የሚገባው የትምህርት ጊዜ ሳይሸፈን ቀድሞ እንዲጠናቀቅ በመደረጉ ቢያንስ ከወር በላይ የትምህርት ቀናት ባክነዋል፡፡ ሥልጠናውም ለመምህራን ሳይሰጥ መቅረቱ ደግሞ ሌላው አሳዛኝ ክስተት ነበር፡፡ ብክነቱ በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ የ2004 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በትምህርት ሚ/ር ካላንደር መሠረት ት/ት መጀመር የሚገባው መስከረም 3 ቀን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ዳግመኛ የመምህራን ውይይት ይኖራል በሚል እስከ መስከረም 18/2004 ዓ.ም ሳይጀመር ቆየ፡፡ የመምህራን ስልጠና የተባለው ግን በሁለት ቀን ስብሰባ ነበር የተቋጨው፡፡ ከመስከረም 15/2004 ዓ.ም ጀምሮ የፕላዝማ ትምህርት ሥርጭት እንደሚጀመር ቢገለፅም ይሄው እስከ ዛሬ ድረስ ፕሮግራሙ ወጥ በሆነ መንገድ አልተጠናቀቀም፡፡ በአገሪቱ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 10% እንኳን አይሆኑም የፕላዝማን ሥርጭት የሚያገኙት መምህሩን ግን "መብትህን ለማስከበር የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ አትችሉም" ይሉታል፡፡ የሥነ ዜጋ ትምህርትን ለሚያስተምረውና የሕገ መንግስቱን አንቀፆች ጠንቅቆ ለሚያውቀው መምህር ሕገ መንግስቱን ከቢሮአቸው የመፅሐፍ መደርደሪያ ላይ አንስተውት የማያውቁ ሹመኞች ግን ሊያስተምሩት ይሞክራሉ፡፡ "ሚሊ ገረገሌ መታ ሆቄ!" ይላል የአገሬ አሮሞ፡፡ ትርጉሙ እግር ተመልሶ ራስን አከከ እንደማለት ነው፡፡

በአዲስ አበባ ለሁለት ሳምንታት ያህል የተከሰተውን ተቃውሞ ለማፈን የኢህአዴግ ግንባር ቀደም ካድሬዎችና በየደረጃው የተሾሙ ካቢኔዎች ያላንኳኩት በር አልነበረም፡፡ ከተማዋ በስብሰባ ብዛት ስትታመስ ነበር የከረመችው፡፡

ስብሰባ አንድ፡- ከኢህአዴግ አባል መምህራን ጋር ውይይት

ኢህአዴግ የሥራ ማቆም አድማው ከመከሰቱ በፊትም በየት/ቤቶች ይታዩ የነበሩ እንቅስቃሴዎችን ለማፈን አባል የሆኑ መምህራንን በተደጋጋሚ አወያይቷቸው ነበር፡፡ ውጤት ግን አላስገኘም፡፡ የደመወዝ ጥያቄው ከመምህራኑ ጋር የሚያስተሳስራቸው መሆኑን በይፋ ገልፀዋል፡፡ ከሥራ ማቆም አድማውና ከየት/ቤቱ በተላለፉ የአቋም መግለጫዎች ላይ እነኚህ የኢህአዴግ አባል መምህራን ግንባር ቀደም ታጋይ ነበሩ፡፡

ሁኔታው ያሰጋው ኢህአዴግ በመላው አዲስ አበባ በየክፍለ ከተሞቹ ስብሰባ ጠርቶ ባወያያቸው ወቅት ስብሰባዎችን ረግጠው እስከመውጣትና ከድርጅቱ አባልነት እስከ መልቀቅ ርምጃን ወስደዋል፡፡

ስብሰባ ሁለት፡- ከ "ቶፕ ቴን" (Top ten) ተማሪዎች ጋር ውይይት በየት/ቤቱ ከየክፍላቸው በውጤታቸው ከ1ኛ እስከ 10ኛ ደረጃ የወጡ በኢህአዴግ ቋንቋ (Top ten) ተማሪዎችን በመሰብሰብ ለማወያየት ተሞክሯል፡፡ በወቅቱ እንዲናገሩ የታዘዙትን ሸክፈው ወደ ስብሰባው የገቡት አወያይ ካድሬዎች መምህራንን በተማሪዎቻቸው ፊት ለመኮነን ሞከሩ፡፡ "መንግሥት አቅሙ በፈቀደው መጠን ያደረገላቸውን የደመወዝ ጭማሪ በመቃወም በየት/ቤቱ የሥራ ማቆም አድማ እያደረጉ ስለሆነ የድርጊታቸው ተባባሪ እንዳትሆኑ! የትምህርት ጊዜያችሁን በማባከን የናንተን የነገ ተስፋ ሊያጨልሙ ነውና አጥብቃችሁ አውግዟቸው . . . " በማለት ቃለ ኢህአዴግን ሲያሰሙ ተማሪዎች በከፍተኛ ጩኸት ተቃውሞአቸውን ገልፀዋል፡፡ በጣም የሚያስገርመው በመላው አዲስ አበባ የተሰበሰቡት ተማሪዎች ምላሽ ተገናኝተው የተማከሩ ያህል ነበር፡፡ "እኛን እጅግ ከምንወዳቸውና ከምናከብራቸው የቀለም አባቶችና እናቶች ጋር ልትነጣጥሉን አትሞክሩ! መምህራኑ የሥራ ማቆም አድማ ማድረጋቸውን እኛም እንደግፈዋለን፡፡ ውሏቸው ከእኛ ጋር ስለሆነ መራብ መጠማታቸውን ከኛ በላይ የሚያውቅ የለም፡፡ ደግሞም በእኛው ቤተሰቦች ግቢ እንደ አቅማቸው በተከራዩበት ክፍል ውስጥ የሚገፉትን አሳዛኝ ህይወት በቅርበት እያየነው ነው፡፡ መንግስት 60 እና 70 ብር ጨምሮ ያን ያህል በቴሌቪዥን ከሰማይ መና እንደ ወረደላቸው አድርጎ መለፈፉ እጅግ አሳፋሪ ነው፡፡ አባባሉ "የእከሊትን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም" እንዲሉ ነው መምህራን በወር ደመወዛቸው ኑሮን መቋቋም እየተሳናቸው እያየን እኛም ለአፍታ እንኳን ወደ ሙያው መሰማራት አንፈልግም፡፡ ስለዚህ የምትሉትን ሁሉ አንሰማችሁም፡፡ ይልቅ መንግስት ጥቂት ግለሰቦች በሙስና የሚቀራመቱትን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያስመለሰ ለመምህራኑ ጠቀም ያለ ደመወዝ ይክፈላቸው....." የተማሪዎቹ ንግግር በየደቂቃው በጭብጨባና በፉጨት የታጀበ ነበር፡፡ አብዛኞዎቹ ተማሪዎች አወያዮቹን እየተሳደቡ አዳራሹን ለቀው የወጡበት ሁኔታም ተከስቷል፡፡

ይሄ ለኢህአዴግ ትልቅ ውርደት ነው፡፡ ተማሪዎችን

ወደ 12 ዞሯል

# በአማራ ሕዝብ . . .

ከገፅ 5 የዞረ

ተከትሎ ስለ ብሔር ማቀንቀን ሲጀመር ልክ እንደ አሁኑ የአማራ ተወላጆች የጥቃት ኢላማ የሆኑበት ጊዜ ነበር፡፡ እነዚያ የአማራ ብሔር ላይ አነጣጥሮ የተፈፀሙ ጥቃቶች ያሳሰባቸው ኢትዮጵያውያን "የአማራው ሕዝብ ወኪል የለውም እንዴ!" የሚል ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ አንድ ማህበር እንደሚያስፈልገውም ታሰበበት፡፡ በዚህ ዙሪያ የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚያሳስባቸው ኢትዮጵያውያን ሲታሰቡ ፕ/ሮ አስራት የሚረሱ አልነበሩም እና አማከሯቸው፡፡

እኒህ የቅርብ ወዳጅ አያይዘው እንደነገሩኝ ፕሮፌሰሩ ሲጠየቁ "እኔ የማውቀው አንዲት ኢትዮጵያን ነው ቢሆንም የአማራ ህዝብ ላይ የተከፈተው ዘመቻ ያሳስበኛል" በማለት ይሞግታሉ፡፡ ከብዙ ውትወታም በኋላ የመላ አማራ ህዝብ ድርጅት (መአህድ) ይመሰረትና ፕሬዘዳንት ይሆናሉ፡፡ አ/ር ኃይሉ ሻወል ደግሞ ምክትል፡፡ ይሄንን ተከትሎም የመኢህድ መመስረት ለኢህአዴግ የራስ ምታት ይሆንበታል፡፡ ፕ/ሮ አስራትን ጨምሮ የአመራር አካላቱንና አባላቱን ማሰርና ማስበርገግም በቂ ሆኖ አልተገኘም ስለዚህ ሌላ ዘዴ ተፈለገ፡፡

ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ኢህዴን ከኢህአፓ ባፈነገጡና ኢህአፓ አሲምባ ላይ ሲመታ የተሰባሰቡ ሰዎች የፈጠሩት ፓርቲ ነው፡፡ ኢህዴን ኢህዴንነቱን እንደያዘም የኢህአዴግ አጋር ሆኖ እስከ ቤተ መንግስት ዘልቋል፡፡ የመአህድ መፈጠር ግን ኢህዴን እንደገና ፈርሶ እንዲሰራ ምክንያት ሆነ፡፡ በህወሓቶች መሀንዲስነትም የአማራ ህዝብ ወኪል እንዲሆን ተደረገ፡፡ ስሙም የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ተባለ፡፡ የብአዴን አጭር የህይወት ታሪክም ይሄው ነው፡፡ ቢጥመንም ባይጥመንም፡፡ ስለዚህ የአማራ ህዝብና ብአዴን በውል አይተዋወቁም፡፡ ለዚህም ነው የዜጐች ህመም የሚያመው፤ እንደ ምንም ነገር ንብረታችሁን ተቀምተው ሲባረሩ ዳርቆሞ የሚያየው ይላሉ፡፡

እኔ በበኩሌ ግን የዚህ ህዝብ ወኪል የዚያ ህዝብ ወኪል የሚለው ቃል ብዙ የሚዋጥልኝ አይደለም፡፡ የሁላችንም ውክልና ኢትዮጵያ የሚለው ስም እንዲሆን ምኞቴ ነው፡፡ የኢህአዴግ የፌደራሊዝም አወቃቀርና ፖለቲካ ግን ይሄንን የሚፈቅድ አይደለም፡፡ የብሔር ብሔረሰቦች መብት መከበር ላይ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ማሳደግ ላይ መከራከር አይቻልም፡፡ እነዚህ ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ መብቶች የሚመደቡ ናቸው፡፡ አስከፊ የሚሆነውና ኢትዮጵያዊነትን የሚያደበዝዘው ግን "ይሄ ያንተ ሃገር አይደለም!" ወደሚለው የወረደና ዘመናዊነት የራቀው ተራ አስተሳሰብ ላይ ስንመጣ ነው፡፡

ስለዚህ ወኪልነቱን ባንወደውም ኢህአዴግ የአማራ ህዝብ ወኪል እንዲሆን ወይም የስርዓቱን መርሆዎች በአማራ ላይ እንድጭንና እንዲያስፈፅም ዳቦ ቆርሶ ወደ ብአዴንነት የቀየረው ድርጅት ሃላፊነቱን እየተወጣ አይደለም፡፡ የአማራ ተወላጆች በእነ አቶ ሽፈራው ሽጉጤና ካድሬዎቻቸው ባዶ እጃቸውን ሲባረሩ ብአዴን ትንፋሽ አላለም፡፡

እንደዚህ አይነቱን በብሔርተኝነት የተጠቃ ድርጊት ማውገዝ ያለባቸው የአማራ ብሔር ተወላጆች ብቻ አይደሉም፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ "አንቀበለውም!" ማለት አለበት፡፡ ለነገሩ የጉራ ፈረዳ ተፈናቃዮችን ተከትሎ የነ አቶ ሽፈራውን ድርጊት ለማውገዝ ኢትዮጵያውያን ዘር፣ ጐሳ፣ ቋንቋ፣ ብሔር . . . መቁጠር አላስፈለጋቸውም፡፡ ይሄ ደግሞ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው፡፡ ብሔርተኝነት በኢትዮጵያዊት እንደተሸነፈ እንድናስተውል ዕድል ፈጥሮልናል፡፡

ለማጠቃለል ያክልም ዜጐች ከቦታ ቦታ ተዘዋውረው የመኖርና ሃብት የማፍራት ነፃነታቸው መገደብ አይኖርበትም፡፡ በሀገር መምራት ላይ የሚገኙ ባለስልጣናትም ነገ ሊያስጠይቃቸው እንደሚችል በውል ማወቅ አለባቸው፡፡ የሚጠይቋቸው ደግሞ የገዛ ልጆቻቸው ናቸው፡፡ ከተሳሳተ አስተሳሰባቸው ተመልሰው በጥሞና ማሰብ ይገባቸዋል፡፡ ካልቻሉ ደግሞ ስልጣኑን ለሚያስቡት ማስረከብ ነው፡፡ "አልችልም" ብሎ ስልጣን ማስረከብ በዘመናችን ጀግንነት እንጅ ውርደት አይደለም፡፡ አለበለዚያም ጥቃት የሚፈፀምባቸው ህዝቦች ጫንቃቸው ጥቃት ብዙ የሚችል አይመስለኝም፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!

# አዲስ አበባ 23ኛውን ዓለም አቀፍ ጤና ጉባዔ ታዘጋጃለች

በየሦስት ዓመቱ በሕዝብ ጤና ጉዳዮች ላይ የሚመክረው የዓለም ሕዝብ ጤና አጠባበቅ ማህበራት ፌዴሬሽን /WFPHA/ ዓለም አቀፍ ጉባዔ እንደሚያደረግ ተገለፀ፡፡ ከሁሉም የዓለም ማዕዘናት የሚመጡ የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ እስከ 3000 የሚደርሱ ተሳታፊዎችን በአፍሪካ ምድር የሚያገናኝና በአብይ የጤና ጉዳዮች ላይ የሚያወያይ 13ኛውን ታላቅ ጉባዔ በመዲናችን በአዲስ አበባ ከሚያዝያ 15 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚያካሂድ የጉባዔው አስተባባሪ የሆነው የኢትዮጵያ ጤና ባለሞያዎች ማህበር አስታወቀ፡፡

ማህበሩ ይህንን ያስታወቀው ባለፈው ዓርብ በራስ ሆቴል ለጋዜጠኞች ባዘጋጀው ወርክሾፕ ላይ ነው፡፡ በወርክሾፑ ላይ እንደተገለፀው ከሦስት ዓመት በፊት በ2009 እ.ኤ.አ የቱርክ መዲና በሆነችው በኢስታቡል ከተማ በተካሄደው 12ኛ ጉባዔ ላይ ማህበሩ እንደገና አጽንኦት በመስጠት የሕዝብ ጤንነት ጉዳይ የሰብአዊ መብት ጉዳይ ስለመሆኑ የጋራ ውሳኔ አስተላልፏል ተብሏል፡፡ በተጨማሪም በመንግሥት ሥራ፣በኢንዱስትሪ፣በሲቪል ማህበራትና በጤና አገልግሎት የተሰማሩ ሠራተኞች፣እንዲሁም ምሁራን፣የሲቪል ማኅበረሰብ መሪዎችና ዜጎች ሁሉ የሕዝብን መልካም ጤንነት ከመንከባከብና ጤናን ከመጠበቅ ጀምሮ ለሰው ልጆች መሠረታዊ የሆኑ አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ የሚያደርጉበትና ሰብአዊ ግንኙነቶች የሚበጁ ሞራላዊ እሴቶችን፣መረጋጋትን፣ፍትህን፣መተሳሰብንና መቻቻልን በማስፈን የሰዎችን ሕይወት ወደተሻለ ገፅታ የሚያሸጋግሩበት ጊዜ አሁን መሆኑን የጉባዔ ሰነድ በግልፅ ያስረዳል በማለት ተገልጿል፡፡

በወርክሾፑ ላይ በቀረበው ጽሑፍ እንደተገለፀው የዘንድሮው "የዓለም አቀፍ ፍትሐዊ የሕዝብ ጤና ምቹ አጋጣሚዎችና ስጋቶች" በሚል መሪ ቃል ስብሰባው እንደሚከናወን ያብራራል፡፡ ሰነዱ በመቀጠልም በዚህ ጉባኤ ላይ ባደጉና በማደግ ላይ ካሉ አገሮች የሕዝብ ጤንነት ጉዳዮችና የጋራ የሆኑ ተዛማጅ ጠቃሚ ተሞክሮዎችና ልምዶች እንደሚቀርቡ እንደሚጠበቅ ያወሳል፡፡ በጤና መስክ የተሰማሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም ለጋራ ጥረቶቻቸው መሰናክል የሆኑ ከፍተኛ ችግሮችን እና ምቹ ሁኔታዎችን በዝርዝር ያቀርባሉ፡፡

የዓለም ሕዝብ ጤና አጠባበቅ ማህበር ፌዴሬሽን /WFPHA/ እና የኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማኅበር /EPHA/ በዓለም አቀፍ፣በአገር አቀፍና በአካባቢ ደረጃ የሚገኙ ባለሙያዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የጤና አሰልጣኞችና ተመራማሪዎች፣ተማሪዎችና ሌሎችም ተቆርቋሪ ግለሰቦችና ተባባሪዎች ፍትሐዊ የሆነ የሕዝብ ጤና ከማስፈን አኳያ ስለሚያጋጥሙ ችግሮችና ምቹ ሁኔታዎች አመላካች ጥናታዊ ሥራዎቻቸውን በሚመለከት ፍሬ ሃሳቦችን የያዘ አጭር ዘገባ /abstract/ ያቀርባሉ፡፡ ጥናቶቹም ወቅታዊ የሆኑና ኢ-ፍትሐዊ ለሆነ የሕዝብ ጤንነት ሁኔታ መንስዔ የሆኑ ክስተቶችንና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን የሚያስገነዝቡ፣የሕዝብ ጤና አገልግሎት ሚና ምን መሆን እንደሚገባው ሐሳብ የሚሰጡ፣በተጨማሪም አዳዲስ ጠቃሚ ግኝቶችን፣የመገልገያ መሳሪያዎችን፣በቀላሉ ማስተላለፍ የሚቻል ዕውቀትና ቴክኖሎጂን የሚያመላክቱ እንደሚሆኑ ይጠበቃል ብሏል፡፡

ወርክሾፑን በንግግር የከፈቱት አቶ ሞቱማ ተመስገን የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ተወካይ ሲሆኑ አቶ ሞቱማ እንዳሉት "የአይካሳን ስብሰባ በድል እንደተወጣን ሁሉ ዛሬም ይህንን ዓለም አቀፍ ሰብሰባ በድል ለመወጣት ሚዲያዎች የተለመደውን ርብርብ እንዲያደርጉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡ በወርክሾፑ ላይ ዶ/ር ተስፋዬ ቡልቶና ዶ/ር አሰፋ ሲማ ጹሑፋቸውን ያቀረቡ ሲሆን የኢትዮጵያ ጤና ባለሞያዎች ማህበር ተወካይ ዶ/ር ተዋበች የመዝጊያ ንግግሩን አድርገዋል፡፡

ስብሰባው በኢትዮጵያ ውስጥ መደረጉ የአገሪቱን የቱሪስት መስብና ታሪኳን ለማስተዋወቅ ጥሩ አጋጣሚ በመሆኑ ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ ቀርቧል፡፡

# እነ አንዱዓለም አራጌ ነገ የቪዲዮ መከላከያቸውን ያቀርባሉ

## - ለህሊና እስረኞች የሻማ ምሽት ይደረጋል

በ "ሽብርተኝነት" ተጠርጥረው በእስር ላይ የሚገኙት እነ አንዱዓለም አራጌ ባለፈው ቀጠሯ
ቸው ዕለት የሰው መከላከያ ምስክሮችን አሰምተው ማጠናቀቃቸውን ለፍ/ቤቱ ገልፀዋል፡፡ ፍ/ቤቱ በያዘው ቀጠሮ መሠረት በነገው ዕለት የመከላከያ የኦዲዮና ቪዲዮ ማስረጃቸውን ያቀርባሉ፡፡

ባለፉት አራት ቀጠሮዎች የሰው የመከላከያ ምስክሮችን ያቀረቡት ተከሳሾች በመጨረሻ የቀጠሮ ዕለት ቀሪውን የሰው ምስክሮች አሰምተዋል፡፡ ባለፈው እሮብ ዕለት የአቶ ክንፈሚካኤል ደበበ መከላከያ ምስክር ሆነው የቀረቡት አቶ ሙላት ጣሰው፣ አቶ ኡርጌሳ ዋከኔና፤ ጋዜጠኛ ብዙአየሁ ወንድሙ ቀርበው መስክረዋል፡፡ አቶ ሙላት ጣሰው ለፍ/ቤቱ በሰጡት ቃል አቶ ክንፈሚካኤል ደበበን ለረጂም ዓመታት እንደሚያውቋቸው በህጋዊና ሠላማዊ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ተደራጅተው እንደሚንቀሳቀሱ አስረድተዋል፡፡ ፓርቲያቸውም ህጋዊ እውቅና እንዳለው ገልፀዋል፡፡ አቶ ኡርጌሳም በተመሳሳይ ሁኔታ መስክረዋል፡፡

ጋዜጠኛ ብዙአየሁ ወንድሙ በበኩላቸው ለፍ/ቤቱ በሰጡት «ቃል አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ ጋር እሳቸው እንደ ፖለቲከኛ እኔ እንደ ጋዜጠኛ እንተዋወቃለን፡፡ በተለያየ መድረኮችም እንገናኛለን» ካሉ በኋላ ከመታሰራቸው ጥቂት ቀናት በፊት የእሳቸው ፓርቲ መኢዴፓና የኢብአድ የተባለ ድርጅት መስከረም 4 ቀን 2004 ዓ.ም በሰሜን ሆቴል ተገኝተው ለጋዜጠኞች የሰጡትን መግለጫ መከታተላቸውን አስረድተዋል፡፡ «የመግለጫው ዓላማና ይዘት ምንድነው?>> ተብለው ከተከላካይ ጠበቆች ለቀረበላቸው ጥያቄ ጋዜጠኛ ብዙአየሁ መልስ ሰጥተዋል፡፡

"ፓርቲዎቹ በዕለቱ ለጋዜጠኞች የሰጡት መግለጫ መስከረም 21/2004 ዓ.ም ህዝባዊ የተቃውሞ ሠልፍ ለማድረግ ማቀዳቸውንና የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትን ፍቃድ መጠየቃቸውን ገልፀዋል፡፡ ፍቃዱ እንደተሰጣቸው ህዝቡ በዕለቱ ወጥቶ የተቃውሞውን ድምጽ እንዲያሰማ ያዘጋጁትን በራሪ ወረቀት እንደሚበትኑና እንደሚቀሰቅሱ አስታወቀዋል፡፡ የተቃውሞው ዓላማ ምንድነው? ብለዉ ነዉ የገለፁት የገለጹት ተብለው ለተጠየቁት ጋዜጠኛ ብዙአየሁ ሲመልሱ በአገሪቱ ውስጥ ከዕለት ወደ ዕለት የኑሮ ውድነት እየጨመረ መምጣቱን፣ በነጋዴዎች ላይ ከአቅም በላይ የግብር ጫና እየተፈጠረ መሆኑን በቴሌ ሠራተኞች ላይ የተፈፀመውን ከሥራ ማፈናቀል፣ የአገሪቱን መሬት ለውጪ ኢንቬስተሮች እስከ 99 ዓመት በሊዝ መስጠትን፣ የትምህርት ፖሊሲ ጥራት መውረድን በመቃወም ነው» ሲሉ መልሰዋል፡፡

«ከጋዜጠኞች የቀረቡላቸው ጥያቄዎች ነበሩ?>> ተብሎ ተጠይቆው ጋዜጠኛ ብዙአየሁ ሲመልስ "አዎ ከጋዜጠኞች በርካታ ጥያቄዎች ተጠይቀዋል፡፡ ህዝቡ አምኗችሁ ይወጣል? ህዝብ ባይወጣላችሁ ምን ታደርጋላችሁ? በዕለቱ ረብሻ ቢከሰት ኃላፊነት ትወስዳላችሁ? ለምን ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በጋራ አላደረጋችሁም? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተው ነበር ብለዋል፡፡ መግለጫውን የሰጡት አቶ ክንፈሚካኤል ደበበና አቶ አድማሱ ኃይሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በተለይ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ በሰጡት መልስ ጥያቄያችን የህዝብ ጥያቄ ስለሆነ ህዝቡ ወጥቶ ይቃወማል ብለን እናምናለን፡፡ ባይወጣ ግን እኛ የፓርቲው አመራሮችና አበላት ወጥተን ተቃውሞአችንን ገልፀን እንመለሳለን፡፡ ረብሻ ቢፈጠር ኃላፊነት አንወስድም፡፡ እኛ የጠራነው በህጋዊና በሠላማዊ መንገድ ተቃውሞአችንን ለመግለጽ ነው፡፡ ከዚህ አልፎ ረብሻ የሚፈጥር አካል ቢኖር ኃላፊነቱን ራሱ ይወስዳል፡፡ መድረክ አብሮአችን በተቃውሞ ሠልፉ ላይ እንዲሳተፍ ደብዳቤ ጽፈናል፡፡ እስከ አሁን መልስ አልሰጠንም» ሲሉ መልስ ሰቷል፡፡"

በዕለቱ ስንት ጋዜጠኞች ነበራችሁ? እርስዎ ብቻ እንዴት መከላከያ ምስክር ሆነው ሊቀርቡ ቻሉ? ተብሎ ከዐቃቢ ህግ ለቀረበላቸው ጥያቄ ጋዜጠኛ ብዙአየሁ ሲመልስ «በግምት ከ10-15 እንሆናለን፣ ባለፈው ቀጠሮ በዚሁ ችሎት የተጠሩ መከላከያ ምስክሮች ሲጠሩ ከእኔ ውጪ ሁለት ጋዜጠኞች ፍ/ቤቱ ስማቸውን ሲጠራ ስምቻለሁ፡፡ ለምን እንዳልመጡ የማውቀው ነገር የለም እኔ የፍ/ቤቱን ጥሪ አክብራ መጥቼአለሁ» እያሉ ሲቀጥሉ ፍ/ቤቱ «ሳይፈቀድልዎ መልስ አይሰጡ ሲባሉ አቋርጠዋል» ጠበቃ ደርበው ተመስጌን «ሌሎች ጋዜጠኞችም ለፍ/ቤቱ ቀርበው እንደመሰከሩ አስመዝግበን መጥሪያ አውጥተን ነበር፡፡ ሆኖም ግን የሚመሰክሩት ቃል አንድ ስለሆነ እሳቸውን ብቻ ይበቃሉ ብለን ነው» በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ በመጨረሻ የተከሳሾች የጋራ መከላከያ ብለው ተከሳሾችን ለማስመስከር ተሞክሮ በዐቃቢ ህግ በኩል ተቃውሞ በመቅረቡና ፍ/ቤቱም ብይን ስለሰጠበት እንዲቀር ተደርጓል፡፡ ጠበቆች ሰው ምስክር መጠናቀቁን በመግለጹ የቪዲዮ ማስረጃ ለማየት በነገው ዕለት በሦስት ሰዓት ተቀጥሮአል፡፡

ዘወትር ወር በገባ በ3 የሚከናወነው የሻማ ምሽትም በነገው ዕለት በተለመደው ሁኔታ እንደሚከናወን አስተባባሪዎቹ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡ አስተባባሪዎቹ እንደሚሉት በመላው አገሪቱ ለሚገኙ የህሊና እስረኞች ዘወትር ወር በገባ በሦስት ከአስር ሰዓት ጀምሮ በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት ውስጥ የሻማ ምሽት ይደረጋል፡፡ በዝግጅቱ ላይ በአገሪቱ የሚፈፀመው የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚወገዝበት በመሆኑ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይኖራሉ ተብሏል፡፡ በዝግጅቱ ላይ ማንኛውም ሰው መገኘት የሚችል መሆኑን አስተባባሪዎች ገልፀዋል፡፡

# በኢትዮጵያ ከፍተኛ ረሃብ ሊከሰት እንደሚችል ተገለፀ

ብስራት ወ/ሚካኤል

በኢትዮጵያ እጅግ አስከፊ ረሃብ ሊከስት እንደሚችል ተጠቆመ፡፡ በተለይ ወቅቱን ጠብቆ ይመጣል የተባለው የበልግ ዝናብ ባለመዝነቡ በደቡብ እና በአማራ ክልል ድርቅ ሊፈጠር እንደሚችልና በዚያም ምክንያት የአካባቢው ማህበረሰብ ለርሃብ ሊጋለጥ እንደሚችል የተለያዩ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን መዘገባቸው ይታወሳል፡፡

በደቡብ ክልል በሚገኘው የሰሜኑ ክፍል የበልግ ዝናብን በመጠቀም የክረምቱን ወቅት መሸጋገሪያ ይሆናቸው ዘንድ ድንች ስኳር የመሳሰሉትን በቶሎ የሚደርሱ የምግብ እህሎችን ያመርቱ ነበር፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ሪፖርቶች እና ጥናቶች እንዳረጋገጡት ከሆነ የበልግ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ባለመምጣቱ ለቀጣዮቹ ወራት እስከ ክረምት ርሃብ ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ የኢትዮጵያ መንግስት ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ ተጠቁሟል፡፡

የዝናብ እጥረቱ በምስራቅ ኦሮሚያና በትግራይ ክልል እንዲሁም በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ቦታዎች ላይ መከሰቱንና አሁን ያለውም ዝናብ ከሚጠበቀውና መደበኛ ከነበረው ያነሰ መሆኑን የዓለም የምግብ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ቃል አቀባይ የሆኑት ጂዲዝ ሼለር ነግረውናል ሲል IRIN ዘግቧል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማትና የረሃብ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ድርጅት በበኩሉ የበልግ ዝናቡ እጥረት እስከ ሰኔ መጀመሪያ ድረስ ሊቀጥል እንደሚችል ጠቁሟል፡፡ በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው እጥኚዎች በበኩላቸው በኢትዮጵያ እየተከሰተ ያለውን የዝናብ እጥረት ተከትሎ ከመጋቢት እስከ ግንቦት 2004 ዓ.ም የአፍሪካ ቀንድ መካከል ከፍተኛ ድርቅ ሊከሰት እንደሚችል ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል፡፡

በተለይ የበልግ ዝናብን በመጠቀም አምራች የሆኑት የደቡብ ክፍልን ጨምሮ የዝናቡ ሁኔታ ወደፊት በምን መልኩ ሊቀጥል እንደሚችል ጥርጣሬ እንዳላቸው የኢትዮጵያ ሜትሪዮሎጂ ኤጀንሲ የቅድመ ትንበያ ክፍል ዳይሬክተር አቶ ድሪባ ቆርጫ መናገራቸው ተገልፃል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ከፍተኛ ኦፊሰር የሆኑት አልማዝ ደምሴ በበኩላቸው ገበሬዎች ለረጅም ጊዜ መተካት የሚያስችላቸውን በቀሎና ማሽላ እንዲያለሙ ማስገንዘባቸውን አስታውሰዋል፡፡

ይህም የሚከሰተው የምግብ ሰብል ምርት እጥረት በጥራጥሬ እህሎች ዋጋ መጨመር ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው፤ የዋጋ ግሽበትም አሁን ካለበት 36.3% ሊጨምር እንደሚችል በመጠቆም በሀገሪቱም ባለፉት 5 ዓመታት ታይቶ የማይታወቅ የምግብ ዋጋ መናር ባልተጠበቀ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችልም የዓለም የምግብ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ቃል አቀባይ የሆኑት ሼለር መናገራቸው ተጠቁሟል፡፡

መንግስት በበኩሉ ችግሮቹ በተከሰቱበት አካባቢዎች በተለይ በደቡብና አማራ ክልል ከየካቲት አጋማሽ ጀምሮ ከፊል አስቸኳይ የምግብ ዋስትና ዳሰሳ በመጪዎቹ ሳምንታት በማድረግ ችግሮቹን መቆጣጠር እንደሚችል አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ የአደጋና የምግብ ዋስትና ቢሮ አስተዳደር ቃል አቀባይ አክሎግ ንጋቱ በበኩላቸው መንግስት ችግሩን ለመቆጣጠር ማቀዱን አስታውሰዋል፡፡ አያይዘውም ለገበሬዎች ችግኞችን እንዳዘጋጁና አርሶ አደሩም ለሚፈልገው መልሶ ማልማት እንዲችል ተደርጓል፣ ችግሮቹ አሉ በተባሉበት አካባቢም የአደጋና ዝግጁነት ግብረ ኃይል ተመድቦ በመጠባበቅ ላይ እንዳለ ገልፀውልኛል ሲል IRIN አስታውቋል፡፡

በቅርቡ መንግስት በኢትዮጵያ ድህነት ቀንሷል ብሎ መግለፁ የሚታወቅ ሲሆን የድርቅና ረሃቡ ስጋት ከጀመረ ግን አንድ ወር ከ15 ቀን እንዳለፈው ተጠቁሟል፡፡

ከሰሞኑ ያንዣበበውን የረሃብና ድርቅ አስመልክቶ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የሚሰጡን የተለየ መረጃ ካለ ብለን ጥረት ብናደርግም ለጊዜው አልተሳካም፡፡

# የአዋቂ አጥፊው የብሔራዊ ባንክ ገዥ



በበለጠ ጐሹ ወ/ሚካኤል

በኢህአዴግ መንግሥት በከፍተኛ ባለሥልጣንነት ለበርካታ ዓመታት የቆዩ ቢሆንም፣ እንደ ሥልጣን ዘመናቸው ርዝማኔ በሕዝቡ ዘንድ ብዙም ታዋቂ አይደሉም፡፡ ስለ አለቃ አጥናፉ ልጅ፣ስለ አቶ ተክለወልድ አጥናፍ እያወራሁ ነው ያለሁት፡፡ የሠለጠኑባቸው የሙያ መስኮች ስታትስቲክስና ኢኮኖሚክስ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት የትምህርት ዓይነቶች አብረው የሚሄዱ ናቸው፤ምክንያቱም በኢኮኖሚክስ የትምህርት ዘርፍ ኢኮኖሜትሪክስ የሚባል በሂሣብ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ዓይነት ስለአለ ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን ኢኮኖሚትሪክስ ዋና የኢኮኖሚ መተንተኛ መሣሪያ ነው፡፡ ሁለተኛ የዩኒቨርስቲ ዲግሪያቸውን ከጨበጡ ዓመታት ተቆጠረዋል፡፡ ብዙ ጊዜያቸውን የሠሩት በደርግ ጊዜ በነበረው የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና አሁን ገዥ በሆኑበት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተራ ኤክስፐርትነት ተቀጥረው፣በአጭር ጊዜ ውስጥ በብርሃን ፍጥነት ወደ ላይ ተምዘግዝገው የባንኩ ገዥ ለመሆን በቅተዋል፡፡ በብዛት የሠሩበት ልዩ የኢኮኖሚክስ ሙያ ንዑስ ዘርፍ የገንዘብ ኢኮኖሚክስ ነው (monetary economics)፡፡ ስለዚህ የብሔራዊ ባንክ ገዥ ለመሆን የሚያበቃ ዕውቀትና ሙያ አላቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ በግለሰብ ደረጃም ብሩህ አእምሮ ያላቸውና በቁጥብነታቸው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ይሁንና ኢህአዴግ ሥልጣን እንደያዘ ስውር ስብዕናቸው ወጣ፡፡ የሁለት ብሔረሰቦች ክልስ እንደመሆናቸው፣ ለማንነታቸው መታወቂያነት ከሁለቱ የፈለጉትን ብሔረሰብ የመምረጥ መብት እንዳላቸው አውቃለሁ፤ ግን ቀድሞ በአማራነት ሊታወቁ ይፈልጉ የነበሩት ሰው፣ድንገት አማራ ጨቋኝ፣ ነፍጠኛ፣ትምክህተኛ፣ወዘተ እየተባለ «ሲሸማቀቅ»፣የወላይታን ታፔላ ለጠፉ፡፡ ይህ ከማንም የሚሰወር ነገር አይደለም፤ የሚያስገርመው ተለዋዋጭነታቸው ነው! ግን ለምን? ስውዬው ዓላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው፣የግለሰቦችን ስብዕና የሚያሽከረክሩ ቢያንስ ሦስት ጠንካራ ውስጣዊ ፍላጐቶች አሉ፤ እነሱም ሥልጣን፣ገንዘብና ዝና ናቸው፡፡ አቶ ተክለወልድ የሀብታም ቤተሰብ አባል እንዳልሆኑ ይነገራል፡፡ ስለዚህ፣በመጀመሪያ የእሳቸውን ሕይወት የዘወረው ኃይል የገንዘብ ፍላጐት እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ ወደ ገንዘብ ለመምጣት ደግሞ ሥልጣንን መጠጋት አንዱ መንገድ ነዉ፡፡ በመሆኑም፣ የቅርብ ጓደኞቻቸው ጭምር ሳያውቁ፣በኢህአዴግ ተመልምለው አባል እንደሆኑ ይወራል፡፡ እንግዲህ፣ከዚህ በኋላ ነው በብርሃን ፍጥነት ከተራ ኤክስፐርትነት ወደ መምሪያ ኃላፊነት ከዚያም ወደ ምክትል ገዥነትና በመጨረሻም አሁን ወደ ያዙት የብሔራዊ ባንክ ገዥነት የተሸጋገሩትና ያደጉት፡፡

ምን ገንዘብና ሀብት አገኙ? ጥሩ ጥያቄ ነው፤ ግን በዚህ ላይ የበለጠ ተዓማኒነት ያለው መረጃ ሊሰጥ የሚችለው የፀረ-ሙስናና ሥነ ምግባር ኮሚሽን ነበር፤ግን እሱም ተዓማኒነት ያጣ ተቋም እየሆነ ነው፡፡ የሃያ ሰባት ሺ ባለሥልጣኖቻችንና ሌሎች ሰዎችን ንብረት መዝግቤአለሁ ይበል እንጂ፣የአንዳቸውንም ንብረት እስከአሁን ይፋ አላደረገም! እኔ በተለይ የእነ ወ/ሮ አዜብ መስፍን ንብረት መጠን ለማወቅ በጣም ፈልጌ ነበር! ግን እስከአሁን እንደጐመጀሁ አለሁ! ንብረትን በተመለከተ፣አቶ ተክለወልድ አጥናፉ በእነ ወ/ሮ አዜብ ደረጃ ያሉ ባለሥልጣን አይደሉም፡፡ አስታውሱ፣ምንም እንኳ ገንዘብን እንደ ዋና ዓላማ አድርገው የተነሱ ለመሆናቸው ጠቋሚ መረጃዎች ቢኖሩም ፣የቄስ ልጅ ናቸው! የአለቃ አጥናፉ፡፡ ከመጠን ያለፈ ነገር እንደማይፈልጉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ የአማራ እና የወላይታ የተወለዱ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ በዚህም ምክንያት ከአማራ የበለጠ ኢትዮጵያዊ ናቸው! በሃይማኖት በኩል፣አክራሪ እስከመባል ደርሰዋል፡፡ ቦምብ ይዘው ስለሚያፈነዱ አይደለም፤ይህንንማ የቄስ ልጅ ሊያደርገው አይችልም፡፡ አክራሪ የሚባሉት በፆም ቀን ከማለዳ እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ስለሚፆሙ ነው፡፡

ቢሆንም፣ቢየንስ ሁለት ቪላ ቤቶች እንደሚያከራዩ በሰፊው ይወራል፡፡ በአዋጅ በተሰጣቸው መብት መሠረት፣አምስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ እና ሁለት መቶ ሃምሣ ሺ ብር የባንክ ብድር እንዳገኙም ይነገራል፡፡ መለስተኛ ቤተመንግሥት በመሰለ የመንግሥት ቤት ውስጥ በነፃ ይኖራሉ፡፡ መኪናን በተመለከተ፣ ባለቤታቸው ጭምር የመንግሥት ኩሩዘር መኪናዎች ያቀያይራሉ፡፡ ለቤንዚን አያስቡም፡፡ ልጆቻቸው አሜሪካን ሀገር እንደሚማሩ ይወራል፡፡ በፈለጉበት የውጭ ሀገር ሄደው የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፤ በነፃ፡፡ ያልተጣራ የወር ደመወዛቸው ወደ አሥራ ሁለት ሺ ብር ይደርሳል፡፡ ከደመወዝ፣ ከቤት ኪራይና እንደ አክስዮን የትርፍ ክፍያ ካሉ ሌሎች ገቢዎች በጠቅላላው በወር ከ70-80 ሺ ብር እንደሚያገኙ ይገመታል፡፡

በአጠቃላይ፣ከሞላ ጎደል ለሚሰሩት ሥራና ለተሰጣቸው "ሥልጣን" የሚያገኙት ገንዘብ ከዚህ የሚበልጥ አይመስለኝም፡፡ (የቤት ኪራይ ገቢን ጨምሮ)፡፡ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ትክክለኛውን መረጃ ቢሰጠን ጥሩ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ነገር አስረግጬ መግለፅ ያለብኝ ነገር አለ፡፡ ይኼውም፣ የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን "እንደመሆናቸው፣ስለ እሳቸው የሕይወት ታሪክና ስለ አፈሩት ንብረት ማውራት ሕገ ወጥ ሊሆን አይችልም፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣን ይባሉ እንጂ፣ሥልጣናቸው የይስሙላ ነው! ለዚህም ነው አቢይ ፍላጐታቸው ገንዘብ ነው ብዬ የተነሳሁት፡፡ ቀደም ብሎ ሙሉ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት የነበረው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተጠሪነቱ ለጠ/ሚኒስትሩ ሲደረግ፣አቶ ተክለወልድ ምንም ትንፍሽ ሳይሉ በፀጋ ነበር የተቀበሉት፡፡ በመሆኑም፣በውስጥ አስተዳደር ነፃነት የሚኖራቸውን እውነተኛ ሥልጣን ለግል ጥቅም ሲሉ፣አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ "ለገንዘብ ሲሉ" ያልኩት ሌላ ምክንያት ስላጣሁ ነው፡፡ ኢኮኖሚስት እንደመሆናቸው ለሙያቸው አልተከራከሩም! ከሙያቸው ሊያገኙ ይችሉ የነበረውን ሙያዊ ሥልጣን በገዛ ፈቃዳቸው ለሌላ አካል አስረክበዋል፡፡

ይህንን ሙያዊ ሥልጣናቸውን ለጠ/ሚኒስትሩ አሳልፈው ከሰጡ በኋላ፣እውነተኛው የብሔራዊ ባንክ አዛዥ ተክለወልድ አጥናፉ ሳይሆኑ፣መለስ ዜናዊ ናቸው፡፡ አቶ መለስ ደግሞ ስለ ፖለቲካ እንጂ ስለ ኢኮኖሚ ሕግጋት ጉዳያቸው አይደለም! እናም፣አቶ ተክለወልድን፣"ሃምሣ ቢሊዮን ብር አሳትሞና ለሶፊያን ስጥልኝ" ሲሏቸው፣"እሺ ጌታዬ!" ከማለት ውጪ በሙያቸው የማያውቁትን የኢኮኖሚክስ ሳይንስ እያጣቀሱ፣ "የለም አይሆንም! የዋጋ ንረት ከወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት የባሰ አደጋ አለዉ" ብለው የፖለቲካ ቅብ ያለው ኢኮኖሚያዊ መልስ መስጠት አልቻሉም! በዘመነ ኃ/ሥላሴ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ የነበሩት ስመ ጥሩ ምናሴ ለማ ቢሆኑ ኖሮ ግን፣ "ጃንሆይ ይዳኙን" ነበር የሚሉት፡፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የገንዘብ ሚኒስትራቸው አቶ ማሞ ታደሰ እና የብሔራዊ ባንክ ገዥአቸው አቶ ምናሴ ለማ በገንዘብ ጉዳይ ተካስሰው እሳቸው ፊት

ወደ 15 ዞሯል

# የሰሞኑ የመምህራን የሥራ . . .

ከገፅ 10 የዞረ

አቅልሎ ማሰብ ምን የሚሉት የፖለቲካ አካሄድ ነው? ዛሬ ባለንበት 21ኛው ክ/ዘመን ጡጦ የሚጠቡ ሕፃናትን እንኳን በቀላሉ ማታለል አንችልም፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ስለ ኢህአዴግ ፖለቲካ በቂ ግንዛቤ አላቸው፡፡ በሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት በህገ መንግስቱ ውስጥ ስለተደነገጉት ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከየትኛውም የኢህአዴግ ሹመኛ በላይ ያውቃሉ፡፡ ስለ ኢህአዴግ የፖለቲካ መስመር የጠበቀ ግንዛቤ አላቸው፡፡

ስብሰባ ሦስት፡- ከተማሪ ወላጆች ጋር ውይይት እሁድ መጋቢት 23/2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ በሚገኙ ት/ቤቶች የተማሪ ወላጆች አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርተው ነበር፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ ለወላጁ የጥሪ ወረቀት ከብርቱ ማስጠንቀቂያ ጋር ነበር እንዲሰጥ የታዘዘው፡፡ የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም በርካታ ወላጆች በየት/ቤቱ ተገኝተዋል፡፡ የፈረደባቸው አወያይ ካድሬዎች እንደልማዳቸው የመምህራንን የሥራ ማቆም አድማ በመኮነን ዲስኩር አቀረቡ፡፡ ሕዝቡ ግን እንዲቀጥሉ እድል አልሰጣቸውም፡፡ "ዛሬም ልትዋሹን ትሞክራላችሁ እንዴ? ኢህአዴግ መቼ ይሆን እውነት የሚናገረው? መምህራኑ እኮ ልጆቻችን ናቸው! ችግራቸውን በቅርበት እናውቃለን፡፡ የወር ደመወዛቸው 15 ቀን አታደርሳቸውም፡፡ በብድር ነው የሚበሉት፤ በብድር ነው የሚለብሱት፤ የተንሻፈፈ ጫማ ተጫምተው ነው ኑሮን የሚገፉት፤ ጠግበው መብላት እንኳን አይችሉም፡፡ በዚያ ላይ መንግስት አንድ ሊትር ዘይት የማትገዛ የደመወዝ ማሻሻያ አድርጎ ሺህ ብር የጨመረላቸው ይመስል በዚያ መከረኛ መዋሸት በማይሰለቸው ቴሌቪዥን የደሰኮራችሁትን የሚመጥን ገንዘብ ጨምሩላቸው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመምህራን ደመወዝ ተጨመረላቸው ብሎ አይቃወማችሁም" የሕዝቡ የቁጣ ስሜት እንደ እሳት ወላፈን የሚፋጅ ነበር፡፡

ውድ አንባቢያን የኢህአዴግ የፖለቲካ አቅጣጫ ጊዜ ያለፈበት ነው፡፡ ኢህአዴግ 21 ዓመት ሙሉ ህዝብን ከህዝብ፣ ወጣቶችን ከአዛውንት አንዱን ብሔረሰብ ከሌላኛው አንዱን ሀይማኖት ከሌላኛው ሀይማኖት፣ ቤተሰብን ከልጆች ወዘተ በአመለካከት ለመለያየት ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም፡፡ እኩይ እቅዱ እንዳልሰመረለት እያወቀው አካሄዱን ከመፈተሽ ይልቅ ዛሬም በዜጎች መሀከል ፅብና ጥላቻን፣ መለያየትና መቃቃርን ሊዘራ ይሞክራል፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጠብመንጃ አፈሙዝና በሚዲያ የቅጥፈት ዜና ማስተዳደርን ዋነኛ አማራጭ አድርጎ ወስዶታል፡፡ ዛሬ ከዓለማችን በኢኮኖሚ ዕድገታቸው በቁንጮነት የሚጠቀሱ አገራት በድህነትና በሥራ አጥነት ችግር ሲታመሱ እያየንና እየሰማን ኢህአዴግ በቴሌቪዥን መስኮት ኢትዮጵዊያን በቁንጣን እንደተቸገርን አስመስሎ ያወራል ተራብን፣ ተጠማን፣ ታረዝን፣ ከሥራ አጣን የሚሉ ዜጎችን ድምፅ ለአፍታ እንኳን መስማት አይሻም፡፡ «አሸባሪ» የሚለው ብያኔ (definition) ከተቃዋሚ የፖለቲካ መሪዎችና ከጋዜጠኞች ቀጥሎ "ተራብን፣ ኑሮውን መቋቋም አልቻልንም" የሚለውን ድሃ ሕዝብም ማካተት ጀምሯል፡፡ ለህወሓት ኢህአዴግ መሪዎች አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ማለት እየተራበ "ጠገብኩ የሚል" ህመሙ እየፀናበት "ጤነኛ ነኝ" የሚል፣ ጎተራው ባዶ ሆኖ "ሚሊየነር ነኝ" የሚል ጥፋትን እያየ "ልማት ነው" የሚል ይሄ ነው የዘመነ ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊነት እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ለመባል እኩይም ቢሆን በኢህአዴግ በኢህአዴግ ቋንቋ «ልክ ነህ» እያልን መቀበል ያለብን ይመስላል፡፡

የሕወሓት /ኢህአዴግ መሪዎች ራሳቸውን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ አሊያም እንደ ነቢዩ መሀመድ መሲህ አድርገው በመቁጠር ሊሰብኩን ይሞክራሉ፡፡ ኢትዮጵያን ከመበታተን ለመታደግ ከፀባአት የተላኩ ለመምሰል ይደሰኩራሉ፡፡ ሙሴ እስራኤላዉያንን ከፈርኦን የግፍ አገዛዝና ከግብፅ የእርኩሰት ኑሮ አላቅቆ ማርና ወተት ወደምታፈልቀው የተስፋይቱ ምድር እንደመራቸው ሁሉ የኢህአዴግ መሪዎችም ኢትዮጵያንን ከወታደራዊው ጁንታ አገዛዝ ነፃ በማውጣት ወደ ምድራዊ ገነት እንዳስገቡን አድርገን እንድናምን ሊያስገድዱን ይዳዳሉ፡፡ ገና ለገና የራስን የሥልጣን ዘመን ለማራዘም ሲባል ዘወትር የሕዝብን ድምፅ ለማፈን መሞከር አንድም ስንዝር እንደማያስኬድ ከሰሜን አፍሪካዎቹ የአረብ አገራት ሕዝባዊ አመፆች የተማርን ይመስለኛል፡፡ ለዓመታት የተጠራቀመ የሕዝብ ብሶት አንድ ቀን በቁጣ ሊፈነዳ ይችላል፡፡ ድንገት የሚገነፍል ሕዝባዊ ቁጣ መቼና የት እንደሚገነፍል ሕዝቡም ራሱ አያውቀውም፡፡ በታሪክ ትምህርት ለአንደኛውና ለሁለተኛው የአለም ጦርነት መፈንዳት ምክንያትና ውጤቱ ምን እንደሆነ (cause and effect) በሚል ይብራራል፡፡ በሥነ ፅሁፍ በተለይም የደራሲ የምናብ ፈጠራ በሆነው ልቦለድ ድርሰት ውስጥ ሴራ /ትልም (plot) የሚባለው የልቦለድ አለባ (Elements fo novel) የምክንያትና ውጤት ትስስር የሚፈተሸበት ነው፡፡ ለአረቡ ዓለም አብዮት መቀጣጠልና እስከ አራት አስርት አመታት ቤተ መንግስትን የግል መኖሪያቸው ላደረጉ መሪዎች ሞትና ውርደት ምክንያት የሆነው የቱኒሲያዊው ቡአዚዝ ራሱን በእሳት ማጋየት ነው፡፡ እዚህ ላይ በጥልቀት ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ የዚህ ወጣት ምክንያት በደምሳሳው ሲታይ መንግስትን ለመገልበጥ የሚያነሳሳ አይመስልም፡፡ በየትኛውም አገር ሰው ራሱን በራሱ ያጠፋል፤ ፈረንጆቹ "self suicide" እንደሚሉት፡፡ ምናልባት ራሱን ያጠፋ ሰው የዜና ሽፋን እንኳን ላይሰጠው ይችላል፡፡ የቡአዚዝ ርምጃ ግን ከቱኒሲያ አልፎ የአረብ አገራትን በአመፅ አናወጠ፡፡ ለምን? ቢባል አስቀድሞ ህዝቡ ያረገዘው ብሶት፣ በውስጡ ያመቀውና እንደ ረመጥ የሚፈጀው ቁጣ የመርፌ ቀዳዳን ያህል መተንፈሻ ይፈልጋልና፡፡

የኛዎቹ ኢህአዴጎች እንደ ቆዳ ስሱ ደራሲ ትንሹም ኮሽታ የምታስበረግጋቸውና በፍጥነት ርምጃ ለመውሰድ የሚቀናቸው የሚመሩት ህዝብ በብሶት የተወጠረ መሆኑን ስለሚያወቁነው፡፡ ለዚህም ነው የዳቦ ጥያቄ ያነሱ መምህራንን እንደ አመፅ ቀስቃሽ በመፈረጅ በአንዲት ገጽ ደብዳቤ ከሥራ ያሰናበቱት፡፡ ግን አንድ ጥያቄ ተባራሪው ማነው? አባራሪውስ የተባራሪውም የአባራሪውም ደመወዝ ከደሀው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚሰበሰብ ግብር እንጂ ከኢህአዴግ ካዝና የሚዛቅ ገፀ በረከት አይደለም፡፡ ሁልጊዜ እህህ ነገም? "ጊዜ እንጂ ሰውን ሰው አሸንፎት አያውቅም፡፡" እውነት አንድ ቀን ታሸንፋለች፡፡

ፈጣሪ የሳምንት ሰው ይበለን

# አንድነት አንድ ሰዉ አጣ

አቶ ዮሴፍ ባህረጥበብ በ1967 አገራችን በለውጥ በምትታመስበት ወቅት ከአባቱ ከአቶ ባህረጥበብ አለሙና ከእናቱ ከወይዘሮ ዘውድነሽ ክብረት በአዲስ አበባ ከተማ ፍል ውሃ አከባቢ መወለዱን ያገኘነዉ መረጃ ያመለክታል፡፡

ዮሴፍ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህረቱን በአካባቢው ወደሚገኘው የፈለገ ዮርዳኖስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በመግባት የጀመረ ሲሆን ወደ ቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተዛውሮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እየተከታተለ ሳለ ቤተሰቦቹ ለልጃቸው በላቸው የወደፊት ብሩህ እድልና የትምሕርት ፍቅር የዘጠነኛ ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ወደ ጀርመን አገር መኳዙ ታዉቋል::

በ1999 ወደ ምድረ አሜሪካ በማቅናት ኑሮውን በሚኒያ ፖሊስ ሚኒሶታ አድርጎ ይኖር እንደነበር ከህይወት ታሪኩ ያገኘነዉ መረጃ ያመለክታል::

ገና በልጅነቱ የሀገር ፍቅር የደረበት ዮሴፍ በጀርመን ሐገር ሳለ በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ይመራ የነበረውን ድርጅት በመቀላቀል ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በፅፈት ቤታቸው ውስጥ የነፃ አገልግሎት በመስጠት የወጣቶች ሊግ ካቋቋሙት ወጣቶች መካከል አንዱ ነበር::

በሀገሩ ጉዳይ ለሚመጡበት የማይተኛው ዮሴፍ ከፍተኛ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ተሳትፎ የነበረው መሆኑ የተነገረ ሲሆን በተለይም 1997 ምርጫ ወቅት የቅንጅት ድጋፍ ድርጅት በሚኒሶታ እንዲቋቋም ካደረጉት ግለሰቦች አንዱና ዋነኛዉ መሆኑ ተመልክቷል::

ከህይወት ታሪኩ ባገኘነዉ መረጃ መሰረት ምርጫ 1997ን ተከትሎ በደረሰው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር እና አባላት እስራት የታቃውሞ ሰልፎችን በመምራት ድምፁን ከፍ አድርጎ በማሰማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረገና የደከመ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነበር::

ይሄ ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰባችን ስለሀገሩ እንዲያውቅና እንዲረዳ በራሱ ገንዘብ የሬዲዮ የአየር ሰዓት በመከራየት የሬድዮ ፕሮግራም ለሕብረተሰባችን አገልግሎት ሲሰጥ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

ብዙዎች ፊታቸውን ባዞሩበት ወቅት እሱ ስለሀገሩ ማሰቡንና መስራቱን ቀጥሎ የአንድነት ድጋፍ ድርጅት በአሜርካ በላስቬጋስ ከተማ በተቋቋመ ወቅት ሚኒሶታን በመወከል ከመስራች አባላቱ አንዱ ነበር::

ከዚያም በሚኒሶታ የድጋፍ ድርጅትን በማቋቋም እስከ መጨረሻው የህይወት እልፈቱ ድረስ ‹‹የኛ ሰዎች እንዴት ናቸው?›› እያለ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርግ የነበረ ወገናችን ነበር::

ዮሴፍ ባለፉት ሁለት አመታት በህክምና ሲረዳ ቆይቶ ቅዳሜ March 31st በ አቦት ሚኒያፖሊስ ሆስፒታል በተወለደ በ37 አመቱ አርፏል፡፡ ዮሴፍ የአንዲት ሴት ልጅ አባት እንደነበር ታዉቋል፡፡

# የመንግሥት ያለህ!

ወ/ሮ ለምለም አርአያ

ነፃ ጋዜጦች ተዘግተው ባሉበት ሁኔታና ሕዝቡ ብሶቱን የዴሞክራሲ ጥማቱን ለወገኑ የሚገልጽበት መንገድ ተዘግቶ መላወሻ በጠፋበት ሰዓት በሀገራችን አንድና ሁለት ጋዜጦች ብቻ መቅረታቸው የዕድገታችንን ቁልቁልነት እንጂ እድገታችንን አያሳይም፡፡ ፍኖተ-ነፃነት ጋዜጣም በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ለህትመት በቅታ የሕዝቡን ብሦትና ችግር የምትተነፍስና እኛንም የምታስተነፍስ ለመሆን እንድትበቃ እምነቴ ነው፡፡

ከዚህ በመነሣትም “በጋዜጣችሁ የአዲስ አበቦቹ ቦሳሶች” የሚል አቶ ብሩክ ከበደ የፃፉትን ርዕስ በተመለከትኩበትና ከጥቁር አንበሣ አካባቢ እስከ ካዛንቺስና አውቶቡስ ተራ ባሉ አካባቢዎች በሚገኙ የውጪ ጉዞ አመቻቺዎችና አስጠላዮች በየጊዜው ቁጥራቸው የትየለሌ የሆኑ ዜጐች በህገ-ወጥና በህጋዊ መንገድ ከሀገር መውጣታቸውን በሚገባ የሚታወቅና ለዚህም ድርጊት ሃይ ባይ መጥፋቱ ሀገራችን መንግሥት አላት ወይ? እስከ ማለት ደርሷል፡፡ ያቺ! የቀደምት ኩሩ ዜጐች ነገር ግን በሚያልፈው ረሃብና ችግር የተያዙ ይኖሩባት ያልነበረችውን ያህል በአሁኑ ጊዜ ለገንዘብና ጥቅማጥቅም እንዲሁም ሥልጣን ፍለጋ ሀገራቸውንና ሃይማኖታቸውን የሚሸጡና የሚለወጡ እንክርዳዶች ተፈልፍለውላት ሳይ ለመጪው ዕድሜዬና ልጆቼ ሥጋት ገባኝ፡፡

የራሱ ያዋቀረውን የመንግሥት ሥልጣንና ሰልጣኞች (ባለስልጣኖች) “የኛ ሌቦች” እያለ የሚናገር



አመራር ያላት ሀገር በስኳር ስበብ አይደለም በጨውም ስበብ ገና ከየቀያችን ያፈናቅሉናል፡፡

ሰሞኑን በዚህ በዓልና መኸር ዝናም ከቀያቸው እያለቁሱ የወጡ ወገኖች ዕንባ እንዲሁ ፈሶ እንደማይቀር ሁላችንም ልናውቀው ይገባል፡፡ የሚገርመው ደግሞ ኢትዮጵያ የራሷ አምላክና ፈራጅ ስላላትም ዝሮ በወንበራቸው ላይ ተቀምጠው የቀለዱትና ያሾፉት ነገ የእጃቸውን እንደሚያገኙ አልጠራጠርም፡፡

ከዛን ጊዜዎቹ ሐሰን ዓሊ፣ታምራት ላይኔና መሰሎቹ ያልተማረ ሥርዓት መቼውኑም አይማርም፡፡

## እስከ 2006 ዓ.ም ...

ከገፅ 1 የዞረ

ከተፈናቃዩ ጋር ብንገናኝ ከባድ ርምጃ እንደሚወስዱብን ገልፀው አባረሩን›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ ቀደም ሲል ሰፍረውበት ከነበረው ወረዳ ስድስት አካባቢ መራቅ ያልቻሉትን ሰብስበው አዋሬ አካባቢ በአንድ ቀበሌ ወጣት ማዕከል መስፈራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ተፈናቃዮች እየተፈናቀሉ ከሚመጡበት አካባቢ አንድ ኃላፊ በቴሌቪዥን ቀርቦ ‹‹ከአካባቢያችን ማንም በግዳጅ አልተፈናቀለም፡፡ የተወሰኑ ግለሰቦች በግል ፍላጐታቸውና ውሳኔያቸው አካባቢውን ለቀው ወደ ትውልድ ሥፍራቸው ሄደዋል፡፡›› በማለት ሐሳብ መስጠታቸው ይታወቃል፡፡ በማግስቱ ሐሙስ በሰባት ሰዓት ላይ ከሚዛን ተፈሪ ተደውሎ እንደተነገረንና እንዳረጋገጥነው ደግሞ በሰዓቱ ከቦታው ተገደው እንዲነሱ የተደረጉ በተለምዶ የሰው ማጓጓዣ በሆነው ቅጥቅጥ አይሱዙ መኪና ተጭነው ፖሊስ ጣቢያ ፊት ለፊት ሜዳ ላይ ሲራገፉ እንደነበር የአይን ምስክሮች ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ደብዳቤ እንደሚገልፀው እንዲባረሩ ያዘዙት ከ1999 ዓ.ም ወዲህ የመጡ ቢልም ተፈናቃዮች እንደሚሉት ደግሞ ከ20 ዓመት በላይ በአካባቢው የኖሩ ሁሉ በአጠቃላይ እንዲነሱ መገደዳቸውን ይገልጻሉ፡፡ ተፈናቃዮች በጋራ እንዳይንቀሳቀሱ ከሦስትና ከአራት ያልበለጡ አብረው እንዳይጓዙ እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ ሳይገቡ በጥንቃቄ ወደየትውልድ መንደራቸው እንዲጓዙ እየተደረገ ነው ሲሉ የመረጃ ምንጮቻችን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ዓይነት አሠራር እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ 78 ሺ አማርኛ ተናጋሪ አባወራ ደቡብን ለቀው እንዲወጡ መታቀዱን ምንጮች ያስረዳሉ፡፡

## አንድነት ፓርቲ ...

ከገፅ 1 የዞረ

ከተፈረጀው ከግንቦት 7 ጋር አንድነት የህቡዕ ግንኙነት ያለው በማስመሰል የንግግር ዘገባ ማቅረብና ፓርቲው ውስጥ ሰርጎ እንደገባ ለዚህ ሽፋን እንደሰጠነው በመናገርና በምስል በማቅረብ፤ እንዲሁም የአንድነት ፓርቲ አባል ያልሆኑት ወይም አባል ለመሆናቸው የምርጫ ቦርድ ያላረጋገጠለትን የሰዎች ስም በመጥቀስ አባል እንደሆኑ አድርገው በማቅረብ በአጠቃላይ አንድነትንና አባላቱን አሸባሪ ተብሎ በህግ ለተፈረጀ ድርጅት ድጋፍ የሚሰጡ፣ሁከትና ብጥብጥ ፈጣሪዎች ናቸው በማለት ሀሰተኛ ዘገባ በማቅረብ የአንድነትን ስም አጥፍቷል” ብሏ፡፡ የአንድነት ፓርቲ የክስ ዝርዝር እንደሚያስረዳው ‹‹ተከሳሾች ይህንን የመሰለ የስም ማጥፋት ተግባር በአንድነት ላይ የፈፀሙት ሆን ብለው፣አቅደው እና አስበው ሲሆን አላማቸውም አንድነት ፓርቲ በሌሎች እንዲጠላ፣እንዲዋረድና እንዲሳቅበት በሌሎች ዘንድ ያለው ተወዳጅነት፣እምነትና መልካም ዝና እንዲበላሽ በማድረግ በቀጣይ ምርጫ ሕዝቡ ውዥንብር ውስጥ ገብቶ አንድነት ድምፅ እንዲያጣ ለማድረግ ነው›› ካለ በኋላ የክስ ዝርዝሩ በመቀጠልም 1ኛ ተከሳሽ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትና 2ኛ ተከሳሽ አቶ አብዲ ከማል ሆን ብለውና አቅደው ፕሮግራሙን የሰሩበት ዓላማ የከሳሹ አንድነት ፓርቲን ስም በማጥፋትና ሰዎች ጥርጣሬ ላይ እንዲወድቁ በማድረግ አባላት እንዳያፈራ፣የገንዘብና የሞራል ድጋፍ እንዳያገኝና በሌሎች እንዳይታመን በማድረግ መልካም ስሙንና ዝናውን በማበላሸት ጉዳይ ላይ ለመጣል መሆኑን አትቷል፡፡

ስለዚህ ለወደፊት በህጋዊ መንገድ ፓርቲው ተወዳድሮ በቀጣይ ክልላዊና ጠቅላላ ምርጫ አሸንፎና ተረክቦ ለመምራት የሚያደርገውን ወሳኝ እንቅስቃሴ ለማዳከምና ለማሰናከል እያገኘ የመጣውን የሕዝብ ድጋፍ ለማዳከም የተፈፀመ ነው፡፡ ድርጊቱ መራጩን ሕዝብም ግራ መሆኑን ያትታል፡፡

ይሄ ሁሉ የተፈፀመው በህጋዊ መንገድ ተመዝግቦ በህጋዊ መንገድ የፖለቲካ ፕሮግራሙን በማራመድ ለፖለቲካ ሥልጣን በሚታገለው ድርጅት ላይ ነው፡፡ ከሳሽ አንድነት ፓርቲ ይሄው የሐሳብ የስም ማጥፋት ዘገባ ሕገ-መንግሥቱን አንቀፅ 24(1)ን እና ሌሎችን አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን የተላለፈ ነው መሆኑን አመልቷል፡፡

ተከሳሾች ይሄንን ሀሰተኛ የስም ማጥፋት ዘገባ አንድነት ላይ በማሰራጨታቸው የተነሳ በከሳሽ ላይ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ ችግር ከመፍጠሩም በላይ አባላቶችና ደጋፊዎቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ ማሳቀቅ፤ ማስፈራራትና ማንገላታት እንዲደርስ ምክንያት እየሆነ ነውም ይላል፡፡

ፓርቲው የተፈፀመበትን ሀሰተኛ የስም ማጥፋት ዘገባ ማስተባበያ መልስ እንዲያወጡለት ተከሳሾችን የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 አንቀፅ 4(1) (ለ)ን መሰረት በማድረግ ቢጠይቅም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች በከሳሽ ላይ ያቀረቡትን ሀሰተኛ የስም ማጥፋት ዘገባ ተገደው ማስተባበያ መልስ እንዲያወጡና ላደረሱትም የህሊና ጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ ለማስወሰን ይህንን ክስ ለማቅረብ ተገድጃለሁ በማለት የክስ ዝርዝሩን ያጠቃልላል፡፡

አንድነት ፓርቲ ከፍ/ቤቱ የሚጠይቀው ዳኝነትም፡-

- በአኬልዳማ ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የከሳሹን ስም በሀሰት እንዳጠፉ እንዲወሰን
- ተከሳሾች ለፈፀሙት የስም ማጥፋት የሀሰት ዘገባ ማስተካከያ መልስ እንዲያወጡና እና
- ተከሳሾች ላቀረቡት የስም ማጥፋት ዘገባ መልስ እንዲያውጡ በከሳሽ ተጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆኑና ለክሱ መቅረብ ምክንያት ስለሆኑ በክሱ ምክንያት የወጣውን ወጪና ኪሳራ ለከሳሽ እንዲከፍሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463 መሠረት ትዕዛዝ እንዲሰጥልኝ በማለት እጠይቃለሁ ይላል፡፡

እሱም ሚያዝያ 29 ቀን 2004 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት ክሱ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 9ኛ ምድብ የፍትህ ብሔር ችሎት እንደሚሆን ያገኘው ማስረጃ ያመለክታል፡፡

## የዋልድባ ገዳም ...

ከገፅ 15 የዞረ

መድረሱንና መነኮሳቱም አደጋ ላይ እንደወደቁ በመግለፅ ይህንንም ለመታደግ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድ ላይ እንዲነሳ ሲኖዶሱ አቅርቧል፡፡ ለዚህም ሲኖዶሱ በምክንያትነት ያነሳው ገዳሙ ንብረትነቱና ሀብትነቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን የሀገር ቅርስ በመሆኑም የመላው ኢትዮጵያውያን ንብረት ስለሆነ ሁሉም ዜጋ ገዳሙን ለመታደግ ሊረባረብ እንደሚገባ መግለጫው ጠቁሟል፡፡ የኃይማኖቱ ተከታዮችም መንግሥት በልማት ስም እያደረገ ያለውን የሀገር ቅርስ እና ኃይማኖትን የማጥፋት ሥራ በአንድ ላይ በመሆን ሊያወግዙና ሊያስቆሙ እንደሚገባ በመግለፅ በሀገር ውስጥ ያሉ አባቶች በተለይ በጠቅላይ ቤትክህነት ያሉት ምንም እንኳ ተፅዕኖ ቢኖርባቸውም አጥብቀው ሊጠይቁና ገዳሙን ሊታደጉ እንደሚገባም ሲኖዶሱ ጠይቋል፡፡

ስለ ጉዳዩም አዲስ አበባ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅዱስ ሲኖዶስ ወቅታዊውንና ተያያዥ መረጃዎችን እንዲሰጡን የሲኖዶሱን ዋና ፀሐፊ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ህዝቅኤልን ጠይቀናቸው ነበር፡፡ አቡነ ህዝቅኤል በበኩላቸው በአካል ሄደው እንዳላዩና የደረሳቸውም መረጃ ባለመኖሩ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልፀውልናል፡፡

# ኢትዮጵያውያን ሀገራችን የት ነው?



ኢ/ር ዘለቀ ረዲ

ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ በፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ አንድ የካርቱን ስእል በማዬቴ ነዉ፡፡ በዚህ ጋዜጣ ላይ ያዬሁትን የካርቱን ስዕል ሞፈርና ቀንበር የተሸከሙ ገበሬዎችን የክልሉ ፕሬዚዳንት በመጥረጊያ እየጠረጉ “ወደ አገራችሁ ሂዱ” እያሉ ከደቡብ ክልል ሲያባርሯቸዉ “ሀገራችን የት ነዉ?” ብለዉ ሲጠይቁ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይህንን የከርቱን ስዕል ስመለከት በእርግጥ የእነዚህ ገበሬዎች ብቻ ሳይሆኑ “የኢትዮጵያዊ ሁሉ ሀገሩ ወዴት ነዉ?” የሚል ሀሳብ በውስጤ ተመላለሰ እና ለመጻፍ ተገደድኩ፡፡ ይህንን ለማለት ያስገደደኝ ደግሞ ሁለት ምክንያቶች አሉ፤

የመጀመሪያዉ እኔ እንኳን የተወለድኩበትን ቦታ ይቅርና የወለደችኝን እናቴን እንኳን አላዉቃትም፡፡ ይህንን እናትን ያለማወቅ ጉዳይ እኔ ብቻ ሳልሆን ማንም “እናትህ ነኝ” ያለችዉን ሰዉ በእምነት ከመቀበል ዉጭ እርግጠኛ መሆን አይችልም፡፡ አንዲት ምስኪን እንደወለደችኝ እርግጠኛ ሆና እኔ ግን እናቴ መሆኗን በእምነት የተቀበልኳት ናት፡፡ ይህቺ ሴት አልተማረችም፤ እኔን ግን አረቄ እያወጣች አስተምራኛለች፡፡ በዚህን ጊዜ ዘጠኝ ወር አርግዛ ሶስት ዓመት እንዳጠባችኝ ስትነግረኝ እንደማትዋሸኝ ስለምቀበል እናትነትዋን አምኜ ተቀበልኩ፡፡

ሁለተኛው በእርግጥ በዚህች አትዮጵያ በምትባል ሀገር ዉስጥ ስንት ሀገር አለ? እንኳን አሁን ዓለም አንድ መንደር እየሆነች በመጣችበት ጊዜ ይቅርና ባልሰለጠነው ጊዜ እንኳ ቢሆን ኢትዮጳያዊ ሀገሩ አንድ ነች፡፡ አማራ የሚባል ሀገር ወይም ኦሮሞ የሚባል ሀገር እንዲሁም ሌሎችን ብሔሮች የሚወክል ሀገር አልነበርም፡፡ ትግራይ ሲነካ ሀዲያ፣ ጉራጌ፣ ሶማሊያ፣ ኦሮሞ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል የሁሉም ሀገር ኢትዮጵያ ነች፡፡ ታዲያ አሁን እዚሁ ሀገር ተወልደዉ አድገዉ ወደ አገራችሁ ሂዱ የሚባል ከሆነ ዛሬ ኑና አልሙ ብለን ሰፋፊ መሬት የሰጠናቸዉ የዉጭ ሀገር ኢንቨስተሮችስ ቢሆን የነገ ዋስትናቸዉ ምንድን ነዉ? በእርግጥ በርካቶች ኑሮና ፖለቲካን መቋቋም አቅቷቸዉ ከሀገራቸዉ እሚሰደዱበት ሀገር ደርሰው መከራ ከሚቀበሉት በተጨማሪ በየመንገዱ የአንበሳ፣የጅብ፣የዉሃ እና የአሳ ነባሪ እራት የሆኑት ህልቆ መሳፍርት የላቸውም፡፡ እነሱ አንድ ጊዜ ሀገራቸዉ ከመቀመጥ ወደ ሌላ ለመሰደድ ሞክረዉ በደል እየደረሰባቸዉ መሆኑ የሚታቅ ሲሆን ሀገር አለን ብለዉ እዚሁ ሀገራቸዉ ለመቀመጥ የመረጡት ላይ እንዲህ ዓይነቱ ግፍና መከራ ሲደርስባቸዉ በእጅጉ አሳዛኝም አሳፋሪም ነዉ፡፡

የአበሻ ጀብዱ በተባለዉ መጽሐፍ ላይ እንደተጠቀሰዉ ጣላት በትግራይ በኩል ገብቶ ሀገሪቱን በወረረ ጊዜ የከምባታ ልጆች ሀገራቸዉ ስለተወረረ ከከምባታ ድረስ ሄደዉ እንደተዋጉና ለዳር ድንበራቸዉ እንደተዋደቁ ያትታል፡፡ የሰላሌ፣የወሎ፣የጎንደር፣የየ ም፣የጎጃም፣የባሌ፣የጂማ፣የከፋና ሌሎችም ጭምር “ክተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት” ብለዉ ሀገራቸዉን ሞተዉ አድነዋታል፡፡ ወጣቱ አቢቹ ትምህርቱን አቋርጦ ከሰላሌ ትግራይ ሄዶ ሁለቱን ወንድሞቹን አጥቷል፡፡ ግን ኦሮሞ እንጂ ትግሬ አልነበረም፡፡በዚያ ጦርነት ላይ የሱማሌ ልጆች መኪና በመንዳት የጉራጌ ልጆች የመኪና መንገድ በመስራት ከፍተኛ ተጋድሎ እንዳደረጉ አስረድቷል፡፡ እዉነት ያን ጊዜ እነአቢቹ እና የሱማሌም ይሁን የከምባታ እንዲሁም ያባጅፋር ልጆች ትግራይ መኖር ቢፈልጉ ኖሮ አገራችሁ ሂዱ ልቀቁ ይባሉ ነበርን? ፈጽሞ አይባሉም ነበር፡፡ የክልሉ መንግሥት ምን እየሠራ ነዉ ያሰኛል፡፡ ከፌደራል መንግሥት መመሪያ ተሠጥቶት ይሆን? ወይንስ በራሱ አነሳሽነት? ምንም ይሁን ምን የተወሰደው ርምጃ ዘግናኝ ነው፡፡ መሪ ማለት ምን ማለት ነዉ? መሪ ማለት እኮ የጎጥም ይሁን የቀበሌ የወረዳም ይሁን የክልል ህዝቡን በአግባቡ የሚያስተዳድር ማለት ነዉ፡፡ህዝብ ከህዝብ ጋር ተፋቅሮ እንዲኖር የሚያደርግ ማለት እንጂ ህዝብ ከህዝብ የሚለያይ ማለት አይደለም፡፡ የእስልምና ሀይማኖት መሪ የነበሩት ነቢዩ መሐመድ ህዝባቸዉ በአረብ ሀገራት ፈተና ሲገጥማቸዉ ተከታዮቻቸዉን የሐይማኖቱ ጠላቶች ሊያጠፏቸው ሲሉ ተከታዮቻቸዉን ለማትረፍ ኢትዮጵያ ወደምትባል ሀገር ነበር የላኩዋቸዉ፡፡ መሪ እንኳንስ ለዜጎቹ ይቅርና በሀገሩ ላይ የሌሎች ሀገራት ዜጎች እንዲበደሉና ፍትሕ እንዲያጡ አይፈቅድም፡፡ በዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን ምንነካን? ምነው እንደ ሥጋ በል አውሬ ጨካኞች አደረገን?

እኔ የደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት የሰጡት ትዕዛዝ ገበሬዉን እንዳፈናቀለዉ የእርሳቸዉን ፊርማ ያለበት ወረቀት ስመለከት በእጅጉ ነዉ ያዘንኩት፡፡ እኚህ ሰዉ መቼም የኢትዮጵያ ህዝብ ህዝብንና ስርዓትን ለይቶ የሚያዉቅ ህዝብ ነዉ እንጂ ለደቡብ ምን እያስቀመጡ ነዉ ለሚለዉ ጥያቄ መልሱን እንኳን እኔ እርሳቸዉም ያውቁታል ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ነገ ደቡብ ሱዳን ወይም እርሷን ከለላ አድርጎ ወራሪ ቢመጣ ማን ነዉ የሚዋጋዉ? የኢትዮጵያ ህዝብ አይደለምን? ደግሞ እኚህ ሰዉ ይህንን መሰል መመሪያ ሲያወጡ ተዉ የሚላቸዉ ባይኖር እንኳን፤ ይህንን መመሪያ አንቀበልም የሚሉ የአካባቢ ባለስልጣናት መኖር ተገቢ ነዉ? እሳቸውንም ከታወረ ጥላቻ ያድናቸው ነበር፡፡ ይህ ዓነቱ ጉዳይ የግለሰቦች ያልሆነና የህዝብ ስለሆነ ህዝብ በዚህ ጉዳይ ላይ ዝም ይል ዘንድ አይገባም፡፡ “ዝምታ ወርቅ ነው” የሚለዉ መልካም አባባል በእርግጠኛነት ይህንን ይጨምራል ብሎ መገመት ሞኝነት ነዉ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በፍቅርና አብሮ መኖርን ያዉቅበታል፡፡ የሀይማኖትም ይሁን የዘር ምንነት በሀገራችን ጎልቶ የሚታይ ነገር አይደለም፡፡ ብዙዎቻችን የጎረቤታችንን የሀይማኖት ልዩነት ያወቅነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ቤተሰቦቻችን ሁለት የተለያዩ ሀይማኖቶች ኖሯቸው አብረዉ ተባብረዉ በሰረግ፣ በለቅሶው፣ በእድር፣ በማህበሩ፣ ተጋግዘዉ በመኖራቸዉ እኛ ልጆቻቸዉ ቤተሰቦቻችን የተለያዩ ሀይማኖት እንደሚከተሉ ያወቅነዉ በጣም ትልቅ ሆነን ነዉ፡፡ ሙስሊሞቹ በሀገራችን ከተሰሩት ቤተክርስቲያኖች ከግማሽ በላይ የሚሆኑትን ማለት ይቻላል ገንዘብ አዋጥተዉ ድንጋይና እንጨት አምጥተው ነው ያሰሩት፡፡ መሰጊድንም ቢሆን በተለይ በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍል ክርስቲያኑ አዋጥቶ ነዉ የሚሰራው፡፡ ወሎንና መርካቶን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንግዲህ ይህንን በሀይማኖት መሀከል እንኩዋን ያለዉን ልዩነት ለማወቅ የሚቸግረዉን የህብረተሰብ ክፍል ወደ አገርህ ሂድ ማለት እነዴት ይቻላል?

ሀገር አንዲት ነች፡፡ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ወደ ፈለገዉ ክልል ሄዶ ሰርቶ መብላት እንዲችል የመስራትና በፈለገዉ አካባቢ ተንቀሳቅሶ የመኖር መብት ህገመንግስቱ ፈቅዶለታል፡፡ ታዲያ የሀገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነዉ ህገ መንግስቱ የፈቀደለትን መብት አንዱ ግለሰብ ወይንም የተወሰኑ ግለሰቦች ወይንም የተጠናወታቸው ቡድኖች የሰዎችን በነጻ የመንቀሳቀስ መብታቸዉን ሲገፉና ታላቁን ህገ መንግስት ሲጥሱ ህገ መንግስቱን በመጣሳቸዉ እንዴት ሊወቀሱ እና ሊከሰሱ አልቻሉም? የሚለዉ ጥያቄ ለእኔ እና እንደኔ መልሱን ለሚፈልጉ ሁሉ ትክክለኛዉን መልስ ማግኘት አስቸጋሪ ይመስለኛል፡፡ አንዳንዶች ህገመንግስቱን ለመናድ ተንቀሳቅሰዋል ተብለዉ በቃልቲ ማረሚያ ቤት የሚገኙ ሲሆን፣ አንዳንዶች ደግሞ ከመንቀሳቀስ አልፈዉ ህገ መንግስቱን ሲጥሱ ለምን አልተጠየቁም?ሊጥሱ ተንቀሳቅሰዋል ከተባሉትና እየጣሱ ካሉት ወንጀሉ የትኛዉ ነው የሚበልጠው? ክልሎች የራሳቸዉ ህገ መንግስት ሊኖራቸዉ ይችላል፡፡ ነገር ግን የፌዴራሉን ህገ መንግሰት የሚጥስ ከሆነ ፌዴራላዊ አስተዳደሩ የት አለ? ጥቅሙስ ምንድን ነዉ?

አሁን ከቦታቸዉ እየተፈናቀሉ ያሉትን ህብረተሰብ ችግርና መከራ ለማወቅና ለመገንዘብ የግድ ተፈናቃዮቹ አንዱን መሆን የግድ አይደለም፡፡ አያስፈልግምም፡፡ ለፍተው ደክመው ካፈሩት ንብረትና ሀብት ህጻናት

ወደ 7 ዞሯል

# ድህነት እና ...

ከገፅ 3 የዞረ

በጣም ዝቅተኛ ነው፤ (ከ2% በታች) ፤አሁንም ከሌላ ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ወደ 14 ሚሊዮን የሚሆነው የገጠሩ ህዝብ ረሀብተኛ ነው፤ የሚተዳደረውም ከውጭ በሚመጣ የርዳታ እህል ነው፡፡ ስለዚህ በዘርፉ ላይ ይህ ነው የሚባል እድገት ካለ ይህ በየጊዜው እየጨመረ የሚመጣው ረሀብተኛ ለምንና ከየት መጣ? ባጠቃላይ መንግስት የሚከተለው የግብርና መር ፖሊሲ በአብዛኛው የአገሪቱ ህዝብ የሚተዳደርበትን ዘርፍ (ወደ 83% የሚሆነው ህዝብ) ትኩረት መስጠቱ ጥሩ የነበረ ቢሆንም ለሌሎች ዘርፎች (በተለይ ለኢንዱስትሪና ለማዕድን ልማት ዘርፎች) የሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ፤ እና በሌሎችም ፖሊሲዎች ባለመታገዙ አገሪቱ ማስመዝገብ የነበረባትን እድገት አቀጭጮታል፡፡ በዚህም ምክንያት ዜጎች ለረሀብ፤ ለርዛትና ለአስከፊ ድህነት ተዳርገዋል፡፡ በሌሎችም የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዘርፎች ላይ አስደንጋጭ የሚባል የፖሊሲ ድክመት ተስተውሏል ፡፡ አንድ ቀላል ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል የመሬት ፖሊሲውን እና የትምህርት ፖሊሲን ማየት በቂ ነው፡፡ የመሬት ፖሊሲው የዜጎችን ንብረት የማፍራት መብት የገፈፈና መንግሰት ብቻውን መሬትን ቸብቻቢ ያደረገ ነው፤ የተዛባው የትምህርት ፖሊሲም የትምህርት ጥራት እንዲያሽቆለቁል እድርጎ ተማሪዎች ማወቅ የሚገባቸውን ነገር እንዳያውቁ፤ አገሪቱም ብቁ የሆነ ተረካቢ እንዳታፈራ አድርጓል፡፡ በሌሎች ዘርፎችም ብዙ የሚባል የፖሊሲ ችግሮች በኢህአዴግ መንግሰት ተስተውለዋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን ችግር ያለባቸው ፖሊሲዎች ተገምግመው አስከፊ ችግር ሳያስከትሉ በፊት ለመቀየር ወይም ለማስተካከል አለመሞከሩ ነው፡፡ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ህዝብ - «ይህ ፖሊሲ ልክ አይደለም፤ በዚህ ምክንያት ችግር እያስከተለ ነው» - ብሎ በሚያስረዳበት ጊዜ ገዢው ፓርቲ - “... አልሰማም፤ መስሚያ የለኝም እንደዚህ የምትሉት እነ እንትናን ስለሆናችሁ ነው” - እያለ ለብዙ አመታት ሲሟገት ከረመ፡፡ አለመታደል ነው፡፡ ወይ በጥንቃቄ የተጠና ፖሊሲዎች አልተረቀቁ ወይ ችግሮች እየታዩ ከስህተት በመማር በፍጥነት መስተካከል(መቀየር) ያለባቸውን ነገሮች አልተስተካከሉም፡፡ አለመታደል ነው፤ ይህ አይነቱ ሁኔታ በአገራችን ላይ ቢያንስ ላለፉት ሶስት መንግስታት ላይ ጎልቶ ታይቷል፤ አሁን ደግሞ ብሷል፡፡

የፖሊሲዎች አተገባበር፡ በአተገባበር ላይ የነበሩ ችግሮችን መንግስታችን ያመነው ጉዳይ ሲሆን ብዙ ጊዜም “በ...ፖሊሲ አተገባበር ላይ ችግር እንደነበረ ተገለፀ” የሚሉ አሰልቺ ዜናዎችን በተደጋጋሚ ሰምተነዋል፡፡ የሚገርመው በተደጋጋሚ መንግስት የአተገባበር ችግር እየገጠመው በአንድ በኩል ሊያስተካክለው አለማቻሉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ችግሩንም ገምግሞ ችግር ያለበት ቦታ አስተዳደሩን አለማሻሻሉ ወይም አለመለወጡ ነው፡፡ ለዚህኛው በቀላሉ ምሳሌ መሬት ጉዳይ አካባቢ ያሉትን “የራሳችን ሌቦች” የተባሉትን አስተዳደሮች መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተለይ ይህኛው ችግር ማለትም የአተገባበር ችግር ያለበት አስተዳደር አለመሻሻሉ ወይም አለመለወጡ ሲደጋገም የችግሩ በዋናነት ያለው አገሪቱን በማስተዳደር ላይ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ላይ እንደሆነ በቀጥታ ያሳየናል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተደጋጋሚ መንግስታቸው «ልማታዊ ነው» ይበሉ እንጂ፤ ሀቁ ግን ይህ መንግስት ቅኝቱ ሁሉ ፖለቲካዊ (ለፖለቲካ ጥቅም ሲባል) ለዛውም ለተወሰኑ ግለሰቦች በስልጣን መቆየት ነው፡፡ ይህም በአገሪቱ የልማት ፖሊሲዎች አተገባበር ላይ ከባድ ችግር አስከትሏል፡፡ መንግስት ባጠቃላይ ሲጨነቅለት የነበረውና አሁንም እየጨነቀው ያለው ስልጣን ላይ እንዴት ተደላድሎ እንደሚቀመጥ ብቻ ነው፡፡ ነጻነትን፤ መብትን፤ እንዲሁም ልማት ጭፍልቅልቅ... ቢሉ ደንታው አይደለም፡፡ ወንበሩን የነኩበት ሲመስለው ሲደናበር የማያጠፋው ጥፋት የለም፡፡ በዚህ ምክንያትም ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊም ይሁን ማህበራዊ ልማቶችን ሲያስብ መጀመሪያ የሚያስቀድመው ፖለቲካውን፤ ስልጣኑን ነው፡፡ ለዚህ ቀላል ምሳሌ ፖለቲካውን የሚያደምቁለትን ነጋዴዎች «ልማታዊ ነጋዴዎች» ብሎ ማፍጠሩ፤ ሌላውን ነጋዴ በነፃነት እንዲሰራ ከመፍቀድ ይልቅ በአሳሪ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች እንዲሁም ከአቅም በላይ በሆኑ ግብሮች ነጋዴውን ሲቀፈድድ ይታያል፡፡ ወደ ግብርናው ከሄድን ደግሞ የልማት ሰራተኞችን ግብርናው ላይ አተኩረው እንዲሰሩ ሳይሆን እርሶአደሩን ፖለቲካ ብቻ እንዲሰብኩት ሲላቸውም በማዳበሪያና በምርጥ ዘር እንዲያስፈራሩት መደረጉ፤ ራሱም መንግስት “ለፖለቲካው ታማኝ ይሁን እንጂ...” የሚላቸው አመራሮች፤ ምን ያህል መንግስት ልማታዊ ነኝ ይበል እንጂ ልማትን ተገን አድርጎ የስልጣን ጥሙን ህዝብን በማፈን የሚወጣ የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡

በጣም የሚያሳዝነው አገሪቱ ውስጥ ያለው አስከፊ ድህነት እና ስራ አጥነት ከመጨመሩም በላይ ውጤቱ ሴት እህቶቻችን ላይ በእስከፊው ሁኔታ እየታየ መሆኑ ነው፡፡ የማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያሳየው ባለፈው አመት ብቻ በህጋዊ መልኩ ወደውጭ ከሄዱት 21269 ሰዎች ውስጥ ወደ 81 % ሴቶች ናቸው፡፡ ህገ ወጡ ቁጥርምከፍተና ነዉ፡፡ በተለይ እህቶቻችን ወደ ውጭ የሚሰደዱበት አንዱና ዋናው ምክንያት የራስንና የቤተሰብን ኑሮ (አብዛኞቹ በትንሹ እስከ 5 ቤተሰብ ያለው ቤት የሚያስተዳድሩ ይሆናል) ለማሻሻል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እነዚህ እህቶቻችን የራሳቸውን ብቻ ሳይሆን የቤተሰቦቻቸውን

# የአዋቂ አጥፊው . . .

ከገፅ 12 የዞረ

ሲቀርቡ፣ "በእናንተ ጉዳይ አልገባም፤ተስማምታችሁ ሥሩ" ነበር የሚሉት! ጠ/ምኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ደግሞ በምንም ዓይነት በአቶ ምናሴ ሥራ ውስጥ ጣልቃ አይገቡም ነበር!

አቶ ተክለወልድ አጥናፉ ስለ ገንዘብ ኢኮኖሚክስ ከአቶ መለስ ዜናዊ የበለጠ እንደሚያውቁ አልጠራጠርም፡፡ አቶ መለስ የሚበልጣቸው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቻ ይመስለኛል፡፡ አቶ ተክለወልድ እንኳን እንግሊዘኛ አማርኛም ያዝ ያደርጋቸዋል፡፡ ለዚህ ነው መሰለኝ፣ከፈረንጆች ጋር መገናኘት እምብዛም የሚወዱት ነገር አይደለም፤ በተለይ ከእነዚህ ከተረገሙ" የዓለም የገንዘብ እና የዓለም ባንክ ኤክስፐርቶች ጋር እነዚህ ፈረንጆች የማይጠይቁት ነገር የለም፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ከሁለት ክፈሉት ይሏቸዋል፤ አቶ ተክለወልድ ይህቺ ሃሣብ በአቶ መለስ እንደማትወደድ ስለሚሚያውቁ፣በተቻለ መጠን ፈረንጆቹ ቢሯቸው እንዳይመጡ ለማድረግ ይሞክራሉ! ግን የሥራ ኃላፊነታቸው ስለሚያስገድዳቸው፣ሁል ጊዜ ፈረንጆቹን "መሸወድ" አይችሉም፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ አቶ ተክለወልድ ስለገንዘብ ኢኮኖሚክስ ያላቸው ዕውቀት ከአቶ መለስ ይበልጣል እንጂ አያንስም፡፡ እንደሚታወቀው፣የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገንዘብ ማሳተም ያለበት ያረጃ የብር ፎት ለመተካትና ለተጨማሪ ምርት ግብይት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የገንዘብ ፍላጐት ለማሟላት ነው፡፡ አቶ ተክለወልድ ግን ለአቶ መለስ ገንዘብ ባጠራቸው ቁጥር በገፍ እያሳተሙ ይሰጧቸዋል፡፡ አቶ መለስ ለካድሬ እና ለሰላይ መንጋቸው ደመወዝ የሚከፍሉት በዚህ መልክ እየታተመ በሚሰጣቸው ጭምር ነው፡፡ እስኪ፣አሁን የካድሬ እና የሰላይ መንጋ ምን ዓይነት ምርት ወይም ተጨባጭ አገልግሎት ሰጥቶ ነው ወፍራም ደመወዝ የሚያፍሰው?! የአቶ መለስን የሥልጣን ዕድሜ ማራዘም ሥራ ነው እንዴ?

ግን አቶ ተክለወልድ የገንዘብ ሕትመቱን አጧጧፉት፤ የገንዘብ መጠን ዕድገት በዓመት ሃምሣ በመቶ እስኪደርስ! አቶ ተክለወልድ በባንኩ የቀጠሯቸው ኢኮኖሚስቶች፣ "ኧረ ይህ ነገር ከቁጥጥር ውጪ እየወጣ ነውና አንድ ነገር ይደረግ" ሲሏቸው፣ "ኖ ኖ! በኢትዮጵያ የዋጋ ንረት መንስዔ የገንዘብ መጠን መበርከት አይደለም፡፡ መንስዔው ከውጭ ሀገር የሚዘመተው የዋጋ ንረት (imported inflation) ነው" እያሉ አፋቸውን ያስያዟቸው ጀመር፡፡ ኢኮኖሚስቶቹ በሚያገኙት ደመወዝ የዋጋ ንረቱን መቋቋም ሲያቅታቸው፣የተሻለ ደመወዝ ወደሚከፍሉት የግል ባንኮች ፈለሱ፡፡ ለነገሩ፣አቶ ተክለወልድ እያቅማሙም ቢሆን፣ለሠራተኞቻቸው በየጊዜው መጠነኛ የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ (bonus) ይሰጣሉ፤ግን ጭማሪው የዋጋ ንረቱን ስለማያካክስ፣የሠራተኛ ፍልሰቱ እስካሁንም አልቆመም፡፡ እሳቸው በግላቸው ጠብሰቅ ያለ የቤት ኪራይ ገቢ ስላላቸው፣ ስለደመወዝ ብዙም አይጨነቁም፡፡

ለአቶ ተክለወልድ አጥናፉ የብሔራዊ ባንክ ገዥነት በኢትዮጵያ የዋጋ ንረት በዓመት ከስልሣ በመቶ (60 በመቶ) በላይ የሆነባቸው ጊዜያቶች አሉ፡፡ አሁን በዓመት ወደ 36 በመቶ ነው፡፡ ይህ አሓዝ ከዓለም ከፍተኛው እንደሆነ ተገምቷል፡፡ በጠ/ሚንስትሩ ትዕዛዝ መሠረት ለበጀት ጉድለት ማሟያ እያሉ፣ከመጠን ያለፈ ገንዘብ ለመንግሥት ከማበደራቸው በተጨማሪ፣የመንግሥት ባንኮች ከሆኑት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ከቢዝነስ እና ኮንስትራክሽን ባንክ ከፍተኛ ብድሮች፣ከባንክ ብድር አሰጣጥ ሕግና ደንብ ውጪ፣ "በበላይ ትዕዛዝ" እንዲሰጡ ፈቅደዋል፡፡ ይህ ሁሉ የዋጋ ንረትን በማባባስ ረገድ ከፍተኛ አሉታዊ ትፅዕኖ አድርጓል፡፡ ከዘመነ ኃ/ሥላሴ ጀምሮ ይሠራበት የበረውን የመንግሥት ብድር ጣሪያ (government borrowing limits) ከባንኩ አዋጅ ውስጥ አሰርዘውታል፡፡ ከፋይናንስ ሕግ ውጪ የግል ባንኮች በየዓመቱ ከሚሰጡት ብድር ውስጥ ሃየ ሰባት በመቶ በሦስት በመቶ የወለድ ተመን የመንግሥት ቦንድ እንዲገዙ አስገድደዋል፡፡ እግዚአብሔር ያሳያችሁ! የግል ባንኮች የሚያበድሩትን የቁጠባ ገንዘብ የሚሰበስቡት አምስት በመቶ ወለድ እየከፈሉ ነው! በራሳቸው ውሳኔ በድንገት የብር የውጭ ምንዛሪ ተመን ሲቀነስ፣በእጃቸው ላይ በርከት ያለ የውጭ ምንዛሪ ይዘው የነበሩ የግል ባንኮች ትርፍ ሲያገኙ፣ "ይሄማ እንዴት ይሆናል?" ብለው "የስዩ አዋጅ" ዓይነት በአንድ ጀንበር አስወጥተው፣የትርፋን ሰባ አምስት በመቶ በ "ንፋስ አመጣሽ" አስነጠቋቸው!

የወለድ ተመኑ ከዋጋ ንረቱ እጅግ በጣም ያነሰ በመሆኑ፣ በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ የመግዛት ኃይል በየቀኑ እየተሸረሸረ መሆኑን እያወቁ፣በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈለውን የወለድ ተመን በአንድ በመቶ ብቻ ጨመሩ፤ ማለትም ከ4 በመቶ ወደ 5 በመቶ፡፡ አሁን ባለው የዋጋ ንረት እንኳን፣በባንክ የተቀመጠ ገንዘብ የመግዛት ኃይል በዓመት በ31 በመቶ እያሽቆለቆለ ነው! ለምን ይህን እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ፣ "የእኛ ሀገር ሕዝብ በባንክ ገንዘብ የሚያስቀምጠው ወለድ ለማግኘት አይደለም" ብለው መልስ ይሰጣሉ፡፡ ይህ ላይ ላዩን ሲያዩት እውነት ሊመስል ይችላል፤ ምክንያቱም የወለድ ተመን ዝቅተኛ ሆኖም የባንክ ተቀማጭ ገንዘብ እየጨመረ ነው! ነው፡፡ ይህ እንግዲህ እውነት ይሁን አይሁን አይታወቅም፡፡ እሳቸው የሚመሩት ባንክ የሚያወጣው ሪፖርት ተአማኒነት፣ማዕከላዊ ስተትስቲክስ ባለሥልጣን ከሚየወጣቸው አሓዞች የበለጠ ሊታመን የሚችል አይመስለኝም፡፡ ዋናው ቁም ነገር ግን፣የባንክ ተቀማጭ ገንዘብ ሊያድግ የሚችለው፣በአብዛኛው እሳቸው በገፍ የሚበትኑት ገንዘብ ተመልሶ ወደ ባንክ ስለሚመጣ ነው! ሰፊው ሕዝብ ግን እንደ መምህራኑ ሁሉ ከዕለት ጉርስ ተርፎ ሊቆጠብ የሚችለው ገንዘብ እንደሌለው ማንም ሰው የሚያውቀው ነው፡፡

አቶ ተክለወልድ አያወቁ የኢትዮጵያን የገንዘብ ፖሊሲ (monetary policy) ምስቅልቅሉን አውጥተውታል፡፡ ከላይ ስማቸውን የጠቀስኳቸው የዘመነ-ኃ/ሥላሴ ስመ ጥር የብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ምናሴ ለማ ከመቃብር ተነሥተው ይኼውን ጉድ ቢያዩ ምን ይሉ ይሆን? እርግጠኛ ነኝ፣ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ

# ፍትህ አጣሁ ያለው የመንግስት ሠራተኛ ፍ/ቤት ግቢ ውስጥ ካለው ዛፍ ወጥቶ አልወርድም አለ

በደቡብ ክልላዊ መንግስት ዳውሮ ዞን ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰው ሀብት ኃላፊ የነበሩት አቶ አባተ አየለ "ፍትህ አጣሁ" በማለት ፍ/ቤቱ ግቢ ውስጥ በሚገኝ ዛፍ ላይ ወጥተው አልወርድም ማለታቸውን የዜና ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "አቶ አባተ አየለ በአመለካከታቸው ምክንያት ተደጋጋሚ በደል ተፈጽሞባቸዋል" ይላሉ፡፡

ምንጮቻችን እንደሚሉት "አቶ አባተ አየለ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ አባል ናቸው፡፡ በአመለካከታቸው ምክንያት በተደጋጋሚ እያሠሩና እያጉሳቆሏቸው ቆይተዋል፡፡ በረሃ ወሰደው አስረዋቸዋል፡፡ ያለ ምንም ጥፋት ከሥራ አባረዋቸዋል፡፡ መ/ቤቱን ፍ/ቤት ከሶ ወደ ስራ እንዲመለስና የኃላ ቀሪ ደመወዙ እንዲከፈለው ተወስኖለታል፡፡ የደረሰበትን በደልም ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አመልክከቶ ተቋሙ አቤቱታውን በዝርዝር ተቀብሎታል፡፡ የፍ/ቤቱን ውሳኔ ለማስፈፀም በመንቀሳቀስ ላይ እያለ ፖሊስ ለምን እንባ ጠባቂ ተቋም አመለከትክ? እንዴት መ/ቤቱን ትከሳለህ? ብለው በድጋሚ አሰሩት፡፡ ጥፋት ካጠፋሁ ፍ/ቤት አቅርቡኝ እንጂ ወደ ሌላ ቦታ አልሄድም፡፡ ብሎ እንቢ በማለቱ ፍ/ቤት ግቢ ይዘውት ገብተዋል፡፡ በትላንትናው ዕለት ፍ/ቤቱ ግቢ ውስጥ እንደገባ ሮጦ በፍ/ቤቱ ግቢ ውስጥ በሚገኝ አንድ ዛፍ ላይ ወጥቶ ተቀምጧል፡፡ ውረድ ቢባል አልወርድም፤ የአካባቢው ባለሥልጣናት በጠቅላላ መጥተው ያነጋግሩኝ፤ በዳውሮ የህግ የበላይነት የለም፤ ፍትህ የለም፡፡ ፍትህ በሌለበት ሁኔታ መኖር አንችልም፡፡ በማለት ድምጹን ከፍ አድርጎ እየጮኸ ይገኛል፡፡ ህዝብ ተሰብስቦ እንዲወርድ ቢለምነው እንቢ ብሎአል፡፡ ሰው ወደ ዛፉ ሲጠጋ ራሴን ከዛፍ ላይ ጥዬ እገለላሁ በማለቱ ማውረድ አልተቻለም፡፡" በማለት ሂደቱን አብራርተዋል፡፡

ወደ ህትመት እስከገባንበት ጊዜ ድረስ አቶ አባተ አየለ ዛፍ ላይ እንዳሉ ሲሆን የአካባቢው ህብረተሰብ ዛፉ ሥር ተሰብስቦ እየጠበቃቸው ይገኛል፡፡ የወረዳው ፖሊስ ጣቢያ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት በተደጋጋሚ በቢሮአቸው ስልክ ላይ ብንደውልም ስልኩን የሚያነሳ ሰው ባለመኖሩ ጥረታችን ለጊዜው አልተሳካም፡፡ ከዚህ ቀደም በዚሁ በዳውሮ ከተማ ነዋሪ የነበሩት መምህር የኔሰው ገብሬ በዞኑ የህግ የበላይነት የለም ፍትህ ዴሞክራሲና ነፃነት በሌለበት አገር መኖር አያሻኝም፤ በማለት በራሱ ላይ ነዳጅ አርከፍክፎ ራሱን በማቃጠል መሞቱ የሚታወቅ ቢሆንም በዚህ ወንጀል እስከ ዛሬ ተጠያቂ ሆኖ ለህግ የቀረበ የአካባቢው ባለሥልጣን አለመኖሩ የአገሪቱን የፍትህ ሥርዓት አጠያያቂ አድርጎታል፡፡

ለመላው የክርስትና ዕምነት ተከታዮች በሙሉ

እንኳን ለብርሀነ ትንሳኤው በሰላም አደረሳችሁ

በዓሉ የሰላም፣ የጤና፣ የፍቅር እንዲሆንላችሁ እንመኛለን

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

# የባህል ባሪያ . . .

ከገፅ 3 የዞረ

ዋጋው ቅጥ ያጣ፣ ለባህል ለባርነት የሚዳርግ፣ ኢኮኖሚን የሚየቃውስ፣ ሥነ-ልቡናዊ ጫናን የሚፈጥርና ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን የማቅረብ አቅም የሚያሳጣ ከሆነ "አያስፈልግም! በቃ!" ማለት መቻል አለብን፡፡ በዚህ የባህል ደረጃ አቋሞችን መውሰድ ካልቻልን፤በመሠረታዊ ዕቃዎች ገበያ ደረጃም አቋም መውሰድ አንችልም፡፡ በዚህ ደረጃም መውሰድ ካልቻልን መንግሥትን በሚመለከት ደረጃም አቋም መውሰድ አንችልም፡፡ በዚህ ሁኔታ እጣፈንታችን የሚሆነው በባህል እያመካኘንና እያልጎመጎምን ባሪያ ሆኖ መኖር ነው፡፡

በሠለጠኑ አገሮች ቆራጥ ዜጎች ከገበያ ባርነት ነፃ ለመውጣት የተደራጀ ተቃውሞ በማሰማት፣ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ጫና ይፈጥራሉ፡፡ በተጨማሪ ነፃ የሸማቾች ማህበራትን በማቋቋም፣ከዚያም አልፈው የመሠረታዊ ዕቃዎች ሱቆችን በጋራ በመክፈት በሸማችነትም በኢንቨስተርነትም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ ይህን ለማድረግ ቁርጠኝነትና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ፣የማያቋርጥ ጥረትን ይጠይቃል፡፡

ከመንግሥት ባርነት ነፃ ለመውጣት፣ባህሉንና ገበያውን በተመለከተ እንደተባለው ቁርጥ አቋም መያዝና በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ መታገል ነው፡፡ ስለ ሠላማዊና ሕጋዊ ትግል በቃል ብዙ ተብሏል፡፡ አሁን የቀረው በዕውቀትና በሕጋዊነት ላይ የተመሠረተ ተግባር ነው፡፡ አምባገነን ሥርዓት በሰፈነበት አገር ውስጥ በዕውቀትና በሕጋዊነት ላይ የተመሠረተ ተግባር ጉዳት ያስከትላል፡፡ መደብደብ፣መታሰር፣መገደል፣ሌላም የጭካኔ ተግባር ይኖራል፡፡ ይህን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆን ይኖርብናል፡፡ ስቃይ የሌለበት መውለድ፣ መደብደብ፣ መታሰር፣መገደል የሌለበት ነፃነት ቢኖር እንዴት ጥሩ ነበር!

ሄንሪ ቫንዳይክ የተባለ አሜሪካዊ ገጣሚ "የድፍረት በሮች" (The doors of daring) በተባለ ግጥሙ እንዲህ ብሏል፡-

Say not too poor but freely give
Say not too weak but boldly try,
You can never begin to live
Until you dare to die

ወደ አማርኛ ሲተረጎም የሚከተለውን ይላል፡-

ደሀ ነኝ አትበል መስጠት ነው ያለህን
ደካማ ነኝ አትበል ሞክር የአቅምህን
አለሁ ብለህ ብትል ዘመን እየቆጠርክ
መኖር አትጀምርም መሞትን ካልደፈርክ፡፡

አዎ፣መሞትን ደፍረን በነፃነት መኖርመጀመር አለብን ነው፡፡ ያለው ሌላው አማራጭ እያማረሩ፣እያልጎመጎሙ፣የሚረገመውን እየረገሙ፣ "እሱ ያመጣዉን እሱ ይመልሰው እያሉ የባህል፣የገበያና የመንግሥት ባሪያ ሆኖ መኖር ነው፡፡ ይህ የኛ ምርጫ ሊሆን አይገባም፡፡

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.37

# ኦህዴድ ሹም ሽር አደረገ

## - የኦሮሚያ ካቢኔ አዳማ ሰማዕታት ግቢ መሽጓል

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ገዢ የሆነው የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኦህዴድ/ ሰሞኑን በድርጅቱ ውስጥ ሹም ሽር ማድረጉን የዜና ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ የውስጥ አዋቂዎች እንደ ገለጹት "ኦህዲድ ሰሞኑን ቁልፍ ቁልፍ የድርጅቱን አመራሮች ከኃላፊነታቸው አንስቷል፡፡" ብለዋል፡፡ "ከኃላፊነታቸው የተነሱ የድርጅቱ ኃላፊዎች በመንግስት የተሰጣቸውን ቦታ ይለቃሉ ወይስ ይቀጥላሉ? በህግ የሚጠየቁበት ሂደት ይኖራል ወይስ ቦታ ቀይረው ይቀጥላሉ? የሚሉት ጥያቄዎች አነጋጋሪ ሆነው የሚገኙ ቢሆንም የኦሮሚያ ካቢኔ ካለፈው ቅዳሜ ጀምሮ አዳማ በሚገኘው ሰማዕታት ግቢ ውስጥ ውሎና አዳራቸውን እዚያው በማድረግ በግምገማ ላይ ናቸው፡፡ ግምገማው የዞንና የወረዳ አመራሮችን ያጠቃልላል፡፡" ተብሎአል፡፡

ምንጮች እንደሚሉት ከኃላፊነትቸው ከተነሱት ውስት የጽ/ቤቱ ኃላፊ አቶ እሸቱ ደሴ፣ የፌደራሉ መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ዲኤታ አቶ አለማየሁ እጅጉ የቀድሞ የጽ/ቤቱ ኃላፊና አሁን ኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ኃላፊና የካቢኔ አባል የሆኑት አቶ ዘላለም ጀማነህ፣ አቶ ለማ መገርሳ ይገኙበታል" ተብሎአል "የኢህዴድ ጽ/ቤጹን ኃላፊነት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር ወ/ሮ አስቴር ማሞ ለጊዜው በያዙት የመንግስት ኃላፊነት ላይ ደርበው እንዲሰሩ መመደባቸውን ለማወቅ ተችሎአል" ሲሉ ገልፀውልናል፡፡

"የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ካቢኔ ካለፈው ቅዳሜ ጀምሮ አዳማ /ናዝሬት/ በሚገኘው ሰማዕታት ግቢ መሽጓል፡፡ ይህ ልዩ ክብደት የተሰጠው ግምገማ በተባለለት ስብሰባ ውስጥ "ማንኛውም ተሰብሳቢ ሞባይልና መኪና እንዳይዝ የተከለከለ ሲሆን ምግብ አደርና ውሎአቸውን እዚያው ግቢ ውስጥ ያደረጉ ሲሆን መግባትም መውጣትም አይቻልም" ተብሎአል፡፡ "በዚህ ግምገማ በርካታ ባለሥልጣናት በሙስና፣ በሥልጣን መባለግ፣ በአመለካከት ችግር አስተዳደራዊ በደል መፈፀምና ፍትህ ማዛባት ተገምግመው ከኃላፊነታቸው ሊባረሩም ሊታሰሩ የሚችሉ ይኖራሉ" ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በተያያዘ ዜና በተደጋጋሚ የጤና መታወክ ገጥሟቸው ነበር የሚባሉት የክልሉ ርዕሰ መስተዳደሩ አቶ አለማየሁ አቶምሳ በበርካታ በዓላትና ዝግጅት ላይ አለመገኘት አነጋጋሪ እየሆነ ነው፡፡አብዛኛውን ጊዜ ከጽ/ቤታቸው የማይለዩት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በቅርቡ አዳማ ባዘጋጀው የመላው ኢትዮጵያ ጨወታዎች መቀሌ ባዘጋጀው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን፣ በአገሪቱ ታላቅ በተባለለት ደርባን ሲሚንቶ ፋብሪካ ምርቃት፣ በዓባይ ግድብ አንደኛ ዓመት ዝግጅት በመሳሰሉት ላይ አለመገኘት አነጋጋሪ ሆኗል ሲሉ የዜና ምንጮቻችን እያይዘው ይናገራሉ፡፡

# የቡራዩ ከተማ አመራሮች ታሰሩ

## - የአዲስ አበባ መግቢያ ኬላዎች በፌዴራል እንዲጠበቅ ተደረገ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት አዲስ አበባ ዙሪያ ዞን ሥር የምትገኘው የቡራዩ ከተማ ሁለቱ ከንቲባዎች ከሌሎች 17 የአካባቢው ባለሥልጣናት ጋር በሙስና ተጠርጥረው ሰሞኑን በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የዜና ምንጮቻችን አስታወቁ፡፡ ምንጮቻችን እንደሚሉት "የከተማው ከንቲባ አቶ ቸርነት ጉርሜሳና የቀድሞ የከተማው ከንቲባ አቶ ኃይሉ ደቻሳ ከሌሎች 23 የአካባቢው ባለሥልጣናት ጋር በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡" ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በየደረጃው ያሉ የመንግስት ባለሥልጣናት "በካሽ ልምጣ ወይስ በክላሽ" እያሉ መሬት የዘረፉበት አካባቢ እየተባለ የሚቀለድበት ቡራዩ ከተማ ባለሥልጣናት በተለያየ ሰው ስም በተደጋጋሚ ቦታ ወስደው በመሸጥ በመለወጥ ከፍተኛ ሙስና ሲከናወንበት ከነበሩት ከተማዎች ውስጥ ቡራዩ አንዷ መሆኗ ይነገራል፡፡ በዚሁ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ 25 የአካባቢው ባለሥልጣናት መታሰራቸው ታውቋል፡፡

በተያያዘ ዜና ከመላው አገሪቱ ወደ አዲስ አበባ መግቢያ የሆኑት አምስቱ ኬላዎች ከኦሮሚያ ፖሊስ ተነጥቆ ለፌዴራል ፖሊስ መስጠቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ ምንጮች እንደሚሉት "ኦሮሚያ ከአዲስ አበባ ልዩ ጥቅም የምታገኝበት መንገድ ወደፊት በህግ ይወሰናል የሚል ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ቢኖርም ጉዳዩ እስከአሁን ድርስ እልባት ባለማግኘቱ ኦሮሚያ ከአዲስ አበባ ከተማ ማግኘት ያለበትን የቀረጥ ታሪፍና የግብር ገቢ ማግኘት አልቻለችም፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ በኦሮሚያ ፖሊስ ይጠበቅ የነበረው ኬላ ተነጥቆ ለፌዴራል ፖሊስ መስጠቱ ቅሬታ ቀስቅሷል" ሲሉ ምንጮች ያብራራሉ፡፡ የዜና ምንጮቻችን እንደሚሉት "ኬላዎቹ ያሉት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ነው፡፡ አዲስ አበባም ቢሆን ኦሮሚያ ናት፡፡ ከኬላዎች የሚገኘው ገቢ የኦሮሚያ መሆን አለበት፡፡ ፌዴራል መንግስት በቀጥታ ኦሮሚያ ውስጥ ገብቶ የክልሉን መንግስት ጥቅም በሚነካ መልክ ጣልቃ መግባቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ቅሬታ ማስነሳቱ አይቀርም" በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

# የዋልድባ ገዳም ደህንነት አሳሳቢ ሆኗል

## - በአሜሪካ የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫ ሰጥቷል
## - የገዳሙ መነኮሳት የድረሱልን ጥሪ አሰምተዋል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ካሉ ታላላቅ ገዳማት በሀገሪቱ ካሉት ቅርስና የቱሪስት መዳረሻዎች መካከል ታላቁ የዋልድባ ገዳም አንዱ ነው፡፡ ገዳሙ ከ13ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ ለመነኮሳትና አበው እያገለገለ እንደሚገኝ የሚታወቅ ሲሆን በዋነኝነት በ15ኛው መቶ ክ/ዘመን በነበሩት ታዋቂው መናኝ አባሳሙኤል ዘዋልድባ እንደተጠናከረ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በውስጡም ብዙ መነኮሳትና መናኒያን የሚገኙ ሲሆን በአሁን ወቅት የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በአካባቢው የስኳር ልማት ለማካሄድ ጥርጊያ መጀመሩ ተገልጿል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የገዳሙ መነኮሳት በስደት ላይ እንደሚገኙና አሁንም የፀጥታው መናጋትን ጨምሮ ገዳሙ ላይ አደጋ እንደተጋረጠ ከሥፍራው ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

መነኮሳቱም የድረሱልን ጥሪ ማሰማታቸው ተገልጿል፡፡ የመነኮሳቱን ጥሪ ተከትሎ ከጐንደር፣ባህርዳር፣አዲስ አበባና መቀሌ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ኃይማኖት ተከታይ ባለሃብቶች ወደ ስፍራው ቢያቀኑም መታወቂያ ሳታሳዩ ወደ ገዳሙ ክልል አትገቡም መባላቸው፤ከዚያም መታወቂያ ካሳዩ በኋላም መግባት እንደማይፈቀድላቸው እንደተነገራቸውና እንደተመለሱ ለዝግጅት ክፍላችን ጠቁመዋል፡፡ ባለሀብቶቹ እንደሚሉት ከሆነ ይህ የሚያሳየው የገዳሙ ደህንነት ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰና ይህንንም ለጠቅላላይ ቤተክህነት፣ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በደብዳቤና በአካል ለመግለፅ እየተዘጋጁ እንዳሉ አስታውቀዋል፡፡ ለዚህም የሚሆን ጉዳዩን የሚከታተል፣የገዳሙንና የመነኮሳቱን የተጋረጠባቸውን አደጋ ለመታደግ የሚያስችል ሥራም ሊሰሩ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

የተለያዩ የኃይማኖቱ ተከታይ ወጣቶችም ወደ ሥፍራው ለመጐብኘት ቢሄዱም ከገዳሙ ረጅም ርቀት ክልል በፌዴራል ፖሊስ መከልከላቸውን ጠቁመዋል፡፡ በገዳሙ አካባቢም በተደረገው ምንጣሮና እርሻ ከ27 በላይ መቃብር ቦታዎች ተነክተው የአስከሬኖች አፅም ተበታትኗል ሲሉ ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ በአሁን ወቅትም በገዳሙ አካባቢ ከፍተኛ ውጥረት መንገሱን በማስታወስ በተለይ መጋቢት 27 ቀን በገዳሙ አመታዊ ክብረ በዓል እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን ይህን ክብረ በዓል ለማክበር የጐንደር ዩኒቨርስቲ እና የጐንደር መምህራን ኮሌጅ ተማሪዎች ለመሄድ መኪና ኮንትራት ከያዙ በኋላ ወደሥፍራው እንዳይሄዱ በመንግሥት ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው ተጠቁሟል፡፡ በተለይ አቶ አባይ ፀሐዬ የስኳር ልማት ፕሮጀክቱ ገዳሙን እንደማይነካና ማንም ሰው ሄዶ ማየት እንደሚችል በኢቴቪ ቢናገሩም፤ነገር ግን ወደ ሥፍራው የሚሄዱ ሰዎች መከልከላቸውን የዓይን እማኞች ገልፀዋል፡፡ የጐንደር ነዋሪዎችም ገዳሙ በአሁን ሰዓት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ያመለክታል ሲሉ ስጋታቸውን ገልፀውልናል፡፡

በስደት መቀመጫውን በአሜሪካን ሀገር ያደረገው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስም ጉዳዩ እንዳሳሰበው በመግለፅ መጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም መግለጫ አውጥቷል፡፡ በመግለጫውም ገዳሙ አሳሳቢ ደረጃ ላይ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል


አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮጋራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል፡፡ ለትግሉ ስኬት የእርስዎ ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮጋራም አዘጋጅቷል፡፡ ለመግቢያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ፡፡ የእራት ግብዣው ግንቦት 24 ቀን፣ 2004 ዓ.ም. ይደረጋል። የሆቴሉ ስም ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም. በሚወጣው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል፡፡

በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያኖች በሀገር ውስጥ በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች አማካኝነት ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ፡፡

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ፣ በቢሮ ስልክ ቁጥር 011-840-08-11 በተንቀሳቃሽ ስልክ 091-161-84-34 ኢ-ሜል፡ andientfinance@yahoo.com ወይም andinet@andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
የሂሳብ ቁጥር፡ 510
ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት መመስረት፣ ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!